

የመለስ
ልቃቂት
ኤርምያስ ለገሰ
300-400

የሚከላከል በመሆኑ ኤፈርት ሞኖፖሊ የሚፈፕርበት እድል እንደሌለም መታወቅ ይኖርበታል" በማለት ምሁራዊ ትንታኔ ሰጠ።

300

የንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚኒስትሩ ትዕምት የግል ባለሀብቶችን ለማገዝ የነደፋቸውን ስትራቴጂዎች አንድ በአንድ አስረዳ። ባለሀብቶች በትዕምት ልማታዊ ጉዞ በመማረካቸው ልምድ እንዲወስዱ መደረጉን ገለጠ። በዘመነ ግሎባላይዜሽን ሀገራችን ኢትዮጵያ ከመሚሸሸ ወደ ተሳፈኝነት፣ ከተሰፈኝነት ወደ ተወዳዳሪነት መሔድ የምትችለው እንደ ኤፈርት ያሉ በአብዬታዊ ዲሞክራት ሀይሎች የሚመሩ ኩባንያዎች ሲኖራት እንደሆነ ተናገረ።

ንግግሩን ሲጨርስ ሞቅ ያለጭብጨባ ተቀበለው። ለካስ ሰዎች ውስጣቸው የተለየ ሆኖ እጃቸው እስኪቀላ ማጨብጨብ ይችሉበታል። እኔም አጨበጨብኩ። ዞር ብዬ ስመለከት አጠገቤ የተቀመጠው ቁጥሮቢች ልብሴን ወደራሱ እየጐተተ "ፍቃደ አዘዘ ጩኸት በሚለው የግጥም መድብሉ 'ለአብዬተኛ ምሁራን' በሚል ርእስ የገጠመውን አስታወሰኝ" አለኝ። እኔም ወደ ጆሮው ተጠግቼ "አንተኮ ስትናገር መቼም ለነገ አትልም" ካልኩት በኋላ የቤተመንግስት ፍተሻው እለት በመናደዱ የሜሜርኳትን እንኳን ቤት ልትመታ የማታንኳኳ እንታአራም ግጥም በቃሌ አልኩለት። ዘመን ተሻጋሪዋ ግጥም "የአሽከሮች ማጀት" የምትባል ነበረች።

ከሚኒስትር አለማየሁ ጋር የነበረን የልብ ለልብ ውይይት በመጠናቀቅ ላይ ሳለ ባትሪውን ወደ ስልኩ ከተተ። ትንሽም ጊዜ ሳይሰጠው ስልኩ ጮኸ። የደዋዩን ስልክ ሲመለከት ባልጠበኩት ሁኔታ ተደናበረ። የእጅ ስልኩን ጥርቅም አድርጐ በመያዝ ድምጹን ዝቅ አድርጐ " ቴዎድሮስ ሆጐስ ነው!...ለምን ፈልጐኝ ይሆን?" በማለት ከተናገረ በኋላ ስልኩን አነሳ። ቴዎድሮስ ሆጐስ ምን እንደሚናገር መስማት ባልችልም ከሚኒስትሩ ምላሽ ተነስቼ ስለምን እንደሚያወሩ ጠርጥሬያለሁ። አለማየሁ ከእኔ ትንሽ ራቅ ብሎ "የጓድ መለስ ገለጻ በጣም ጥሩ ነበር።..." ይላል።

ቴዎድሮስ ሆጐስ የሚለውን ካዳመጠ በኋላ፣

"በጣም ትክክል ነው። ጓድ መለስ ውስብስብ እና አደናጋሪ የሆነውን የማዕድን ልማት ለማብራራት የተጠቀማቸው ምሣሌዎች የሚገርሙ ናቸው በተለይ ስለ ደች በሽታ ብትን አድርጐ ያስረዳው ለስራው ሂደት ባለቤቶችም ጭምር አዲስ እቅም ጨምሮልናል።...የማዕድን ልማት

አብዮታዊ ዴሞ[illegible]ራ[illegible] ከሚ[illegible]ልገው [illegible]ስተማማኝ፣ ፈጣንና ዘላቂ ልማት ጋር የማይሔድ የሊራዊ ሰብሳቢዎች ለጃራጭ መንገድ መሆኑን በጥልቀት ማስረዳቱ በካድሬው ዘንድ የነበረውን ብዥታ ለማጥራት አስችሏል" በማለት ተናገረ። ቴዎድሮስ የሚናገረውን በመጣደፍ መጻፍ ጀመረ።

አለማየሁ የስልክ ወሬውን ሲጨርስ ተጣድፎ ወደ እኔ መጣ። ፀጉሩን በአመልካች ጣቱ ቆፈር ቆፈር እያደረገ፣

"ጓድ! የስልጠናው የበላይ ሀላፊ ቴዎድሮስ ሁሉስ በአስቸኳይ እንዳገኘው ነግሮኛል። ድርጅቱ በአዳራሹ የማቀርበው ጥናታዊ ሰነድ ልኮልኛል። እኔ በፊት የሰጠሁት ይሁን ሌላ አዲስ አላወኩም። በፍጥነት ወደ አዳራሽ መሔድ አለብኝ...የተጫወትነውን የሰይጣን ጆሮ አይስማው" በማለት ተናገረ። ለስንብት ሲጨብጠኝ ሰውነቱ እና እጁ በላቦት ተጨማልቆ ነበር።

ምላሼን ሳይሰማ ሀውልቱ ጋር ጥሎኝ ወደ ገልማ አባገዳ አዳራሽ ሄደ። አለማየሁ ሀሳቡን ሳይጠይቅ በፍጥነት የሔደበት ምክንያት ገብቶኛል። እሱም ገብቶታል። ወደድንም ጠላንም በባርነት ውስጥ የሚኖር ሰው ከርቀት ያሸታውቃል። ራሳችንን እንደ ሰጐን አሸዋ ውስጥ ቀብረን ስለምንኖር ሌላው ያላወቀብን ይመስለናል።

የሚቀፍና የሚከብደው ሀውልት ውስጥ ሳልወጣ ቁጥሮቪች ደወለልኝ። እንደለመደው እየተንቀገቀገ የት እንዳለሁ ጠየቀኝ። የዘመዶቼን ቅልጥምት እየተመለከትኩ እያዘንኩ እንደሆነ ገለጥኩለት። ብቻዬን ተከዤ ስለማያዛልቀኝ አብሮኝ ለቅሶ ለመቀመጥ እየመጣ እንደሆነ ነገረኝ።

ቁጥሮቪች በብርሃን ፍጥነት ደረሰ።

በወረቀት ላይ "የስልክህን ባትሪ ንቀል" በማለት ፃፍኩለት። እንጀቱ ሲሸማቀቅ ተመለከትኩ። ሳልነግረው ለምን እንደዛ እንዳልኩት ገባው። እንደ እውነቱ ከሆነ እንደ ቁጥሮቪች ጠርጣራ፣ ፈሪ እና ንቁ ካድሬ አግጥሞኝ አያውቅም። ግራ ቀኙን በጥንቃቄ ካማተረ በኋላ ስልኩን ከኪሱ አወጣ።

ባትሪውን እየነቀለ፣

"መለስ በማዕድን ልማት ላይ የገፈው ሳያንስ ስድብ ቀረሽ ንግግር ለምን ይናገራል? ትብብርና የሠው ስብዕና ሳትነካ አስተሣሠብን ማራመድ አይቻልም እንዴ?" በማለት ጠየቀኝ።

በነገሩ ሳስብበት ቆየሁና፤

"ጉዳዩ ትንሽ አስገራሚ ነው። የአንድን መሪ ማንነት ለማወቅ በወረቀት ካሰፈረው ባሻገር ተግባር እንቅስቃሴውን መፈተሽ ያስፈልጋል።...አንተ ከመምጣትህ በፊት ከማዕድን ሚኒስትሩ አለማየሁ ተገኑ ጋር ነበርኩ። እሱም በጣም ተናዷል። የማዕድን ልማት ኪራይ ሰብሳቢነት ስለሆነ ትኩረት እንሰጠውም መባሉ አበሳጭቶታል። በተለይ የማዕድን ልማት እንደ ኢንዱስትሪ ያሉ ሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎችን ያቀጭጫል መባሉ በፍጹም አልተዋጠለትም" አልኩት።

ቁጥሮቪች ሐውልቱንና እኔን እያፈራረቀ እየተመለከተ፤

"የማእድን ዘርፍ ትኩረት የማይሰጠው ከሆነ ለምን የአራት ኪሎ ዩኒቨርሲቲ ጂኦሎጂ ዲፓርትመንት 75% በላይ የትግራይ ወጣቶች በመምህርና ተማሪነት እንዲቆጣጠሩት ተደረገ?...የዲፓርትመንቱ ስያሜ ተቀይሮ 'ዲፓርትመንት ኦፍ ትግራይ' ለምን የተባለ ይመስልሀል?..." በማለት መልሶ ጠየቀኝ።

"ወዲ ቁጥሪ ከጂኦሎጂ ዲፓርትመንት ወደ ማተማቲክስ የቀየርከው አንተ እንጂ እኔ አይደለሁም" በማለት ምላሽ ሰጠሁት። ይህም ሆኖ የቁጥሮቪችን ጥያቄ ወደኋላ ሔጄ ከማሠላሠል መመለስ አልቻልኩም።

ርግጥም ቁጥሮቪች እንዳለው የአራት ኪሎ ዩኒቨርሲቲ ጂኦሎጂ ዲፓርትመንት ተቀብሎ ከሚያስተምራቸው ተማሪዎች ውስጥ 90% የትግራይ ተወላጆች ናቸው። ከሌሎች የኢትዮጵያ ክፍሎች የሚመጡ ተማሪዎች ዲፓርትመንቱን መቀላቀል አይፈልጉም። በስህተት እሊያም የዲፓርትመንቱ ኮታ ሳይሞላ በግድ የተመደቡ ካሉ እንኳን ብዙም ሳይቆዩ ለመቀየር ጥረት ያደርጋሉ። ከሌሎች አካባቢ የሚመጡ ተማሪዎች ዲፓርትመንቱን የማይመርጡበት ዋነኛ ምክንያት ከምርቃት በኋላ በተማሩበት ሙያ ስራ የማግኘት እድላቸው በጣም ጠባብ ስለሆነ ነው። በተለይም የቤተሰባዊ መሰረታችን ከዝቅተኛ ኑሮ ለምንመጣ ሰዎች የተማረ ስራ አጥ መሆን የሚፈጥረው ጭንቀት ኮሌጅ ካልገባው በላይ ስለሚሆን በፍላጐት የሚገባው በጣም ጥቂቱ ነው።

በዛ ላይ ዲፓርትመንቱ የትግራይ ተወላጆች ነጻ መሬት እንደሆነ ስለሚታሰብ ምቾት አይሰጥም። የትምህርት ቋንቋው እንግሊዘኛ ይሁን እንጂ ተማሪዎች በክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጭ የሚናገሩት ትግርኛ ነው። የቡድን ጥናት የሚካሄደው በትግርኛ ነው። ከውስጥ ተሰርቆ የወጣ ፈተና እንኳን ተማሪዎች የሚያጠኑት ወደ ትግርኛ ከተቀየረ በኋላ ነው።

አንድ ጊዜ የቅርብ ጓደኛችን የሆነ ኮታ ለማሟላት የገባ ጓደኛችን ያጋጠመው ነገር ሁላችንንም ገርሞን ነበር። ይህ በአዲስ አበባ እንብርት ላይ ተወልዶ ያደገ ጨላጣ ጓደኛችን የትግራይ ልጆችን ጓደኛ ያደርጋል። በተለይም ከሁለተኛ አመት እስከ አራተኛ አመት ያሉ የትግራይ ልጆች ከሚጠረንፉት ውስጥ አስፋው ወሰን እና አስመላሽ የሚባሉ ተማሪዎች ጋር የጠበቀ ወዳጅነት ይፈጥራል። የተማሪው መናኸሪያ ከሆነው ይገባዋል ጠጅ ቤት ጀምሮ፣ ዘውዲቱ ሆቴልና ኢጀርሳ ባር የምሽት ቤታቸው ያደርጋል። የአራት ኪሎ ዲሲ (ደርቲ ኮርነር) ጉራ እያሉ ሳምንታዊ የፍትወት ጥማታቸውን እንዲወጡ ያደርጋል።

303

እናም ከእለታት በአንዱ ምሽት እነ አስመላሽን አስከሮ ዲሲ ከሴተኛ አዳሪዎቹ ጋር ካጣመደ በኋላ የዶርም ቁልፉቸውን ተቀብሎ ይመጣል። ወደ ማደሪያቸው ዘልቆ ከገባ በኋላ በትግርኛ የተጻፉትን ለቅሞ በመለየት በጠዋት ተነስቶ ፎቶ ኮፒ ያደርጋል። ያገኘበት ቦታ መልሶ ያስቀምጣል። በንጋታው ራቅ ያለ ቦታ ሄዶ የእንግሊዘኛ ትርጉሙን ያሰራል። ለካስ በትግርኛ የተጻፈው ወረቀት ከአንድ ሳምንት በኋላ በማጠቃለያ ፈተና ከሚወሰደው ኮርስ አንዱ ነበር። ፈተናውን የወሰዱ እለት የኮርሱ አስተማሪያቸው (እሱም የህወሓት አባል ነው) ፈቱን አጨማዶ ሲፈትናቸው ሁቀኛ ይመስል ነበር።

በነገራችን ላይ ጭንቀት (ቴንሽን) ፍራሽ እንጥፎ በተጉዘጎዘበት አራት ኪሎ ውስጥ ምንም አይነት መረበሽ የማይታይባቸው የትግራይ ተወላጅ ተማሪዎች ናቸው። (ቴንሽን:- T1፣ T2፣ T3 የሚል ስያሜ እንሰጠዋለን። በተለይ በፍሬሽማን "ሲድስ" (ዘመነስቃይ) የሚባለውን የፊዚክስ መጽሀፍ እናስታውሰበታለን)። ...ሌላው ቀርቶ መፈጠርን በሚያስጠላበት የፈተና እወጃ ቀናት (T3) እንኳን ዘና ብለው የሚታዩት እነሱ ናቸው። የተማሪ ላውንጅ ከጠዋት እስከ እኩለ ለሊት የቼዝ እና የጠረጴዛ ቴኒስ መጫወቻውን የሙጥኝ ብለው የሚይዙት እነሱ ናቸው። ቀናው

ላይብረሪ እና ማተማቲክስ ዲፓርትመንት ፊትለፊት ያለው መናፈሻ ከአሊ አብዶ ለ99 አመት ለሊዝ የገዙት ይመስል ከእነሱ ውጭ ሌላው አያዘወትርበትም። የአዲስ አበባ ልጆች ከሆኑ ቅምጥል (None cafe) ሴቶች ጋር እንደ ጅራሬ ተያይዘው የሚዞሩት እነሱ ናቸው። ቅምጥሎቹ ሴቶች እነዚህን የህወሓት አባላት የሆኑ ተማሪዎች የሚቀርቧቸው ከተሰረቀው ፈተና ፍርፋሪ እንዲደርሳቸው በማሰብ ነበር። የመንዲ ሴቶች እያፈራረቁ እና እያቀናን ...ነገ ከአንዱ ጋር ...በጠፉ ከሌላው ጋር በመውጣት የሚፈልጉትን ያገኛሉ። እነ አስመላሽም "ይሄንን ጥያቄ ለአገሊት እታሳያት። ላንቺ ብቻ ነው የሰጠሁሽ" በማለት ወሮታውን ይቀበላሉ። ዩኒቨርሲቲውን ሳይለቁ ዉለማ እና ጥጋጥግ ይዘው ወደ እንስሳነት ይቀየራሉ። የዩኒቨርሲቲውን ማህበረሰብ ከመጤፍ አይቆጥሩትም።

304

(የመጨረሻ አመት እያለን አንድ በጣም የምንወደው.አመለ ሸጋ ጓደኛ ነበረን። ትሁቱ ጓደኛችን None cafe ቢሆንም አዳርና ውሎው ከእኛ ጋር ነበር። እናም አንዷ ከእነ አስመላሽ አጠገብ የማትጠፋ ቅምጥል ግራ መቀመጫዋ እስኪንቀጠቀጥ ትወደዋለች። መቆሚያ መቀመጫ ታሳጣዋለች። ሁኔታው ከቁጥጥር ውጭ ሲወጣበት ለዶርምተሪ ውይይት ከፍት ያደርገዋል። በወቅቱ የምንወስዳቸው የሳይኮሎጂ ትምህርቶች ጠረጴዛ ላይ እየተቀመጡ ይበጠራሉ። ብዙዎቹ የአራት ኪሎ ቅምጥል ሴት ወንድሞቻችን ዩኒቨርሲቲ እስኪገቡ ድረስ የሚማሩት ሴቶች ብቻ አሊያም ወንዶች ብቻ የሚያስተምር ትምህርት ቤት (ናዝሬት ስኩል፣ ሴንጆሴፍ...) ስለሚሆን ቶሎ የመበላሸት እድል እንዳላቸው እንከራከራለን። በዛ ላይ ጠበቅ ካለው የቤተሰብ ቁጥጥር በአንድ ጊዜ ስለሚላቀቁ ታስሮ የተፈታ ጥጃ ባህሪ እንደሚኖራቸው እናነሳለን። ርግጥም ቶሎ ጫት፣ ሲጋራ፣ መጠጥ፣ ዳንኪራና ወሲብ የሚለምዱት እነሱ ናቸው። ጥንቢራቸውን እስከሚስቱ ጥምብዝ ብለው በመስከር ከዩኒቨርሲቲው ዘበኛ ጋር በየምሽቱ የሚጣሉት እነሱ ናቸው።

እናም አመለሸጋ ጓደኛችንን ትንፋሽ የነፈገችው ቅምጥል እህታችን እንስቶች ብቻ የሚማሩበት የናዝሬት ስኩል ተማሪ ስለሆነች እንደሆን መግባባት ላይ ደረስን። ቀርበ እንዲያናግራትም በድምፅ ብልጫ ወሰንን። እኔ እንድጨመርበት በጠየቀው መሰረት ፍቃደኛ ሆንኩኝ። በሊላ በኩል ደግሞ ፈራን። ጠብ ያለህ በዳቦ የሆኑት እነ አስመላሽ እና እስፋው ወሰን እንዳይተናኮሉት ሰጋን። አንዲት ምሽት ጠብቀው ቢታጠቁት ሽጉጥ እናቱን ቢበረቅሱት የማን ያለህ ልንል ነው። እኔ ደግሞ ከመጀመሪያውም ለህወሓት/ ኢህአዴግ መልካም ስሜት ስለነበረኝ

በቅርበት አውቃቸዋለሁ። በኢህአዴግ ደጋፊነት ተመልምዬ እንደምንቀሳቀስ ከፊል መረጃ አላቸው።

የሆነው ሆኖ እኔ እና ትሁት ጓደኛዬ ከተማሪ ዞር ብለን እንድናናግራት ቆረጥን። የእሱ ሰፈር የሆነው ሀያሁለት ማዞሪያ ቀጠርናት። ልጅት ከእኛ በፊት ቀድማን ደረሰች። አትኩሬ ስመለከታት እንደ ቀትር ፀሀይ ታበራለች። አይኖቿ እንደ ሴንጢ ይወጋሉ። ጓደኛዬን ዞር እያልኩ ስመለከተው ፍርሃት እና ደስታ ልቡን አሸብሮታል። የወትሮ ባህሪው ቢሆንም የበሰጠ አንገቱን ደፍቶ ዝም አለ። ባለጉዳዩ እኔ እስኪመስል ድረስ የቆጡን የባጡን እያወራሁ ስጫዋታ በር ከፈትኩኝ። ቀስ በቀስ ወደ ቀደመው ጉዳያችን ሰተት ብለን ገባን። ልጅት ሳትፈራ የልቧን አጫወተችን።

305

ወጋችን እንዲህ ነበር…

ሞልቶ በፈሰሰ የቤተሰብ ሀብት ውስጥ የምትኖረው ልጅት የምትማረው ስራ ፈልጋ ለመቀጠር ሳይሆን አባቷን ለማስደሰት ብቻ ነው። የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የዲግሪ ወረቀት ለአባቷ ለማሳየት። ቆብ ጭኖ የሚነሳው ፎቶዋ የአባቷ ንብረት የሆኑት ሁለት ግዙፍ ህንጻዎች ላይ በትልቁ እንዲለጠፉ። ተመርቆ መታየትን እንደ መጨረሻ ፍላጐት የወሰደችው እንስት ጂኦሎጂ ዲፓርትመንት የገባችበት አንዱ ምክንያት ይህ ነበር። እነ እስመላሽን የተዋወቀችው ዲፓርትመንቱን ከተቀላቀለች በኋላ ነበር። በሂደት ትውውቃቸው ስር እየሰደደ ሲሄድ የተሰረቀ ፈተና ይሰጧት ጀመር። እሷም ባገኘችው ፈተና ልክ አብሮ መውጣት ጀመረች። ከሁሉም የሚገርመው አንዱ የሰጣትን የተሰረቀ ፈተና ሌላ ጓደኛው እንዳያውቅ ያስጠነቅቃት ነበር። አንደኛው ከሌላው ልቆ ለመታየት የሚያደርገው ጥረት እስከ መጠፋፋት የሚደርስ እና የባላንጣነት ስሜት ያለበት ነው። እስመላሽ ስለ አሰፋው ወሰን ደደብነት፣ ራስ ወዳድነት እና የጥላቻ መወረር በየደቂቃው ካልተናገረ እረፍት አያገኝም። አሰፋው ወሰንም ስለ እስመላሽ " ወዲ ሸርሙጣነት"፣ ስግብግብነት እና ተንኮለኛነት ካልተናገረ የራሱን የበላይነት ያሳየ አይመስለውም። እነ እስመላሽ በራሳቸው ጉዳይ ላይ አንድ ቢመስሉም አንድ አይደሉም። ጫፍ የረገጠ ባላንጣዎች ናቸው። አንድ የሚሆኑት ሌላውን ሊያጠቁ ሲፈልጉ ብቻ ነው። ያኔ ተባብረው እስከ ህይወት ማጥፋት ሊሄዱ ይችላሉ። ልዩነታቸውን አምቀው የጋራ ጠላታቸው ላይ እንደ ጃርት ይረባረባሉ። አደጋ መጣብን ብለው ሲያስቡ በጋራ እሾህአቸውን ይቆማሉ። አደጋው ሳይመጣ አስቀድመው በማድባት እሾሃቸውን ያርከፈክፋሉ።

ትሁቱ ጓደኛዬ የቀረበለት ምርጫ ይሄ ነበር። የመጣው ይምጣ ብሎ በደም ሀረጋቸው የሁከሩትን ተጋፍጦና በነብሱ ፈርዶ መግባት አሊያም እርግፍ አድርጎ መተው። …እኛም ባልጠፉ ሴት ያውም የዩኒቨርሲቲ ተማሪ ሆነህ በማለት እንዲቀርበት ምክር ቢጤ ለገስን። …እናም ህይወቱን ለማቆየት ሳይጀምረው ተወው። ከካባ ማጥለቅና መነሳነስ ከቀኝ ወደ ግራ ማድረግ በኋላ የኢትዮጵያ አየር መንገድ የስራ ባልደረባ ሆነ። ምርጫው ትክክል ነበር።

ሲያልቅ አያምር እንዲሉ አንድ ጊዜ ዲሲ፣ ሌላ ጊዜ የዩኒቨርሲቲው ቅምጥል ሴቶችን ሲያግባብጡ የከረሙት እነ አስመላሽ የስራው አለም ላይ ብዙም መቆየት አልቻሉም። ያጋጠማቸው ሀመምና እርኩሠት የሚፈወስ አልሆነም። ወደው እና ፈቅደው በየጊዜው የሚቆፍሩት ጉድጓድ መቃብሪያቸው፣ በስርቆት የደረደሩት ግሬድም የእምቧይ ካብ ሆነ። እንደ ጠዋት ጤዛ ቀስ በቀስ መራገፍ ጀመሩ። የሰማዩ ጥሪ አስቀድሞ የደረሰው ለአስመላሽ ነበር። ስንቶቹ ቅምጥል ሴቶች ተከትለውት እንደሄዱ መረጃው የለኝም። ሁለቱ በኢትዮጵያ አየር መንገድ ሆስቴስ ተቀጥረው የመጨረሻ የሆነው ሙሉ የጤና ምርመራ ላይ እንደወደቁ አረጋግጫለሁ። ከአሜሪካ ጉዞ የተሰናከሉ እንዳሉ አውቃለሁ። የማታ ማታ የነበረው እንዳልነበር ሆነ።)

***

"እንደ አባትህ መቃብር ሀውልቱ ላይ ተተክለህ ቀረህ እኮ። የጠየኩህን እንኳን ሳትመልስልኝ" በማለት ቁጥሮቪች ሲናገረኝ በሰመመን ከሄድኩበት ተመለስኩ።

"ምን ነበር የጠየከኝ?" አልኩት። ርግጥም ያነሳልኝን ጥያቄ ዘንግቼው ነበር።

ከእግር ጥፍሬ እስከ ራስ ፀጉሬ እየተመለከተ፣

"እውነት ሳትሰማ ቀርተህ ነው?… የማላውቅህ ቢሆን አምንህ ነበር።… እንግዲያውስ እደግምልሀለሁ። …አንደኛ፡ የማእድን ዘርፍ ትኩረት የማይሰጠው ከሆነ ለምን የአራት ኪሎ ዩኒቨርሲቲ ጂኦሎጂ ዲፓርትመንት ከእስሩ ሰባቱ በመምህርና ተማሪነት እንዲቆጣጠሩት ተደረገ?… ሁለተኛ፡ የዲፓርትመንቱ ስያሜ በተማሪዎች 'ዲፓርትመንት እፍ ትግራይ' ለምን ተባለ?" በማለት እየተቆጣ ተናገረ። ትኩስ መረጃ ያገኘ ይመስል ውስጡ ተብከነከነ። የበለጠ

እንዲናደድ ስለፈለኩ ባለቤቱን የማላውቀው ብንኝ ተቀኘሁበት። ብለነው ብለነው የተውነውን ነገ ባኋ ትላንት ሠምቶ ታንቆ ሊሞት ነበር።

ከጥቂት ዝምታ በኋላ፣

"ወንድሜ! ቁጥሮቪች!... ስራ እንደምታገኝ እርግጠኛ ሆነህ እንደመማር ትልቅ ነገ የለም። ...እነዚህ ወጣቶች ገና ሳይመረቁ የት ስራ እንደተመደቡ ያውቃሉ። ከረምት በመጣ ቁጥር በትግራይ በሚገኙት የትዕምት ኩባንያ አካል የሆኑት ኢዛና፣ መሰቦ ሲምንቶ ፋብሪካ፣ ሳባ እምነበረድ፣ ብሩክ ኬሚካል፣ ሰገን ኮንስትራክሽን፣ ሱር ኮንስትራክሽን፣ መስከረም ኢንቨስትመንት የመሳሰሉ ድርጅቶች ደሞዝ እየከፈሉ የስራ ላይ ስልጠና ይወስዳሉ። ትምህርታቸውን ጨርሰው ሲመረቁ የከረምት ልምምድ ወዳደረጉበት ኩባንያ በመሔድ ከሌላው የዲግሪ ተመራቂ ሁለት እጥፍ ይቀጠራሉ።...ይሔን ደግሞ አንተም ሆንክ እኔ የምናውቀው ነው። ለምን እንደምትጠይቀኝ አይገባኝም እርጅቶ የቀረፈደ ወሬ ፊት ለፊት አምጥተህ መነታረክ ትወዳለህ።" በማለት ምላሽ ሰጠሁት።

ቁጥሮቪች አጨንቁሮ እየተመለከተኝ፣

"በግራ በኩል የማእድን ልማት ኪራይ ሰብሳቢነት መንገድ ስለሆነ አፋችሁን ዝጉ ይባላል፡ በቀኝ በኩል የትግራይን የኢንዱስትሪ ልማት በበላይነት እንዲመራው የተደረገው ኢፈርት ከተሰማራባቸው አምስት ቁልፍ ዘርፎች አንዱ የማእድን ልማት የኢኮኖሚ ዘርፍ ነው። ይህ ዘርፍ እንዲመራ የተደረገው ደግሞ ቁልፍ የህወሓት ሰው በሆነው እና ዛሬ የአዳማን ስልጠና በበላይነት በሚመራው ቴዎድሮስ ሀጐስ ነው። በግልጽ እንደሚታየው ደግሞ የኢፈርት የማእድን ኢኮኖሚ ዘርፍ ከተቋቋመ ከ1985 ዓ.ም. ወዲህ በኢኮኖሚው ውስጥ የሚኖራቸው ተሳትፎ በከፍተኛ ሁኔታ እየተስፋፋ ነው። እነዚህ ኩባንያዎች ከሀገር ቤት አልፈው ከአፍሪካ ሀገሮች እና ቻይና ጋ ሽርከና በመፍጠር የአገሪቷን ማእድን ከእላሙዲን ጋር በመሆን ሙሉ በሙሉ እየተቆጣጠሩት ነው" በማለት ምላሽ ሰጠኝ።

ርግጥም ቁጥሮቪች እንዳለው ትዕምት በመጀመሪያ ሰሞን የተሰማራባቸው ስድስት ቁልፍ የኢኮኖሚ ዘርፎች ነበሩ። እነሱም የኢንዱስትሪ (በአባዲ ዘሙ የሚመራ)፣... የማእድን ኢኮኖሚ ዘርፍ (በቴዎድሮስ ሀጐስ የሚመራ)፣ ...የፋይናንስ እና ንግድ (በስብሀት ነጋ የሚመራ)፣

...ኮንስትራክሽን እና ትራንስፖርት (በአርከበ እቁባይ የሚመራ)፣ ...ሚካናይዜሽን እርሻ (በፀጋዬ ብሥያለው የሚመራ)፣ ...እና የኢንፎርሜሽን ዘረፍ (በአዜብ መስፍን እና ብርሀነ ማእረት የሚመሩ) ናቸው። ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደጉ፣ እየበዙ እና እየተጠናከሩ የመጡት የህወሓት ኩባንያዎች የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ሙሉ በሙሉ በመቆጣጠር የሞኖፖሊ ስርአት በመገንባት ላይ ይገኛሉ። ቁጥሮቹ እንዳለው የትግራይ ክልልን የኢንዱስትሪ ስትራቴጂ እንዲመራ በመንግስት ረጂ የተወሰነው ኤፈርት ነው።

(አቶ መለስ ካዘጋጀው የህወሓት ኢምፓወርመንት ፕላን የሚቀዳው የትግራይ አምስት አመት ትራንስፎርሜሽን እቅድ የሚከተለውን ይላል። ማስታወሻ: ትራንስፎርሜሽን እቅዱ የተጻፈው በትግርኛ እና እንግሊዘኛ ብቻ በመሆኑ የባእድ ቋንቋውን እንደወረደ ተጠቅሜበታለሁ። እናም ድርጅቱ በትግራይ ፕላን እና ፋይናንስ ቢሮ ማህፀን ውስጥ ገብቶ የሚከተለውን ይለናል፣

Five years (2011 -2015) Regional GTP: Tigray Region plan and Finance Bureau፣

308

"By the end of the next five years, industrial developement is expected to reach at the stage which it can take the leading role of overall development of the region. The Industrial sector has to be export oriented, support to overcome shortage of foreign currency and should activate the rapid transfer of technology. Moreover, industries play a significant role in minimzing the shortage of foreign currency by producing imported goods and services in our country, special focus will be given to expand industries in a better way than of the last five years. The EFFORT companies are expected to play a significant role in strengthening the industrial sector of the region.

Tigray Region plan and Finance Bureau: page 54)

***

ቁጥሮቪች የተቆጣ ሰውነቱን እያወራጨ፣

"የሚገርመው እኮ ማእድን ልማት ላይ የሚሳተፉት እንደ ኢዛና ያሉ የትዕምት ኩባንያዎች በትግራይ ውስጥ ሌላ ባለሀብት መጥቶ ማእድን እንዲያለማ አይፈቅዱም። እነ ኢዛና መድረስ ያልቻሉበት ቦታዎች መሳተፍ የሚችሉት የትግራይ ተወላጅ የሆኑ ባለሀብቶች ብቻ ናቸው ...በዚህም ምክንያት በትግራይ ምን ያህል ማእድን በተለይም ወርቅ ተመረተ የሚለውን ማእድን ሚኒስቴርም ሆነ ብሔራዊ ባንክ የሚያውቀው ነገር የለም..." በማለት ሲናገር አቋርጬው፣

"ቁጥሮቪች ምን አለ የማላውቀውን ብትነግረኝ?...አሁንስ የመረጃ ቋትህ ደረቀ መሰለኝ" አልኩት።

ቀኑን ሙሉ ሲከነክነኝ የነበረው ለመጠየቅ፣

"እረስተኸው ካልሆነ በስተቀር መለስ በ1993 ዓ.ም. በጻፈው የአብዮታዊ ዴሞክራሲ የልማት መስመሮችን በሚያመላክተው መጽሀፍ ላይ ማእድን ቢኖረን እንኳን እናወጣውም፣ ደሀ እንሆናለን ብሎ አቅጬን ነግሮን ነበር። ዛሬም የደገመው ተመሳሳይ ቃል ነው። እንደውም ከኪራይ ሰብሳቢነት ጋር አያይዞ የደች በሽታ (Dutch disease) የሚል ቃል ስልጠናውን በሰጠ ጊዜ እንደ አቡነ ዘበሰማያናት ሲደጋግመው ነበር። ዛሬም እስኪቻለቸን ተናግሮታል" አልኩት።

ቁጥሮቪች ባለመስማማት አንገቱን እየነቀነቀ፣

"ማንጥል አስተሳሰብ ነው" በማለት መልስ ሰጠኝ።

"እንዴት?"

"የደች በሽታ ጽንሰ ሀሳብ በተፈጥሮ ሀብት እና ግብርና (ማኑፋክቸሪንግ) መካከል ስለሚኖረው ተዛምዶ ብቻ አያነሳም። ሌላም ገጽታ አለው" አለኝ።

ለመስማት ጓግቼ፣

"ምንድነው ሌላው ገጽታ? ...ለመቃወም ብለህ የማትቆፍረው ጉድጓድ የለህም።"

"አቦ! ይህን ተራ ነገር ለማወቅ መቆፈር አያስፈልግህም። ጢና ጢኖ Wikipedia ማህበ! አሊያም ኢንተርኔት መነካካት በቂህ ነው። …ችግሩ ሰውየው በዙሪያው የሰበሰበን ሰዎች አማን ነን ? …እናነባለን ወይ? …ዘመናዊ ቴክኖሎጂ እንጠቀማለን ወይ? የሚለው ይመስለኛል" አለኝ።

ያለማቋረጥ ሳቀ። ተናደድኩኝ። በነገራችን ላይ ቁጥሮቪች የወጣለት አንባቢ ነው። መቼም ቢሆን የሆነ ነገር ሲናገር ካነበባቸው መጽሀፍት ውስጥ አንዱን መዞ እንደሚሆን አውቃለሁ። ከሆነ ጫት ይዞ ከተቀመጠ ከማንበብ ውጭ የሚታየው ነገር የለም። በተለይ በምርቃና ሰአት መጽሀፍ ያነባል ሳይሆን ይበላል ቢባል የሚያንሰበት አይደለም። ለእሱ በአንድ ጉዳይ ላይ ጥናት ለማካሄድ ፍንጭ መስጠት ብቻ በቂ ነው። በጥልቀት ቆፍሮ ዝርዝር ነገር ይዞ ይመጣል። ማትማቲክስ መማሩ ሳይጠቅመው አልቀረም። ሁልጊዜ " ማትማቲክስ በራሱ የመጨረሻ ውጤት አይደለም፣ ሌሎች ነገሮች ለማወቅ መሳሪያ ነው" የሚል እምነት አለው። በተለይ እንደ ኢኮኖሚክስ ያሉ ትምህርቶችን ከዘርፉ ሙያተኞች ባልተናነሰ እውቀት እንዲያዳብርለት ያደረገው ሂሳብን እንደ መሳሪያ በመጠቀሙ ነው። ቁጥሮቪች የኢኮኖሚክስ ትንተና የሒሳብ ስሌት ዘዴን መጠቀም ባይጀምር ኖሮ ተገትሮ ይቀር እንደነበር እምነቱ ነው።

310

መናደዴ ታውቀው መሰለኝ ይበልጥ እየሳቀ፣

"Obbo! የኢዩብ ትግስትህ የት ጠፋ?…ደግሞ እንደልማድህ ሄደህ ኢኮኖሚስ አጠናለሁ ብለህ ዩኒቨርሲቲ እንዳትመዘገብ …ታዋቂው የፈረንሳይ የኢኮኖሚ ፈላስፋ አንቱዋን ኩርኖ ሁሉንም ጨርሶታል" አለኝ።

መቼም አንድ ነገር ሲያወራ የኢኮኖሚክስ አስተሳሰብ የወለዱትን ፈላስፎች በስም ካልጠራ አይሆንለትም። እነ አርስቶትል፣ የወረቀት ብር የፈለሰፈው እና ኢንፍሌሽን ያስተዋወቀው ፈረንሳዊው ጆን ሎ፣ …የሰነ ኢኮኖሚ እና ሰነ ማእድን ተመራማሪው ዴቪድ ሪካርዶ…፣ የካፒታል ደራሲው ካርል ማርክስ፣ …'የታሪክ መጨረሻ እና የመጨረሻው ሰው' ደራሲ ፍራንሲስ ፋኩያማን የመሳሰሉ ምሁራን ከአንደበቱ አይጠፉም። በተለይም ለመጀመሪያ ጊዜ የሒሳብ ቀመሮችን ለኢኮኖሚክስ ምርምር ያቀለውን ሳይንቲስት አንትዋን አውግስቲን ኩርኖ እንደ መጽሀፍ

ቅዱስ ጥቅስ ሳይጠቅሰው ማለፍ አይፈልግም። በተለይ የትምህርት ቤት ደጃፍ ያልረገጡትን እነ ታጋይ ካሚል አህመድ ያሉ ጠርናፊዎቻችንን ከጨዋታ ውጭ ለማድረግ ሲፈልግ "ፖለቲካል ኢኮኖሚን ለመረዳትና ለመተንተን ባዙቃ ትከሻ ላይ አቁሞ እንደመተኮስ ቀላል አይደለም። እነ ኩርኖ ያሉ ኢኮኖሚስቶች የተጠቀሙትን የፎርሙላ ሀ ሁ ማወቅ ይጠይቃል" ይላቸው ነበር። እኔንም በእነ ታጋይ ካሚል መንገድ የመጣብኝ መሰለኝ።

ሆኖም እጅ ላለመስጠት የእጅ ጣቴን እየቆጠርኩ፣

"ኢኮኖሚክስም ቢሆን ከአምስት በላይ ኮርስ ወስጃለሁ። ኢትዮጵያን ኢኮኖሚ (Eco 101, Eco 102)፣ ማክሮ ኢኮኖሚ፣ ማይክሮ አንድ፣ ማይክሮ ሁለት፣ ዴቨሎፕመንታል ኢኮኖሚ ...ወረቀት አለኝ ብሎ ለመመጻደቅ ካልሆነ በስተቀር ሀገሪቷ ከደረሰችበት እድገት አንጻር በቂ ነው። እነብብን የምትሉትስ ቢሆን ከመመጻደቅ ውጭ ምን ያመጣችሁት ነገር አለ?" በማለት የአፀፋ ምላሽ ሰጠሁት።

"እረ ከበቂ በላይ ነው። ማእከላዊነት ለጠበቀበት ስርአት ከበቂም በላይ ነው" አለኝ።

"መፈላሰፉን ተውና የደች በሽታ ሌላ ገጽታ የምትለውን ንገረኝ" አልኩት።

311

ምንም ሳይናገር በእጁ የያዘውን ቦርሳ ከፈተ። ከአሰር ገጽ ያልበለጠ ወረቀት አወጣ። በቀይ ማርከር የሚከተለውን ቀብቶ አቀበለኝ፣

In economics, the Dutch disease is the apparent causal relationship between the increase in the economic development of a specific sector (for example natural resources) and a decline in other sectors (like the manufacturing sector or agriculture). The putative mechanism is that as revenues increase in the growing sector (or inflows of foreign aid), the given nation's currency becomes stronger (appreciates) compared to currencies of other nations. This results in the nation's other exports becoming more expensive for other

countries to buy, and imports becoming cheaper, making those sectors less competitive.

While it most often refers to natural resource discovery, it can also refer to "any development that results in a large inflow of foreign currency, including a sharp surge in natural resource prices, foreign assistance, and foreign direct investment."

It is usually difficult to be certain that a country has Dutch disease because it is difficult to prove the relationship between an increase in natural resource revenues, the real-exchange rate, and a decline in the lagging sector.

312

በተቀመጥኩበት ሙጥጥ አድርጌ አነበብኩት፡፡ በጣም ስለመሰጠኝ በድጋሚ ሔድኩበት፡፡ የጽሁፉ ጽንሰ ሀሳብ የዳች በሽታ በማእድን ላይ ብቻ የተንጠለጠለ እንዳልሆነ የሚያመላክት ነው፡፡ የአንድን ሀገር የውጭ ምንዛሪ ችግር ውስጥ ሊከቱ የሚችሉ እንቅስቃሴዎችን በሙሉ ያጠቃልላል፡፡ ለአብነት' ያህል የውጭ ምንዛሪ በውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት (FDI) እና የውጭ እርዳታ መልኩ ወደ ሀገር ውስጥ ከገባ ችግሩ ሊከሰት ይችላል፡፡

አንብቤ ስጨርስ፣
"አሁን እያልከኝ ያለኸው ምን እንደሆነ ታውቃለህ?" በማለት ጠየኩት፡፡ ምንም ሳይናገር በጥያቄ ምልከት ይመለከተኝ ጀመር፡፡

"ኢትዮጵያ በደች በሽታ ከተጠቃች ቆይታለች እያልከኝ ነው፡፡ ምክንያቱም ከየትኛውም ዘመናት በላይ ከፍተኛ የውጭ እርዳታ እየፈሰሰ ያለው በእኛ ጊዜ ነው" አልኩት፡፡

"Obbo! ተው እንጂ፣ እየተዋወቅን።... መቼስ ድምጿ መጀመሪያ ጣራ ላይ ወጣች፣ ቀጥሎ ከጣሪያ ወደ ምድር አየች፣ ቀጥሎ... እያልኩ የማስረዳህ ሰው አትመስለኝም?" አለኝ።

"ታዲያ መፍትሔው ምንድነው?" በማለት ጠየኩት።

"የተገኘውን የውጭ ምንዛሬና እርዳታ ተመልሶ በህገወጥ መልኩ ወደ ውጭ እንዲወጣ ይደረጋል እንዳልልህ ለቀባሪው ማርዳት ይሆንብኛል። መቼም ከኢትዮጵያ በየአመቱ በህገወጥ መንገድ የሚወጣውን የገንዘብ መጠን ሳትሰማ አትቀርም። ...መፍትሄው ደህን የበሰጠ ደሀ በማድረግና ሀገሪቱን ከድህነት አዙሪት እንዳትላቀቅ ተግቶ የሚሰራን ድርጅት ዞር ማድረግ እንዳልልህ ደግሞ አንተንና እኔን የመሳሰሉ አብዩታዊ ዲሞክራቶች ስራ ማሳጣት ይሆንብኛል" አለኝ።

ከልቤ ባልሆን እነጋገር፣

"ከአፍሪካ ሀገሮች በተለየ ሁኔታ ከኢትዮጵያ ገንዘብ ወደ ውጭ ሀገር የሚሰደድ አይመስለኝም። እንደምታውቀው የፋይናንስ ስርአታችን በጣም ጥብቅና የማያላውስ ነው። የንግድና ፋይናንስ ስርአቱን በአይነ ቁራኛ እንዲከታተሉ የተመደቡት ደግሞ ኢህአዴግ አለኝ የሚላቸው ካድሬዎች ናቸው" በማለት ተቃወምኩት።

313

"ይህን ውሀ የማይቋጥር መከራከሪያ ወደ ጉን ተወውና አለም አቀፍ ተቋማት የሚያወጡትን ሪፖርት ተከታተል ...ምንአልባት አንድ ቀን የታሰርከበት እግረ ሙቅ ሲወልቅልህ 'እሪ በይ ሀገሬ!፣ እሪ በይ ኢትዮጵያ የሚል ጽሁፍ ጽፈህ ታስነብበናለህ። እኔ እንኳን የተጻፈ ማንበብ እንጂ መከተብ እጣ ፋንታዬ እንዳልሆን ታውቃለህ" አለኝ።

ትንሽ ሳሰላስል ከቆየሁ በኋላ፣

"ወዲ ቀጥረ! እውነቱን ንገረኝ ካልክ የድርጅቱ አካሄድ አልመቸኝ ብሏል። አድሮ ቃሪያ እየሆነብኝ ሔዷል። የዛሬ ሶስት አመት የጻፈውን ገልብጦ በተቃራኒው ይጽፋል። የዛሬ ሶስት አመት ዋነኛ አቅጣጫችን ይሄ ነው ብሎ ነግሮን እኛም እንደ በቀቀን ለፍልፈን ስናበቃ ዛሬ ሙሉ ለሙሉ

ይዳረጋል። ...መያዣ መጨበጫ የሌለው ሰዉ ሆኖብናል" በማለት ነገርኩት። እሱ ጋር ለማግባቱ በፊት ከማዕድን ሚኒስትሩ አለማየሁ ተገኑ ጋር የነበረንን ቆይታ በዝርዝር ለማወቅ ችሏት።

በጣምና ሲያዳምጠኝ ቆይቶ፣

'አንድ ድርጅት እና አባላቱ አፈጣጠራቸው በጭካኔ እና አጦት ላይ የተመሰረተ ከሆነ ስለት ያጣ ስግብግብ ይሆናሉ። ስግብግብነቱ እያደር ምቀኝነት እና ቅናት ይወልዳል። ያለው ሃብት ለሁሉም የሚበቃ ቢሆን እንኳን እንደ ህጻን 'እኔ ብቻ' ስለሚሉ መጨረሻው መጠፋፋት ጣጡ አይቀርም። ...ቅዱስ መጽሀፉ እንደሚገልጠው ቃኤል አቤልን የገደለው ሁለቱ ወንድማማቾች የሚበሉት አጥተው አይደለም። ነገር ግን በቃኤል ልቦና ውስጥ ባደረበት ቅናት እና ምቀኝነት ምክንያት ወንድሙን ገደለ። ኢቶ መለስም ሆነ ህወሓት ከበታችነት በመነጨ ቅናት እና ምቀኝነት ወጥተው በአኩልነት መንፈስ መንቀሳቀስ ካልቻሉ የመጨረሻው ውጤት መገዳደል ሊሆን ይችላል። በስምንተኛው ሺህ ደግሞ ገዳዩ አቤል እንጂ ቃዩል አይሆንም' በማለት ተናገረ።

314

አነጋገሩ ስለመሰጠኝ፣

"ወዲ ቁጥሪ! ለምን በህወሓቶች ብቻ እናላክካለን። እነሱ የበታችነት ስሜት በወለደው ቅናት እና ምቀኝነት እንደሚሰቃዩ ሐገር ያወቀው ፀሀይ የሞቀው ነው። አንተም በአንድ ወቅት ባደረከው ዝርዝር ጥናት ይህንኑ ማረጋገጥህን አሳውቀሀል። ከዛ ይልቅ አብረናቸው የምንሰራ ሰዎች እውነቱን ከመግለጥ ይልቅ አድርባይነት ተጠናውቶን..." ከማለቴ አቋረጠኝ፣

"እኛም ብንሆን የማህበረሰባችን ውጤት መሆናችንን መዘንጋት የለብህም። ማህበረሰባችን ደግሞ የጭቆና ቀንበር መሸከም የሚከብደው አይደለም። እየተበዘበዘ እና ራቁቱን እየቀረ ትንፍሽ አይልም። 'የባሰ አታምጣ!' በሚል አመለካከት ተውጥሯል።... ዊኒስተን ቸርቺል እንደሚለው ጥሩ ሰዎች እጃቸውን አጣጥፈው እስኪተቀመጡ ድረስ መጥፎ ሰዎች ማሸነፋቸው አይቀርም ። ...በዛ ላይ ማህበረሰባችን ውስጥ መተማመን እየጠፋ ነው። መተማመን ከሌለ ደግሞ በጋራ መቆም አይቻልም። በጥርጣሬ የተሞላ ማህበረሰብ ተሸክመን ለውጥ እናምጣ ማለት አይቻልም። በኢትዮጵያ ህዝብ ዘንድ የመገለል ስሜት እየፈጠረው ያለ አዲስ ማንነት አለ። የህዝብ ሀይል እየመከነ ያለው በዚህ ምክንያት ነው" በማለት ተናገረ።

"አዲስ ማንነት?... መቼም የማታመጣው ጉድ የለህም። ደሞ ብለህ ብለህ መላ አዲስ ማንነት ይፈጥራል ልትል ይሆናል?" በማለት ጠየኩት።

"ድብን አድርጎ! ...ጭቆናውን እየበዛ ሲሔድ፣ ብዝበዛው ለከት ሲያመጣ፣ ማንነት ሲኖር ...በተለይ በዘር ላይ የተመረኮዘ ግፍና መከራ ሲበዛ እየተሠባሠበ የሚሔድ አዲስ ማንነት መፈጠሩ አይቀርም" አለኝ። በተልዕኮ የአመራር ስልጠና ጥናት እየሰራ ያለው በዚህ ዙሪያ የሚያጠነጥን እንደሆነ ጨምሮ ነገረኝ።

አጋጣሚ አንድ፣

ከሖለታት በአንዱ ቀን ከማደሪያችን ጎረቤት በሆነ አዳራሽ ውስጥ የተመደቡ ከአማራ ክልል የመጡ ባለስልጣናትና ካድሬዎች ተሰብስበው ካርታ ይጫወታሉ። ጨዋታው ሲደራ ከ ቁጥሮቪች ተቀላቀልናቸው። በጥቂት ሰአታት ውስጥ ቁጥሮቪች ተበልቶ ኪሱ ባዶ መሆን ሲጀም "ምድረ አማራ! ትላንት በግላጭ የበዘበዝሽኝ አንሶ ዛሬም በቁማር ልትበዘብዥኝ?" በማለት ብሎ ተናገረ። እኔን ጨምሮ ሁሉም "አማሮች" ከት ብለው ሳቁ። ጨዋታውን በሳቅና ፈገግ ቀጠሉ። አሁንም ትንሽ ቆይቶ አንዱ "ውሎዬ" የቁጥሮቪችን ኪስ ማናጠብ ጀመረ። ቁጥሮቪች "ወሎዬነትን" ጠቅሶ ተረበው። ሠውየው ከመናደዱ የተነሳ ጨዋታውን ለደቂቃዎች አቋረጠ። አላርፍ ያለች ጣት ሆነና ቁጥሮቪች "ጎንደሬ!" "ጎጃሜ!" "መንዜ" እያለ መተረብ ሲጀም እያንዳንዱ እየተነሳ "ዘራፍ!"፣ ማለት ጀመረ። ጎጃሜው ለመደባደብ ሽሚዙን ሠበሠበ። ጎንደሬው እንገቱን አንቀው። መንዜው አዳራሹ እስኪ.ጠበው ተንቆራጠጠ።

315

ሁኔታው አላምረኝ ሲል ቁጥሮቪችን ጠቅሼው እንድንወጣ ነገርኩት። እሱም ገብቶታል መሰለኝ ትንሽ ካሠላሠለ በኋላ "ከጨቋኟ አማራ ልጆች..." ብሎ ሳይጨርስ ሁሉም እኩል ብድ አሉ። ካርታቸውን መሬት ላይ ጥለው ከበቡት። ...ጎንደሬው ካድሬ "ቁጥሮቪች! ወንድ ከሆንክ ጨርሳት?" በማለት አፈጠጠበት። ...ሌሎችም ተራ በተራ ዛቱበት። አደራሹን ለቆ እንዲወጣ አስጠነቀቁት። ሁኔታዎች ወደ መጥፎ እንዳያመሩ እጁን ይዤው ወጣሁ። ቁጥሮቪች እንደ በግ እየተንተተ ግን ደግሞ እየሳቀ አደራሹን ለቆ ወጣ።

ለካስ ቆጥሮቪች ጥናታዊ ጽሁፋን እየሠራ ነበር።

አጋጣሚ ሁለት፤

"ማንነት ሲለወጥ!"

ከጋዜጠኛ እና መምህርት ርዕዮት አለሙ ጋር በአሌክሳንደሪያ ቨርጂኒያ በሚገኝ አንድ ካፌ እየተጫዋወትን ነው። የወጋችን አምብርት ደግሞ የእስር ቤቷ አከራሞት ሆኗል። እንደ እውነቱ ከሆነ ርዕዩት በማእከላዊ እና ቃሊቲ እስር ቤት ያሳለፈችው መከራ ተወርቶ የሚያልቅ አይደለም። ዘመኑ ሲደርስ ለኩራዙ በተያዘው ቦታ ፋንታ በሙዚየም ይቀመጣል። ለእስቱ መታሰቢያም በየአመቱ ሻማ የሚበራበት ይሆናል። ለአመታት የቆየችበት የእስር ቤት ክፍል እና መኝታ በቁጥር እየተጠቀሰ የሚጐበኝ ይሆናል።

በአሌክሳንድሪያ ከርዕዩት ጋር እያነሳን በምንጥለው ጨዋታ መሀል የአቶ መለስ ስም ተነሳ። የሰውየውን ባህሪያት አንድ በአንድ እያነሳን ተጫወትን። በአጋጣሚ እሬ ላይ የመጣውን አቶ መለስ ለጋዜጠኞች የሚሰጠውን ጋዜጣዊ መግለጫ አነሳሁ። በተለይም ከጋዜጠኞች ስለ መብራት መቆራረጥና መጥፋት ተጠይቆ "ከኪሱ አውጥቶ" የሰጠውን አስገራሚ ምላሽ ነገርኳት።

316

ርዕዩት ከት ብላ ሳቀች።

ከዝች አይናፋር ሳቅ በስተጀርባ መቀርቀሪያ የሚያካክል ገጠመኝ እንዳለ ስለሚገባኝ በቀላሉ ልተዋት አልፈለኩም። በቅርብ እንዳየሁት ከሆነ ርዕዩት ነጭ ወረቀት ነበረች። ሀገሯን ሙያዋን የምትወድ፤ ሰዎችን በሰውነታቸው ብቻ የምትቀርብ ነበረች። ለዚህም ይመስላል ለፍቅረኝነት ጓደኛ ስትመርጥ እንኳን እጥንት እና ደም ያልተመለከተችው።

ዛሬ ይህች ብርቅዬ እንስት በትላንት መንፈሷ ውስጥ አይደለችም። በማእከላዊ እና ቃሊቲ እስር ቤት የተመለከተችው ከትግራይ የመጡ እሳሪዎቿ ውሸት፣ ንቀት እና ጥላቻ በቀይ እስኪረብቶ አበላሽተውታል። በወህኒ ቤቶቹ የበላይ ሀላፊዎች ከላይ እስከ ታች የትግራይ ልጆች መሆናቸው፣ የአሳሪዎቿ ቋንቋ ትግርኛ ብቻ መሆኑ "እውን የት ነው ያለሁት?…መቀሌ አይደለሁምን?" የሚል ጥያቄ እንድታነሳ አድርጓታል። የአሳሪዎቿ የኩራት ምንጭ ዜጐችን አሰቃይቶ መግዛት እና እርስ

በራስ ማጋጨት መሆኑን መመልከቷ መሸከም የማትችለው የመጠቃት ስሜት እንዲሰማ... አድርጓል።

***

የማዕድን ሚኒስትሩ አለማየሁ ተገኑ የኮምፒዩተሩን ቁልፍ እየነካካ ጥናታዊ ጽሁፍ ማቅረብ ጀመረ። እኔም ማስታወሻዬን አውጥቼ የሚናገረውን ቃል በቃል መከተብ ጀመርኩ።

"ክብር!" ሚኒስትሩ እንዲህ አለ፦

"...የማዕድን ስራ እንደ ሁሉም ኪራይ የማሰባሰብ ስራ በመሰረታዊ የልማት አቅጣጫችን ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ይኖረዋል። ሁላችሁም እንደምታውቁት የማዕድን ስራ ምንም ሳይሰራና ሳይደከም የሚመጣ ሀብት ነው። እኛ እንዳስቀመጥነው የልማት አቅጣጫ ሁሉም በየደረጃው ተጠቃሚ የሚያደርግ አይደለም። የማዕድን ልማት ዋነኛ የልማት አቅማችንን በመሠባበር ከኪራይ የመከፈል ባህሪ እንዲጎለብት ያደርጋል። ይህም ለሙስናና ለተለያዩ ፖለቲካዊ ችግሮች ያጋልጠናል። የምርት አቅምንም ያሽመደምዳል።... በአጠቃላይ መልኩ የማዕድን ልማት ልናመጣው ለምንፈልገው ቀጣይና ፈጣን ኢኮኖሚና ቴክኖሎጂካዊ ልማት መሠረት ሊሆን አይችልም። አይገባምም!!" በማለት ተናገረ።

ከልቤ ደነገጥኩ...

የማዕድን ሚኒስትሩ የላስቲክ ውሀውን ተጎንጭቶ ንግግሩን ቀጠለ፣

"ለሁላችሁም ግልጽ እንደሆነ የልማታችን መሠረት ግብርናና በሱ ላይ ተመስርቶ የሚመጣው እንዱስትሪ ጉልበትንና መሬትን ጥቅም ላይ ማዋል ነው። ለአገራችን ዘላቂ እድገት የሚኖረን አቅጣጫ በአርሶ አደር ማሳ ላይ ያተኮረ ልማት እንጂ ሥራ የመስኖ ስራዎችን በመስራት አሊያም ማዕድን በማፈላለግ አይደለም።... 'ሳንንጠራራ የምናወርደው ፍሬ ምን ማለት እንደሆነ እናውቃለን?" በማለት ተሠብሳቢውን በጥያቄ ምልክት ተመለከተ። አስከትሎም አቶ መለስ የጻፈውንና በመጋቢት/ሚያዚያ የፓርቲው ልሳን የሆነችው አዲስ ራዕይ ላይ ዘግየት ብላ የሠፈረችውን ሠነድ መዞ አወጣ።

እንዲህ በማለት ማንበብ ጀመረ፣

17

"ከፍተኛ ፍሬ የዛፍ ፍሬ ከታች እስከላይ የበሰለ ፍሬ ይዞ ሲገኝ አወራረዱን ማወቅ ያስፈልጋል። በመጀመሪያ መሰብሰብ ያለባቸው ፍሬዎች መሬት ላይ ሆነን ሳንጠራራ በቀላሉ ልንሰበስባቸው የምንችል ፍሬዎች መሆን ይገባቸዋል። እነዚህን ፍሬዎች በቀላሉ ከሰበሰብን በኋላ ከመሬት ራቅ ብሎ የበሰሉትን ፍሬዎች ወይ ዛፍ ላይ በአንድ ወይም በሌላ መንገድ ወጥተን ወደ መሰብሰብ ልንሻገር እንችላለን። ይህን አድካሚ ጊዜ የሚጠይቅ ስራ የምንሰራው በቀላሉ ሊለቀም የሚችለውን ፍሬ ለቅመን ከጨረስን በኋላ መሆን ይገባዋል።...

"የግብርና ቴክኖሎጂን በተመሳሳይ መልኩ ልናየው እንችላለን። የአግሮኖሚ ቴክኖሎጂያችንን በላቀ ደረጃ አለም የደረሰበት የምርታማነት ደረጃ ላይ የማንደርስበት ምክንያት የለም። የሚከፈለውን ዋጋ ሁሉ ከፍለን በሂደት በመስኖ ሊለማ የሚችለውን መሬት ሁሉ በመስኖ አልምተን በአመት ሶስቴ ከፍተኛ ምርት የማናገኝበት ምክንያት የለም። ይሁንና እዚህ ላይ ለመድረስ ከፍተኛ ጊዜ፣ ካፒታልና በላቀ ደረጃ የሰለጠነ የሰው ሀይል ይጠይቀናል። ከመሬት ራቅ ብሎ እንደሚገኝ የበሰለ ፍሬ ሊወሰድ ይችላል። ይህንን ፍሬ በመልቀም ስራ ላይ የምናተኩረው ሳንጠራራ ልንለቅመው የምንችለውን ፍሬ ለቅመን ከጨረስን በኋላ መሆን ይኖርበታል። መጀመሪያ የምንለቅመው ቴክኖሎጂ ከፍተኛ ካፒታል፣ ጊዜና በላቀ ደረጃ የሰለጠነ የሰው ሀይልየማይጠቀንን ቴክኖሊጂ መሆን አለበት።

18

"የተሻሻለ አግሮኖሚ ስንል አለም የደረሰበት የላቀውን ሳይሆን የኛ መሀይም አርሶ አደር ተግባራዊ ያደረገውን ስለሆነ በተግባር እኛም እሁኑኑ ሳንንጠራራ ልናወርደው የምንችለውን ቴክኖሎጂ መሆን አለበት። በመስኖ የሚለማው መሬታችንን በሙሉ ለማልማት ስፍር ቁጥር የሌላቸው ታላላቅ ግድቦችን አሁኑኑ መገንባት ሳይሆን በጥቂት ገንዘብና በሰፊ ጉልበት ቢያንስ አንድ ጊዜ ጥሩ ምርት የምናመርትበትን መላው የሚታረስ መሬታችንን፣ በዝናብ ውሀ ብቻ በአመት ሁለት ጊዜ ልናመርትበት የምንችልበትን በቢሊዮኖች ሄክታር የሚቆጠር ኮትቻ አፈራችንን፣ በመለስተኛ የወንዝ ጠለፋ ወይም በአነስተኛ የጉድጓድ ቁፋሮ በመስኖ ልናለማው የምንችለውን በሚሊዮኖች ሄክታር የሚቆጠር መሬታችንን ማልማት ሊሆን ይገባል። በተጨባጭ በኛ አቅም ሊሰራ የሚችል መሆኑን መንጠራራት የማይጠይቅ መሆኑን ያረጋገጥነውን ቴክኖሎጂና ፍሬ ሳንሰበስብ ወደ መንጠራራት መሻገር የለብን" በማለት አነበበ።

My text!

ንባቡን ጨርሶ ወደ ሌላ መዕ[illegible] ሊሸጋገር ሲል ቃና ብሎ አዳራሹን ቃኘ። ከሁለት ሺህ በላይ ካድሬዎች ማስታወሻ እየወሰዱ በጥሞና እያዳመጡት ነው። እንዳንዶቹም በሀሳቡ በመስማማት አንገታቸውን ከላይ ወደ ታች ያወዛውዛሉ። እኔም ከርቀት አውራ ጣቴን ወደላይ በማድረግ አሳየሁት።

ሚኒስትሩ ቀጠለ፣

"...ብዙ ሠዎች እናንተንም ጨምሮ ፈጣን የልማት መንገድ ምንድነው ተብለው ሲጠየቁ የሚሰጡት መልስ በማዕድን በተለይም በነዳጅና ወርቅ እና ሌላ ምርጥ ማዕድን ማግኘት እንደሚሉ አልጠራጠርም። ይህ ፈጽሞ የተሳሳተ ነው። ጓድ መለስ! ከዚህ በፊት እንደ ገለጠው ከሆነ የደች በሽታ የሚባል ነገር አለ። ኔዘርላንድስ ከፍተኛ የተፈጥሮ ጋዝ ባገኘች ወቅት የተፈጠረ ችግር ነው። በኔዘርላንድ የተገኘው ጋዝ ሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች እንዳያብቡ ተጽእኖ አሳረፈ።...

የዳች በሽታ በከፋ መልኩ የታየው ግን ናይጀሪያ ውስጥ ነው። ናይጀሪያ ነዳጅ በማግኘቷ ምክንያት ግብርና እና ጉልበት የሚጠቀሙ ኢንዱስትሪዎች በአፍጢማቸው ተደፍተዋል። በዚህም ምክንያት ኪራይ የሚያሠባስቡ የአካባቢ ጎረምሶች ማዕድኑን በመቆጣጠር አገሪቱን በሙስና ተወዳዳሪ የሌላት አደረጓት። ህዝቡም በተለይም ማዕድኑን አካባቢ ያለው ልማታዊ አቅሙን በመግደል ኪራይ ሠብሳቢ ሆነ።... ስለዚህ በሀገራችን እርስ በራሱ የሚቆራኝና ተመጋጋቢ የሚያድግ ኢኮኖሚ እንዲኖር ምኞታችን ከሆነ የማዕድን ሀብት ልማት ላይ ማተኮር አይኖርብንም፡ በእርሶ አደር ማሳ ላይ የሚካሄደውን ልማት እንደ ዋነኛ አቅጣጫ መውሰድ ይኖርብናል" በማለት ተናገረ።"

"ክብር!" ሚኒስትሩ ተናግሮ ሲጨርስ አዳራሹ በጭብጨባ ተናወጠ።

እኔም አጨበጨብኩ።

***

እነሆ! ክፉ ጓደኛዬ ቴዎድሮስ ቂ.ች በሰጠኝ ማሳሰቢያ መሰረት መረጃዎች ማሰባሰብ እንዱ ስራዬ ሆነ ። ...እውነት ከኢትዮጵያ ገንዘብ እንዲወጣ ይደረጋል? ምን ያህል ገንዘብ ይወጣል?

ገንዘቡን የሚያሸሸው ማነው?... ከፋ ጓደኛዬ ሳልወድ በግድ አንድ የማስታወሻ መስኮት
እንድከፍት አደረገኝ። እሪ በይ ሀገሬ!...

እሪ በይ ሀገሬ!

እሪ በይ ኢትዮጵያ!!

ጥር ወር 2015(እ•ኤ•አ•)

"ትራክ፣ ስቶፕ፣ ጌት
በቀድሞው የደቡብ አፍሪካ ፕሬዝዳንት ታቦ ምቤኪ የሚመራውና "ትራክ፣ ስቶፕ፣ ጌት
በቀድሞው የደቡብ አፍሪካ ፕሬዝዳንት ታቦ ምቤኪ የሚመራውና

My

ተግባር የሚፈፀመው በንግድ አማካይነት ደረሰኝ በማጭበርበር፣ ሐሰተኛ የግብይት ደረሰኞችን በማሰራጨት፣ አሳንሶ ወይም አጋኖ ዋጋዎችን በማሳየት ገቢን ለመሰወር የሚደረግ ገንዘብ የማሸሽ ተግባር እንደሚታይ አሳውቋል። ከኢትዮጵያ በሚሸሸው የውጭ ምንዛሪ ሳቢያ የአገሪቱ የልማት ጉዞ ከፍተኛ እንቅፋት እያጋጠመው እንደሆነም አሳስቧል።

እንግዲህ ከሪፓርቱ ለመረዳት እንደሚቻለው ከኢትዮጵያ በአስራ ሦስት አመት ውስጥ ብቻ 26 ቢሊዩን ዶላር (600 ቢሊዩን ብር) በዝቅተኛ ግምት እንዲኮበልል ተደርጓል። ከሁሉም እንነት የሚያስደፋው ከአፍሪካ ሀገሮች ውስጥ ወደ ሲሶው የሚጠጋውን (28%) የሚሸሸው አቶ በረከት "የአፍሪካ ኑብር አደረግናት" በማለት ከሚጠሯት ኢትዮጵያ መሆኑ ነው። ሪፖርተር ከአስር የአፍሪካ ሀገሮች አንዷ የሚል ማደናገሪያ ቢያስቀምጥም እውነታው ከአፍሪካ በንግድ ማጭበርበር፣ በወንጀልና ሙስና ከሚወጣው አጠቃላይ ገንዘብ ከሦስት እጅ አንድ እጅ ከኢትዮጵያ ነው።

እንደ እውነቱ ከሆነ የአፍሪካ ህብረትም ሆነ ሪፓርተር ጋዜጣ "የትሮይ ፈረስ" የሚል ስያሜ በስምአን ልጅ ሊሰጣቸው ይችል ይሆናል እንጂ በታአማኒነቱ ላይ ጥያቄ የሚነሳ አይሆንም። በኢህአዴግ የሚንቆለጳጰሱትና የአቶ መለስ የቅርብ ወዳጅ የሆኑት ታቦ ምቤኪም ጉዳዩን በቅርብ ከትትል በመስራት ይፋ እንዳደረጉት መገመት ይቻላል። ይህን እውነታ ከግምት ተወስዶ ይህን ያህል ገንዘብ ከኢትዮጵያ ባይወጣ ምን ሊሰራ ይችል ነበር? የሚለውን አብሮ መመልከቱ በሀገራችን ላይ እየደረሰ ያለውን አደጋ ለመረዳት ያስችለናል። ልማታዊ መንግስታችን እስከልተቀየመን ድረስ!!

ከላይ ለማሳየት እንደተሞከረው በአስራ ሶስት አመት ውስጥ ብቻ ከኢትዮጵያ እንዲሸሽ የተደረገው ከ30 እስከ 36 ቢሊዩን ዶላር ይደርሳል። ኤፈርትን የመሳሰሉ ኩባንያዎች ገንዘብ የማሸሽ ተግባራቸውን አጠናክረው ቀጥለዋል። ይህ ገንዘብ ኢትዮጵያ ውስጥ ኢንቨስት ቢደረግ ኖሮ ምን ይሰራ ነበር?

***

"የ60 አመት አጠቃላይ የትምህርት ወጪ"

ከ70 በላይ ዩኒቨርሲቲዎች"=

መጽሀፍት ማዘጋጃ፣ ለአንደኛ፣

አጠቃላይ የትምህርት ወጪ ፍላጐት የሚያዘው ለመማሪያ መጽሀፍት ማዘጋጃ፣ ለአንደኛ፣ ሁለተኛ ደረጃና ቴክኒክ ትምህርት የመደበኛ ወጪ ማለትም በትምህርት ገበታ ላይ ያሉትን ተማሪዎች ለማስተማር እና ለካፒታል ወጪ የሚያስፈልግ ወጪን ማለትም በአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ላይ መማር ያለባቸው ሆኖ ግን ወደ ትምህርት መስክ ያልተቀላቀሉትን በሙሉ ያጠቃልላል።

ከኢትዮጵያ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በተገኘ የአምስት አመት መረጃ (ከ1998 -2002 እም) መረጃ መሰረት ለአጠቃላይ ትምህርት ወጪ ማለትም ለመማሪያ መጽሀፍት ዝግጅት፣ አንደኛ፣ ሁለተኛና ቴክኒክ ትምህርት መደበኛና ካፒታል ወጪ ፍላጐት የሚያስፈልገው የብር መጠን 9 ቢሊዩን ያህል ይሆናል።

በመሆኑም የኢትዮጵያ ባለስልጣናትና ኤፈርትን የመሳሰሉ ኩባንያዎች በአስራ ሶስት አመት ውስጥ ብቻ ያሸሹትን ገንዘብ በአጠቃላይ የትምህርት ወጪ ላይ ቢውል ለ60 አመት ያህል የኢትዮጵያ ታዳጊዎችና ወጣቶች ወጪያቸው ተሸፍኖ የተሟላ ትምህርት ያገኙ ነበር። ይህን ቀመር ወደ ዩኒቨርሲቲዎችም መውሰድ ይቻላል። አንድ ዩኒቨርሲቲ ለመገንባት እስከ አስር ቢሊዩን ብር ሊፈጅ እንደሚችል ታሳቢ ቢወሰድ ፣ በተጠቁሰት አስራ ሶስት አመታት ብቻ የሸሸው የፋይናንስ መጠን ከ60 በላይ ዩኒቨርሲቲዎችን ይገነባል። ይህ ማለት አሁን ካሉት ዩኒቨርሲቲዎች እጥፍ ይኖረን ነበር።

***

"የ68 አመት የመጠጥ ውሀ ወጪ"

በአቶ መለስ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ መሰረት በእቅዱ መጨረሻ (2007 መሆኑ ነው) የከተሞች የንጹህ መጠጥ ውሀ ሽፋን 100%፣ የጠር ደግሞ 98% መድረስ እንደሚኖርበት ያስገነዝባል። የመጠጥ ውሀ ሽፋን አለ የሚባለው በከተማ የሚኖር አንድ ሰው በቀን 30 ሊትር ውሃ በ500 ሜትር ርቀት ውስጥ፣ በገጠር የሚኖረው ደግሞ 15 ሊትር ውሃ በ1•5 ኪሎ ሜትር ርቀት ውስጥ ማግኘት ሲችል ነው። ከማእከላዊ ስታቲስቲክስ /2003 እም/

My

በተገኘ መረጃ መሰረት በመላ ሀገሪቱ የአመት ድምር የመጠጥ ውሀ የወጪ ፍላጐት 8.8 ቢሊዮን ብር ያህል ይሆናል። ይህ ቀመር ወደ አጠቃላይ አመት ቢገለበጥ በግማሽ የዘመነ ኢህአዴግ ከሙስና የወጣው ገንዘብ የ68 አመት የመላው ኢትዮጵያን የመጠጥ ውሃ ይሸፍናል።

***

"እምስት የአባይ ግድብ"

ስለ አባይ ግድብ የገንዘብ ሞብላይዜሽን ሳስብ በሚያዝያ 28 ቀን 2003 እ.ም የወጣችውና እጄ የገባችው ፍትህ ጋዜጣ ትታወሰኛለች። በጋዜጣዋ ላይ " ይድረስ ለአቡነ ቀውስጦስ፡ የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ" በሚል ርእስ ጳጳሱን የሚሞግት እንደሆነ ተመልከቻለሁ። ጳጳሱ " አባይን መገደብ" አስመልክቶ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ላይ ተገኝተው የሰጡት አስተያየት በተደጋጋሚ በየቀኑ በመቅረቡ ምክንያት የተሰማውን ቅሬታ ያቀረበበት ነበር።

የጳጳሱ መልእክት፤

"ለአባይ ግድብ በማህፀን ካሉ ህጻናት፤ በመቃብር ካሉ ሙታን በስተቀር ሁሉም ኢትዮጵያዊ ይተባበራል። መተባበርም አለበት። አልተባበርም ካለ እሱ በገዛ ራሱ ኢትዮጵያዊነቱን ሰርዞታል" የሚል ነበር።

የጋዜጣው አምደኛ የእምነት አባቱን የሞገተውና ብርቱ ቅሬታ ያደረበት ለግድቡ አልተባበርም ካለ ኢትዮጵያዊነቱ ተሰርዟል የሚለው አባባላቸው እንደሆነ በግልጽ አመላክቷል። ኢትዮጵያዊነት ሰጭና ነፋጊ ሆነው በመገኘታቸው ንስሀ ገብተው የኢትዮጵያን ህዝብ ይቅርታ ጠይቀው ወደ መንፈሳዊ አባትነታቸው እንዲመለሱ በደረታቸው በያዙት መስቀል ተማጽኖ አቅርቧል።

ሊቀ ጳጳሱ በይፋ ይቅርታ ይጠይቁ / አይጠይቁ መረጃው በይኖረኝም አባይን ለመገደብ የሚያስፈልገውን ወጪ በማህፀን ላይ ያሉ ህጻናት ሳይጠሩ፤ በመቃብር ያሉ ሙታን ሳይነሱ፤ ኢትዮጵያዊነትን መሰረዝ ሳያስፈልግ በቀላሉ መሸፈን ይቻል እንደነበር ሊገነዘቡት ይገባል። አባታችን እንደሚያውቁት የአባይ ግድብ እስከ 5 ቢሊዮን ዶላር እንደሚፈጅ ምድራዊ መንግስትዎ ይፋ አድርጓል። አባታችን እንዳማያውቁት ደግሞ ከኢትዮጵያ ህዝብ ጉሮሮ እየተቀማ በእስሩ

በት አመት ብቻ የተሰደደው ገንዘብ ከ26 ቢሊዮን ዶላር ደርሷል። በዚህ መልኩ የሸሸው ገንዘብ ግንም ግዙትና ተግባሩ ሳያስፈልገው አምስት የአባይ ግድቦችን ይገነባል።

በአጠቃላይ መልኩ ኤፈርትን የመሳሰሉ ኩባንያዎች በተጭበረበረ መንገድ፣ የንግድ ሰነዶችን በማሳሳት፣ ዝቅተኛ ገቢ አግኝተው የከሰሩ በማስመሰል፣ ከፍተኛ ወጪ በማስመዝገብ ...ወዘተ ያገኙትን ገንዘብ ወደ ወጪ ባያወጡት ኖሮ ምን ይህል ለውጥ ማምጣት ይቻል እንደሆን ማት ይቻላል። ለዚህ እውነት አማኝ እንዲሆን የፌደራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ አስረኛ ወንጀል ችሎት በታህሳስ 10 ቀን 2005 ዓ. ም. የሰጠውን የፍርድ ውሳኔ አንድ ማሳያ ተደርጐ ሊወሰድ ይችላል። ፍርድ ቤቱ የኤፈርት አንድ አካል የሆነውና በወይዘሮ አዜብ የበላይነት ሲመራ የነበረው ሜጋ ኪነጥበባት ማእከል ለሰምንት አመታት (1996 -2002 አም) ያደረገው የንግድ እንቅስቃሴ በማጭበርበር ላይ የተመሰረተ፣ ወጪን ከፍ አድርጐ የሚያሳይ አሳሳች ማስረጃ የቀረበበትና ተጨማሪ እሴት ታክስ ያልከፈለ መሆኑን በማረጋገጥ የቅጣት ውሳኔ አሳርፎበታል።

My text!

ምእራፍ 9

አልመዳ

"የሲሚንቶ ፋብሪካውም ቢሆን የሀገር ሲሚንቶ ነው። ጨርቃ ጨርቁም ቢሆን የሀገር ጨርቃጨርቅ ነው። ምርቱ ሁሉ የሀገር ምርት ነው። በባሕርዳር ይሠራ! ትግራይ የሀገር ምርት ነው። ለትግራይ የተደረገው ሁሉ ለመላው ኢትዮጵያ እንደተደረገ መቆጠር አለበት።"

ስብሀት ነጋ

(ሪፖርተር መጽሔት ቅጽ 3 ቁጥር ፪4)

"ኤፈርት የትግራይ ህዝብ ንብረት ነው።"

አዜብ መስፍን

(ኢቲቪ ታህሳስ 2005 ዓ.ም.)

"በአሁን ሰዓት የትግራይ ህዝብ ከማንኛውም የኢትዮጵያ ህዝብ በላይ የተበደለ ነው።"

ግደይ ዘራፅዮን

(ፎረም 65፡ ሜይ/2016)

***

በዚህ ማስታወሻ የኤፈርት ኩባንያዎችን በሙሉ በዝርዝርና ነጥብ በነጥብ መመልከት አይቻልም። እያንዳንዳቸው ኩባንያዎች ለምን ተልዕኮ፣ በየትኛው ዘርፍና አገልግሎት እንደተቋቋሙ ለመግለጽ አሁንም ራሱን የቻለ መድብል ይፈልጋል። ገደብ ባጣ የገንዘብ ምንጭ ከኢትዮጵያ መሬት በላይ ያበጠውን ኤፈርት ለመቃኘት ሠፊ ትንተና እና ዘገባ ይፈልጋል። የተሸከመው ክብደት ግመል የሚሸከመውን ውርንጭላ እንደሚሸከመው ማድረግ ያህል ስለሆነ ከላይ ለመግለጥ እንደተሞከረው የኤፈርት ነገር "የበላችው ያስገሳታል፤ በላይ በላዩ ያጎርሳታል"

የሚለውን ሀገራዊ አባባል የሚገልጥ ነው። ሁሉም ነገር ወደ ኤፈርት በሚል የከተት ዘመቻ አዋጅ ግልፅ በሆነ አላማና መመሪያ የተፈፀመ እና እየተፈፀመ ያለ!!

በተለያዩ ጊዜያት ኢኮኖሚያዊ ጉዞ በተመለከተ ጉዳዩን በጥልቀት የመረመሩ ምሁራን ጋር ተደጋጋሚ ውይይት የማድረግ እድል አጋጥሞኛል። እነዚህ ምሁራን እንደገለጡት ከሆነ ኤፈርት ኢትዮጵያዊያንን የመዝረፍ ሕልሙ ትልቅ ነው። ድርጅቱ ራሱን በበርካታ ግዙፍ ኩባንያዎች አደራጅቶ በሁሉም አቅጣጫ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ በመቦጥቦጥ ላይ ይገኛል።የኤፈርት ኩባንያዎች ያሻቸውን ያህል ብድር ወስደው ያለመክፈል ልዩ ፈቃድ ያላቸው ቅምጥል ድርጅቶች ናቸው። በየጊዜው በብድር የወሰዷቸው በርካታ ቢሊዮን ብሮች የባንክ እዳ እንዲሠረዝላቸው ይደረጋል። በግል ባንኮችም የአንበሳ ድርሻ አክሲዮን በመያዝ ፋይናንስ ሴክተሩን በመቆጣጠር ላይ ይገኛል። በአገሪቱ ያሉ ዋና ዋና የቢዝነስ ኮንትራቶችን እና አቅርቦቶችን የሚወስደው ኤፈርት ነው። ለአባይ ግድብ ግንባታ ዋና አቅራቢ ነው። የአገሪቱን 40 በመቶ የፒቪሲ (ፕላስቲክ ነክ ምርቶች) ገበያ ለመቆጣጠር የሚያስችለውን የማምረቻ ተቋም እየገነባ ነው። ፎርቹን ጋዜጣ "Ethiopian First PVC Resin Plant- 7 Billion By EFFORT" በሚል ርዕስ መረጃውን ይፋ አድርጓል። በከፊል ይሔን ይላል፡-

"ኤፈርት በኢትዮጵያ የመጀመሪያ የሆነው የፒቪሲ (ፕላስቲክ ነክ ምርቶች) ማምረቻ በ7 ቢሊዮን ብር እየገነባ ነው። ይህ በትግራይ ልዩ ቦታው ማይ መኪደን በተባለ ስፍራ በ48 ሔክታር እየተገነባ ያለ ፋብሪካ የሚያመርተው ፖሊቪኒክ ሎራይድ (ፒቪሲ) እና ለሌሎች ኢንዱስትሪዎች ግብአት የሚሆኑ ኬሚካሎችን ነው። የፋብሪካው ግንባታ ተጠናቆ ወደ ምርት ሲገባ በአመት 60ሺህ ቶን የማምረት አቅም ይኖረዋል። የኤፈርት ዋና ስራ አስፈፃሚ የሆኑት ወይዘሮ አዜብ መስፍን ፒቪሲ ፋብሪካው የሚያመርታቸው ኬሚካሎች እንደ መሶቦ፣ መስፍን ኢንዱስትሪያልና አልመዳ የመሳሰሉ እህት ኩባንያዎች ግብአት ሆኖ እንደሚያገለግል ገልፀዋል። አዲሱ የኬሚካል ፋብሪካ ኤፈርት ካሉት 14 ፋብሪካዎች አንዱ ሲሆን ከእሱ በፊት የነበሩት መሶቦ ሲሚንቶ እና መስፍን ኢንዱስትሪያል ተጠቃሚ የሚያደርግ ነው።"

ዜናው ከሞላ ጎደል ይሔን ይመስላል። ከሁሉም የሚገርመው በ7 ቢሊዮን ብር ወጪ እየተገነባ 40 በመቶ የአገሪቱን ፒቪሲ ገበያ የሚቆጣጠረው ፋብሪካ በዜናው ላይ አስተያየት የሚሰጠው የአህዴድ ባለስልጣን ነው። የአህዴዱ ካድሬና የፋይናንስ ሀላፊ ግርማ እለሙ

እንደገለጠው በሙቀሌ የሚገነባው ፋብሪካ የሀገሪቷን የውጭ ምንዛሪ ከማዳኑም ባሻገር ሌሎች የሀገር ውስጥ ፋብሪካዎ እንዲጠናከሩ ያደርጋል።

በነገራችን ላይ አቶ መለስ በቀረፀው የኤፈርት የሠላሳ አመት ኢምፓወርመንት ፕላን መሠረት በእቅዱ ግማሽ ክፍለጊዜ ኩባንያዎች የት መድረስ እንዳለባቸው በግልፅ አመላክቷል። አብዛኛዎቹ ፋብሪካዎች እና የንግድ ኩባንያዎች 40 በመቶ የአገሪቱን ገበያ ለመቆጣጠር የሚያስችል ነው። አቶ መለስ ባስቀመጠው መሰረት ብዙዎቹ ፋብሪካዎች ግባቸው በመምታት ላይ ይገኛሉ። መሰቦ ሲሚንቶ 40 በመቶ የአገሪቷን ሲሚንቶ ገበያ እንዲቆጣጠር ተደርጓል። መስፍን ኢንዱስትሪያል በከባድ ተሽከርካሪ ሽያጭ ከ40 በመቶ በላይ ሆኗል። ጉና የንግድ ድርጅት፣ ትራንስ ኢትዮጵያ፣ ኢዛና የማዕድን ልማት ወደተጠበቀው ግብ እየደረሱ ነው። "ኤፈርት-መር ካፒታሊዝም" የህወሓት የኢኮኖሚ ፖሊሲ ውጥን ወደ ተግባር እየተመነዘረ ነው።

በአንድ ወቅት መምህሬ ("ሜንቶሬ") የሆነው ኢኮኖሚስቱ ወዳጄ በሁለተኛው ማስታወሻ ኤፈርት ላይ አጽንኦት እንደምሠጥ ጠቆም አደረኩት። መረጃውን የሠጠሁት እዛው ሳለ የሜንቶር አገልግሎት ለማግኘት በማሰብ የተቀየሠ ነበር። ወዳጄ በአድናቆት ማበረታታት ውስጥ ሆኖ፣

"ስለ ኤፈርት-መር ካፒታሊዝም መፃፍ እነ መለስ ምን አይት የኢኮኖሚ ስርአት እየገነቡ እንደሆነ በደንብ ስለሚያመላክት "አቶ እንደልቡ" *(ስብሀት ነጋን "አቶ እንደልቡ" እያለ እንደሚጠራው አውቃለሁ)* በተለያየ ጊዜያቶች የሚሠጣቸውን መግለጫዎች በደንብ መርምራቸው። "አቶ እንደልቡ" የድርጅታቸው የኢኮኖሚ ፖሊሲ ግብ ካፒታሊዝም መሆኑን፣ ይህ ካፒታሊዝም የሚመራው በኤፈርት መሆኑ እና ካፒታሊስቱ መደብ ሲጎላበት እንደ መነሻ መውሰድ ትችላለህ" አለኝ።

አስከትሎም እንዲህ አለኝ፣

"ለማስታወሻው መነሻ የሚሆን መጣጥፍ ከፈለክ የአሜሪካው ኢኮኖሚትስ ማንኩር ኦልሠን "እምባገነንነት፣ ዴሞክራሲና ልማት" በሚል ርዕስ የፃፈውን አንብበው። ኦልሠን የሠጠው ስዕላዊ ገለፃ ዘላን ወንበዴዎች **(roving bandits)** ከነጥቆ በራሪነት ወደ ቋሚ ወንበዴነት **(stationary bandit)** እንዴት እንደሚቀየሩ ይገልጣል። መጣጥፉን አልከልሃለው።... ሁሉንም የኤፈርት ኩባንያዎች ("የሙስና መርከብ") መዳሠስ ስለማይቻል እንደማሳያ የተወሰኑት ላይ አተኩር" አለኝ።

My text!

በቃሉ መ[illegible]ት [illegible]ሬን[illegible] ቃ[illegible] መመዘኛ [illegible]ንደ[illegible]ጠን [illegible]ውቁ ኢኮ[illegible]ሚስት ማንኩር ኦልሠን ማስታወሻ ላከልኝ። እ[illegible]ን እንዲህ ይ[illegible]፡

"ዘላን ወንበዴዎች /roving bandits/ ንጥቀው ይሮጣሉ። እነዚህ ወንበዴዎች ንጥቀው በሮጡ ቁጥር የማህበረሰቡ ሀብት የማፍራት ፍላጎት ስለሚዳከም በሚቀጥለው ዙር የሚዘርፉት ነገር እያነሰባቸው ይመጣል። ቀን ባለፈ መጠን ነጥቆ መሮጥ እንደሚጎዳቸው ይገነዘቡና ራሳቸውን ከተዘዋዋሪ ወንበዴነት ወደ ቋሚ ወንበዴነት /stationary bandit/ ይቀየራሉ። ለንጥቂያቸውም ስርአትና ልክ ያበጁለታል።"

እናም! ይህ ወዳጄ እንዳለው የህወሓት ኩባንያዎች ነጥቆ ከሚበር ዘላን ወንበዴነት ወደ ሠፋሪ ወንበዴነት ተቀይረው ይሆን?... በሂደትስ እነዚህ ኩባንያዎች የሚፈጥሩት የሀብት ማጋበስና ኢፍትሐዊነት ሀገሪቷን ወደ ብጥብጥና አለመረጋጋት ይቀይሯት ይሆን?...ስርአት የተበጀለት ዘረፋና ንጥቂያው ጊዜ ከተሰጠው ሀገሪቷን ሊጠገኑ የማይችሉ ቋሚ ስብራቶች ይዳርጋት ይሆን?...እስቲ "አልመዳን እንደ ምሳሌ" በመውሰድ ጉዳዩን ዘርዘር አድርጎ ወደ መመልከት እንሸጋገር።... በዚህ ምዕራፍ በተቻለ መጠን የተወሰኑ ቁልፍ ጉዳዮችን ለመዳሰስ እንሞክራለን። ...አልመዳ ለምን አላማ እንደተቋቋመ፣ በእነማን እንደተቋቋመ!... ለምን ልዩ ትኩረት እንደተሰጠው፣... ፋብሪካውን ለማጠናከር ምን ስትራቴጂ እንደተቀየሰ፣... ከንግድ ባንክ ምን ያህል ብድር እንደወሰደና የባንክ እዳው ምን እንደተደረገለት፣... በአንድ ወቅት አልመዳ የገበያ ችግር ሲገጥሞት የሞት ጉዞ ሲጀምር በአቶ መለስ የተቀረፀው "አለምዳን አናድን" ፕሮጀክት ምን ውጤት እንዳስገኘ እንመለከታለን። አልመዳ ከራሱ አልፎ ሌሎች የኤፈርት ኩባንያዎች እንዲቋቋሙ የአክሲዮን ባለቤት የሚሆንበትንና እርስ በራስ የሚተሳሰርበትን ሁኔታ እንዳስሣለን።

አንባቢያን ምን አልባት ይህንን ምዕራፍ ሲያነቡ አንድ ጥያቄ ሊያነሱ እንደሚችሉ እገምታለሁ። አልመዳ ብቻ ተለይቶ ለምን ቀረበ የሚል ጥያቄ ሊቀርብ ይችላል። ከሌሎች የኤፈርት ኩባንያዎች ምን የተለየ ገፅታ ስለኖረው ነው የሚልም ተደምሮ ሊነሳ ይችላል። በመሠረቱ የህወሓት ኩባንያዎች ተቋማት አመሰራረትና አላማ ተመሳሳይ ነው። እንዳፈተተው የተፈጠሩ አይደለም። ለፓርቲው እና ለተቋቋሙለት ማህበረሰብ የሚሰጡት ጠቀሜታ በመጠን ይለያይ ይሆናል እንጂ የተለአኮ ልዩነት የላቸውም። ሁሉም ኤፈርት-መር ካፒታሊዝም በኢትዮጵያ ተገንብቶ ማየት መዳረሻ ህልማቸው ነው።...

ሁሉም በኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ጉልላት ላይ ተቀምጠው የህወሓትን ፖለቲካል ኢኮኖሚ የበላይነት ማረጋገጥ የሚችሉበት ሁኔታ መፍጠር ነው።... ሁሉም እርስ በራስ ተሳስረውና ተደጋግፈው እንዲሁም የሌላውን ስልጣን ተጠቅመው ሌላውን እየደቆሱና መፈናፈኛ እያሳጡ ከጥቅም ውጪ ማስወጣት ነው። በመሆኑም የኤፈርት ኩባንያዎች የመኖርና ያለመኖር ጉዳይ ለህወሓት በቀላሉ የመቢታተን አደጋ ያጋጥመዋል። በተመሳሳይ መልኩ ህወሓት የበላይነቱን ከተነጠቀ ኤፈርት በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ውስጥ ስር እንዲሰድ እንደሚያስችለው የተቀየሰው ስትራቴጂ ወደ ተግባር ሊቀየር አይችልም።

አልመዳ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ ህወሓት በመጀመሪያ አካባቢ ካቋቋማቸው ስድስት ስትራቴጂክ ኢንዱስትሪዎች አንዱ ነው። ፋብሪካውና ዋና ጽ/ቤቱን በትግራይ ያደረገው አልመዳ፣ በአዲስ አበባ እና በድሬዳዋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እንዲኖሩት አድርጓል። ፋብሪካው ከሚያመርታቸው ምርቶች ውስጥ ከሱፍ (ውል) እና ጥጥ የተሰሩ ክሮች፣ ሱሪ፣ ጃኬት፣ የስፖርት ትጥቅ፣ አልጋ ልብስ፣ እንሶላ፣ ትራስ፣ ፎጣ፣ ካልሲ፣ ወታደራዊ ዩኒፎርሞችንና ቁሳቁሶችን ... ወዘተ ይገኙበታል። ፋብሪካው ከጃፓን፣ ከስዊዘርላንድና ከኢጣሊያ የመጡ እጅግ የረቀቁ መሳሪያዎች የተገጠሙለት ሲሆን፣ በርቦት የሚሰራ ክፍልም አለው። አልመዳ ትግራይን የኢንዱስትሪ ከለል (ኢንደስትሪያል ስቴት) እንድትሆን ልዩ ትኩረት ከተሰጣቸው የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ በግንባር ቀደም የሚጠቀስ ነው።

አቶ መለስ የጨርቃጨርቅና የልብስ ስፌት ኢንዱስትሪን ከሁሉም ተግባራት ግምባር ቀደም ትኩረት የሰጡበት የራሱ ምክንያት በግልጽ አስቀምጧል። የመጀመሪያው፣ ከህወሓት የተቀነሱ "ዲሞብላራይዝድ" ታጋዮች በሰፊው ወደስራ የሚያሰማራው ዘርፍ የጨርቃጨርቅ የልብስ ስፌት ፋብሪካዎች ከተቋቋሙ ነው። በተለይም ቶሎ ስሜት የሚይዙትን እነስት ተጋዳሊቶች በፍጥነት ቦታ ቦታ ማስያዝ በስርዓቱ ላይ እንዳይነሱና፣ ተመልሰው እንዳይሸፍቱ ያደርጋቸዋል። በቀናት ቀላል ስልጠና ወደ ምርት ማሸጋገር ስለሚቻል ተጋዳሊቶቹ ወደስራ ለመሰማራት የተለየ እውቀት የሚጠይቅ አለመሆኑም ለህወሓት አመራሮች አቋራጭ መንገድ ሆኖላቸዋል። እንደተገመተው አልመዳ ጨርቃጨርቅና የልብስ ስፌት ፋብሪካ እንደተቋቋመ ከ10ሺህ በላይ ለሚሆኑ ተጋዳሊቶች በቀጥታና በተዘዋዋሪ መንገድ የስራ እድል ፈጥሯል።

በሂደትም አልመዳ ራሱን እያሳደገ እና አዳዲስ ምርቶችን እየጨመረ ሲሄድ የሚያስማራቸው ተጋዳሊቶች በሶስት እጥፍ አደጉ።

የህወሓት ነባር ታጋይ እና የትግራይ ክልል ፕሬዝዳንት የነበረው ገብሩ አስራት "ሉአላዊነት እና ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ" በሚለው መፅሀፍ አልመዳ ጨርቃጨርቅና የስፌት ፋብሪካው ለበርካታ ሴት ተጋዳሊቶች የስራ እድል መፍጠሩን ገልጿል። እነዚህ ተጋዳሊቶች በትምህርታቸው ያልገፉና ብቃታቸው ደካማ ቢሆንም በተሰጣቸው ስልጠና በዚህ ስራ ሊሰማሩ መቻላቸውን አመልክቷል። ገብሩ አስራት "የ1985 ዓ.ም የህወሓት ግምገማና ውዝግቦች" በሚለው ርዕስ ስር በገጽ 203 ላይ፤

"... ሴት ታጋዮች ብቻ እስከተወሰነ ጊዜ መከላከያ ሚኒስቴር እየከፈላቸው እንዲማሩ ተደርጎ፤ ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ ስልጠና ተሰጥቷቸው በተለያዩ ስራዎች እንዲመደቡ ተደርጓል። በርካታ ሴት ታጋዮች ትዕምት ባቋቋማቸው የጨርቃጨርቅና የስፌት በመሳሰሉ ፋብሪካዎች በጉልበት ሠራተኝነት ሲመደቡ በትምህርት ደህና የገፉ ደግሞ እንደየአቅማቸው በመንግስት መስሪያቤቶች ተመድበው ነበር" በማለት ይገልጻል።

አቶ ገብሩ አስራት በዚህ ርዕስ ስር ብዙ ተጋዳሊቶ የተመደቡበት ስራ እጅግ አድካሚ ከመሆኑ ባሻገር የሚከፈላቸው ደመወዝ ዝቅተኛ ስለነበር ከፍተኛ ቅሬታ ቋጥረው እንደነበር ይገልፃል። በተጨማሪም ተጋዳሊቶች "በምትከፈላቸው አነስተኛ ደመወዝ የኪራይ ቤት፣ የምግብ፣ የልብስና ሌላ ወጪያቸውን መሸፈን ያዳግታቸው ስለነበርም በጊዜው ቅሬታና አለመግባባት ቢኖርም ለችግሮቹ መፍትሔ መገኘት አልተቻለም ነበር" በማለት በወቅቱ የነበረውን ሁኔታ ለተጋዳሊቶቹ ተቆርቋሪ በመሆ በቁጭት ያስታውሳል። ርግጥም አቶ ገብሩ እንዳለው ተጋዳሊቶቹ ከሌሎች ጓደኞቻቸው ጋር ራሳቸውን አወዳድረው ስሜት ይዘው ነበር። ይህንን ቅሬታ መጋራት እንደ አንድ የታጋዮች መሪ ትክክል ሊሆን ይችላል። ይገባልም።

ነገር ግን አቶ ገብሩ አስራት ከስሜት ወጥተው እንደ አንድ ኢትዮጵያዊ የፖለቲካ አመራር ቢመለከቱት ከ10ሺህ በላይ ተጋዳሊቶች በልዩ ሁኔታና ፍትሐዊ ባልሆነ መንገድ "ከነፍጠኝነት" ወደ "ላብአደርነት" ሲቀየሩ መመልከቱ ቅር ያሰኛቸው ነበር። ሌላው ቀርቶ የትግል አጋራቸው የሆነው የበረከት ፓርቲ (ብአዴን) ሴት ተጋዳሊቶችን "መቀመጫችሁን ላሱ" በማለት አውላላ ሜዳ ላይ መበተኑን በተመለከተ አይናቸው ቢመዝኑት ጥሩ ነበር። የብአዴን ነባር ታጋይ

የሆነችው እና ጀነራል ባጫ ደበሌ ሁለት ልጅ አሳቅፏት ቀበሌ በሰጣት ቆርቆሮ ቤት የምትኖረውን አሚይቱ ቢመለከት ሚዛናዊ ይሆን ነበር። ከሁሉም በላይ የትግራይ ክልልን "የኢንዱስትሪ ግዙፉ ለማድረግ አልመዳ ጨርቃጨርቅ የሔደበት ርቀት እንደ ቀድሞ ህወሓት አባልነታቸው የሚያኮራቸው መሆን ይገባው ነበር። በዛ ላይ የአልመዳ የደሞዝ ስኬል በኢትዮጵያ ውስጥ ካሉ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች በእጥፍ የሚጨምር መሆኑን ለሚያውቁ ሠዎች የአቶ ገብሩ እንባ የአዞ አሊያም ከጀርባው ሌላ ማነሳሳት እንዳለው መገመት አያቅተውም።

የትዕምት ዋና ስራ አስፈጻሚ የሆነችው ወ/ሮ አዜም መስፍን በአንድ ወቅት ከኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ጋር ባደረችው ቃለመጠይቅ በአልመዳ ጨርቃጨርቅና ልብስ ስፌት ፋብሪካ በቋሚነት 6ሺህ፣ እንዲሁም በተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍል በሽያጭ የተሰማሩ ተጋዳሊቶች ከ10ሺህ በላይ መሆናቸውን ይፋ አድርጋለች። እፍታም ሳይቆይ የአልመዳ ጨርቃጨርቅ የአመራር አባልና የማርኬቲንግ ሃላፊ የሆነው ተስፋዬ ገ/እግዚያአብሄር ከሪፖርተር ጋዜጣ ጋር ባደረገው ቆይታ የአልመዳን ሰራተኛ ብዛት ወደ 40,000 (40 ሺህ) እየተጠጋ መሆኑን ገልጿል። ታጋይ ተስፋዬ በእንግሊዝኛ ታትሞ በሚወጣው የአማረ አረጋዊ ጋዜጣ በጥቅምት 10 ቀን 2005 ዓም (ኦክቶበር 18, 2014) እንደገለጸው ከሆነ አልመዳ ጨርቃጨርቅ በሚቀጥለው አመት በአምስት እጥፍ ያድጋል። የማምረት አቅሙም በቀን እስከ 100 ቶን ይደርሳል። አጠቃላይ የኢንቨስትመንት መጠኑም ወደ 8 ቢሊዮን ብር ይደርሳል።

331

እነሆ! የሪፖርተር ዘገባ በከፊል ይሔን ይመስላል፣

"Tesfay Ge. Egziabher, marketing and Sales Manager at Almeda Textile, told the Reporter that the factory has planned to expand five times bigger than what it currently is... The 15 year old Almeda Textile is situated in the Tigray Regional State, some 1,000 km north of the capital. The overall expected investment according to Tesfay, is estimated to be between six and eight billion birr, depending on the marketing fluctuations. By then the total number of employees will reach 40,000 Tesfay said."

አቶ መለስ ለአልመዳ ጨርቃጨርቅና ልብስ ስፌት ፋብሪካ ልዩ ትኩረት የሰጠበት ሁለተኛ ምክንያት የተለያዩ መንግስታዊ ከለላዎች በመጠቀም ለህወሓት የማይነጥፍ የገንዘብ ምንጭ ሆኖ እንዲያገለግል በማሰብ ነው።እንደታዋቂው የስነልቦና ፈላስፋ አብራሀም ማስሎ ትንተና መሰረት ከሰው ልጅ መሰረታዊ ፍላጎቶች ከሆኑት ምግብ፣ መጠለያ እና ጾታዊ ግንኙነት ጋር "ቁብስ" አብሮ የሚሰለፍ ነው። በመሆኑም የሰው ልጅ በህይወት እስካለ ድረስ የአልባሳት ገበያ ፍላጎት አብሮ ይኖራል። ስለዚህም ይህን የማይነጥፍ ገበያ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ መንቀሳቀስ የሚታለፍ አይደለም። ለእለታዊ ኑሮ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች ላይ የሚያተኩር ፋብሪካ የመቆየት እድሉ ሠፊ ነው። አልባሳት ከውሃና ዳቦ ባላነሰ እኳኋን ለህይወት አስፈላጊ ነው። በዚህም ምክንያት የአንድ ህብረተሰብ አመታዊ ምርት ከሚይዘው የፍጆታ እቃዎች በከፍተኛ ዋጋ ከሚጠቃለሉት አንዱ የጨርቃጨርቅ ምርቶች መሆኑ አይቀርም። በተለይ የህብረተሰቡ ኑሮ እየተሻለ ከሔደ ማህበረሰቡ ከሚያገኘው ጠቅላላ ገቢ ውስጥ ለአልባሳት የሚያወጣው እየጨመረ ይሔዳል።

አቶ መለስ ለአልመዳ ጨርቃጨርቅ ልብስ ስፌት ፋብሪካ ልዩ ትኩረት የሰጠበቻ ሶስተኛ ምክንያት ከሌሎች የትዕምት ኩባንያዎች ጋር ተመጋግቦ የማደግ እድሉ ከፍተኛ ስለሆነ ነው። አልመዳ በአንድ በኩል በግብርና ሜካናይዜሽን ላይ እንዲሰማራ ከተደረገው "ህይወት ሜካናይዜሽን" እንደጥጥ ያሉ የአልባሳት ግብዓቶች ይገዛል። በሌላ በኩል በዘመናዊ ንግድ እንዲሰማራ ከተደረገው "ጉና" ምርቶቹን በማቅረብ ገቢውን እንዲያሳድግ ያደርጋል። በዚህም ላይ ሳይወሰን ከትዕምት ኬሚካልና ትራንስፖርት ኢንዱስትሪዎች ጋር በማጣመር ተያይዘው የሚበለጽጉበትን ሁኔታ ይፈጥራል። በመሆኑም "አልመዳ" በራሱ ዘርፍም ሆነ በሌሎች የ ትዕምት ኩባንያዎች መሻሻል የቅንጅት አሰራር እንዲፈጠር አገናኝ ሆኖ የሚያገለግል ነው። ከሁመራ እና ወልቃይት ጥጥ በሰፊው ማምረት ስለሚቻል አልመዳ በቀላሉና ዝቅተኛ ዋጋ ያገኛል። በጥጥ ምርት ላይ የተሰማራው "ህይወት ሜካናይዜሽን" ሰፊ ገበያ በማግኘቱ ምርቱን ለማሳደግ ተግቶ ይሰራል። የአልመዳ ምርቶች ወደ መጨረሻ ተጠቃሚው በጅምላ እና ችርቻሮ የሚያቀርቡት ራሳቸው የ ትዕምት ድርጅቶች ስለሆኑን በአገሪቱ ዋና ዋና ከተሞች መሸጫ ሱቆች ስላላቸው ቀልጣፋ የግብይት ስርዓት ይፈጥራሉ።

አልመዳ ጨርቃጨርቅ ከህወሓት ድርጅቶች ውስጥ ግንባር ቀደም ተዋናይ እንዲሆን ከተወሰነ በሁዋላ ቀጣዩ ጥያቄ "በምን መልኩ ይመስረት?" የሚለው ሆነ። ለዚህ ጥያቄ የተሰጠው

ምላሽ እንደሌሎቹ የህወሓት ኩባንያዎች በህወሓት ነባር ታጋዮች አክሲዮን ባለቤትነት ይጸ… የሚለው ሆነ። ታጋዮች የተመረጡበት መመዘኛ ለብዙ የህወሓት ሰራዊት አባላት ግል… ባይሆንም። አምስት ታጋዮች የአልመዳ ባለቤቶች እንዲሆኑ ተደረገ። እነዚህም የቅርብ ወዳ… የሆነው ፍስሃ ዘሪሁን (መአሲ) ጨምሮ የውብማር አስፋው (የትግራይ ክልል ፕሬዚደን… የነበረው ገብሩ አስራት ባለቤት) ፣ ፀጋ ብርሃን ሀዱሽ ወ/ማሪያም፣ ግደይ ገ/እግዚያብሄር መ… እና ሃይሌ ሊባኖስ ወ/ሚካኤል (የደህንነት ሐላፊ የነበረ) ናቸው። በመጀመሪያዎቹ አመታት የውብማር፣ ፀጋብርሃን እና ሃይለ የአልመዳ የቦርድ አመራር ኮሚቴ አባላት ነበሩ።

ተ.ቁ.	የአልመዳ ጨርቃጨርቅ አክሲዮን ባለቤቶች	የአክሲዮን መጠን	የአንድ አክሲዮን ዋጋ	ጠቅላላ የአክሲዮን ዋጋ
1.	የውብማር አስፋው ኪዳኑ	1,000,000.00	36.00	36,000,000.00
2.	ጸጋብርሃን ሃዱሽ ወ/ማሪያም	1,000,000.00	36.00	36,000,000.00
3.	ሃይሌ ሊባኖስ ወ/ሚካኤል	1,000,000.00	36.00	36,000,000.00
4.	ፍስሃ ዘሪሁን ወልዱ	1,000,000.00	36.00	36,000,000.00
5.	ግደይ ገ/እግዚያብሄር መሸሻ	1,000,000.00	36.00	36,000,000.00
	ድምር			180,000,000.00

ሰንጠረዥ ቁጥር 5: የአልመዳ ጨርቃጨርቅ የመጀመሪያዎቹ አክሲዮን ባለቤቶች

እነዚህ አምስት መስራቾች እያንዳንዳቸው ሰላሳ ስድስት ሚሊዮን ብር አዋጥተው እንደመሰረቱት ተደርጎ የተሰራ ነው። በመጀመሪያዎቹ አካባቢ ታጋዷሊት የውብማር፣ ፀጋብርሃና ሃይሌ ሊባኖስ የቦርድ አባላት እንዲሆኑ ተደርጎ ነበር። የቦርድ ሰብሳቢው ደግሞ ነባሩ የህወሓት ታጋይ አባዲ ዘሙ ሆነ። አባዲ ዘሙ የትግራይ መልሶ ማቋቋም (ሬስት) ከተመሰረተ ጊዜ ጀምሮ ማኔጂንግ ዳይሬክተር በመሆን አገልግሏል። ህወሓት መላው ኢትዮጵያን በቁጥጥር ስር ካዋለ በኋላ ለሶስት አመታት ያህል እመገዘኑ (Government Relief and Rehibilitation Commision) ምክትል ኮሚሽነር በመሆን ሰርቷል። ለጋሽ ሀገራት የሚያደርጉት የእህል እርዳታ በልዩ ልዩ ሁኔታ ወደ ትግራይ እንዲሔድ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል። የኤፈርት ኩባንያ አካል የሆነው ትራንስ

ኢትዮጵያ የእርዳታ እህሉን በሞኖፖሊ ከወደቦች ወደ መሀል አገር እንዲያመላልስ ያመቻቸው እሱ ነው።)

አልመዳ የተመሰረተው በአምስት ታጋዮች ስም በህወሓት ገንዘብ እንደሆነ ቢገለጽም፣ እውነቱ በተቃራኒ ነው። አልመዳ የተቋቋመው በትጥቅ ትግሉ ወቅት ከተሰባሰበ ገንዘብና ንብረት ሳይሆን፣ አቶ መለስ በሰጠው ትዕዛዝ ከንግድ ባንክ በተገኘ ብድር ነው። አልመዳ ጨርቃጨርቅ የተመሰረተው በ470 ሚሊዮን ብር ሲሆን፣ ከዚህ ካፒታል ውስጥ 64% ወይም 300 ሚሊዮን የተገኘው ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ያለመያዣ በተሰጠ ብድር ነው።

(ብድሩ እንዴት ተሰጠ፣ መጨረሻ ላይ ብድሩ ተመለሰ ወይ? አቶ መለስ ምን ውሳኔ ሰጠ? ወዘተ የሚሉትን ጥያቄዎች ምላሽ "የ ትዕምት ፋይናንስ ምንጭ" በሚለው ምዕራፍ ላይ ያገኙታል።)

አቶ መለስ "የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ" በሚለው መጽሃፉ ውስጥ በገጽ 234 ላይ "መንግስት ለአገሌ ብድር ይስጥ ወይስ አይሰጥ ብሎ መወሰን የለበትም። ከጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ አኳያ መንግስት ሊያደርግ የሚገባው በመጀመሪያ ደረጃና በዋነኛነት ኢንዱስትሪው ያሉበትን ችግሮች ቀርፎ በፈጣን እድገት ሂደት የሚገባበትን እቅድ አዘጋጅቶ ተግባራዊ ማድረግ ነው" ብሎ ይናገራል። ይሁን እንጂ እንደዚህ አይነት አቅጣጫዎች አልመዳን ስመሳሰሉ የህወሓት ድርጅቶች የሚሰሩ አይደሉም። እነ አልመዳ ለሚፈልጉት ስራ ባንኩን የመጠየቅ፣ ባንኩ ደግሞ "የብድር ጥያቄው አዋጭነት" የሚሉ ግምገማዎች ሳይካሄድ በአስቸኳይ የመፍቀድ ግዴታ አለበት። በተግባርም የታየው ህወሓት ምንም አይነት የብድር ዋስትና ሳያስይዝ አስጣጡን ፎርማሊቲ ሳያሟላ ብድር መውሰዱ ነው።

ህወሓት በየጊዜው የሚሰበስባቸውን ንብረቶች በቦርድ ሊ/መንበርነት የሚመራው አቶ መለስ ከትግል ጓዶቹ ጋር በመሆን ኩባንያዎች በታጋዮች ስም ከሚያዙ ይልቅ በትዕምት እንዲወረሱ ውሳኔ አሳለፈ። በዚህ ውሳኔ መሰረት በነሃሴ ወር 1988 በተካሄደ ስብሰባ የአልመዳ አክሲዮን ባለቤቶች የሆኑት እነ ተጋዳሊት የውብማር፣ ታጋይ ፀጋብርሃን፣ ግደይ፣ ሃይሌ እና ፍስሃ ሙሴ የነበራቸውን ሼር ለ ትዕምት በስጦታ መልክ እንዲሰጡ ተደረገ። በእያንዳንዳቸው ስም አየር ላይ የነበረው 36 ሚሊዮን ብር በተሰናዳ የወረቀት ፎርማ ተንከረባብቶ ለትዕምት ተሸጋገረ። የአልመዳ አክሲዮን ባለቤቶችም ከግለሰብ ተቀይረው ትዕምት እና ኩባንያዎቹ እንዲሆኑ ተደረገ።

በመሆን ትዕምት አጠቃላይ ድርሻውን 97% በማድረግ የተቀረውን ለጉና፣ ህይወት ሜካናይዜሽን፣ ሼባ የቆዳ ፋብሪካ እና ታጋይ አባዲ ዘሙ እንዲከፋፈል ተደረገ። በውሳኔው መሰረት የእልመዳ ጨርቃጨርቅ ዝርዝር የአክሲዮኑ ባለቤቶች እና ድርሻቸው ደግሞ በሰንጠረዥ ቁጥር 6 እንደሚታየው ሆነ።

ተ.ቁ	የአክሲዮን ባለቤቶች	የአክሲዮን መጠን	የአንድ አክሲዮን ዋጋ	ጠቅላ የአክሲዮን ዋጋ
1.	ትዕምት	8,729,999.00	20.00	174,599,980.00
2.	ጉና ትሬዲንግ	90,000.00	20.00	1,800,000.00
3.	ህይወት የጥበርና ሜካናይዜሽን	90,000.00	20.00	1,800,000.00
4.	ሼባ የቆዳ ፋብሪካ	90,000.00	20.00	1,800,000.00
5.	አባዲ ዘሙ	1.00	20.00	20.00
			ድምር	180,000,000.00

ሰንጠረዥ ቁጥር 6: የአክሲዮን ሽግግር ከተደረገ በኋላ የእልመዳ ጨርቃጨርቅ አክሲዮን ባለቤቶች

My text!

በነገራችን ላይ እልመዳ ሲቋቋም የነበሩ ታጋዮች የአክሲዮን መጠን፣..እልመዳ ከንግድ ባንክ የተበረደውን ብድርና የመጨረሻውን የአክሲዮን ባለቤቶች ድርሻ በተመለከተ መሰረታዊ የሂሳብ ስሌት ለሰራ ሰው በቀላሉ አንድ ነገር መመልከት ይችላል። ይኸውም ቀድሞ ባለቤቶች የነበሩ ታጋዮች አክሰዮን መጠን ድምር ውጤት (180 ሚሊዮን ብር) እና መጨረሻ ላይ ባለቤት የሆኑት (ትዕምት፣ ጉና፣ ህይወት፣ ሼባ፣ እና አባዲ) አክሲዮን ድምር ውጤት (180 ሚልዮን ብር) እኩል ነው። ይሄ መጠን ደግሞ እልመዳ ጨርቃጨርቅ ገና ሲመሰረት ለንግድ ባንክ "በትጥቅ ትግሉ ወቅት ያሰባሰበው" በማለት ለመበደር ካሳየው ገንዘብ ጋር እኩል ነው። ታዲያ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የሰጠው 300 ሚልዮን ብር (ሳይጠጋጋ በትክልል ለማስቀመጥ 299,044,435.00) የትኛው ቢርሙዳ ዋጠው? ከንግድ ባንክ የተገኘው ብድር ወዴት ሄደ? ...እልመዳ ጨርቃጨርቅን ለመመስረት የሚያስፈልገው ካፒታል 180 ሚሊዮን ብር ሆኖ ሲያበቃ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ

My text!

ለምን 300 ሚሊዮን ብር ተወሰደ... ለሌሎች የህወሓት እህት ድርጅቶች ለምን በተመሳሳይ አልተፈቀደም?

በአጭሩ ትዕምት ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በአልመዳ ጨርቃጨርቅ ስም የወሰደው 300 ሚሊዮን ብር የተጠቀመው ሌሎች ኩባንያዎችን ለማቋቋም ነበር። አልመዳ በብዙ የትዕምት ድርጅቶች ውስጥ የአክሲዮን ባለቤት የሆነበትም ምክንያት ገንዘቡን ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ስላገኘ ነው። ለምሳሌ ያህል አልመዳ የተሰፉ ልብሶች ፋብሪካ የተመሰረተበት 400 ሺህ ብር በሙሉ በአልመዳ ጨርቃጨርቅ የተሸፈነ ነው። ከዚህም በተጨማሪ በህይወት የእርሻ ሜካናይዜሽን ውስጥ 250ሺህ ብር በአፍሪካ ኢንሹራንስ አክሲዮን ማህበር 6 ሚሊዮን ብር፣ በሼባ የቆዳ ፋብሪካ አክሲዮን ማህበር 400ሺህ ብር፣ በጉና የንግድ ስራዎች ድርጅት 100ሺህ ብር፣ በአዲስ ኢንጂነሪንግ ኮንሰልታንሲ ኢ.ማ. 40ሺህ ብር ሼር በመግዛት ኩባንያዎቹ እንዲመሰረቱ አድርጓል። በመሆኑም አልመዳ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በወሰደው ገንዘብ የትዕምት ቦርድ ሊቀመንበር ለሆኑት አቶ መለስ ለወጠነው ስትራቴጂያዊ ኢንዱስትሪዎች የማቋቋም አላማ ከፍተኛ አስተዋጽዖ አድርጓል። (አልመዳ አክሲዮን በማዋጣት የመሠረታቸው የኤፈርት ኢንዱስትሪዎች፣ የንግድና አገልግሎት ተቋማት በዚህ ምዕራፍ መጨረሻ ቀርበዋል።)

በዚህ መልኩ የተደራጀው አልመዳ ጨርቃጨርቅ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ባገኘው ገንዘብ በመስፋፋቱ ምክንያት ከራሱ አልፎ ለጨርቃጨርቅ ምርት ግብዓት የሚሆኑ ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን የሚተኩ ኢንዱስትሪዎች በትግራይ እንዲያብቡ አድርጓል። በተለይም ጨርቅና ልብስ ስፌት የሚያስፈልጉ ኬሚካሎችና ሌሎች ግብዓቶች የሚያመርቱ ኢንዱስትሪዎች እንዲስፋፉ አድርጓል። ከዚህ አንጻር የትዕምት ንብረት የሆነ ብሩክ ኬሚካል አክሲዮን ማህበር በምሳሌነት የሚጠቀስ ነው። ፋብሪካው የሚያመርተው ኬሚካል ከህይወት ሜካናይዜሽን የተገኘው ጥጥ ወደ ክር እና ብትን ጨርቅ ለመቀየር ያገለግላል። በዚህም ምክንያት አልመዳ በጥጥ የተሰሩ ክሮች (Cotton Fabric) በኢትዮጵያ ገበያ ውስጥ ከማቅረብ አንጻር ተወዳዳሪ የለውም። ይህንን የገበያ የበላይነት ጠብቆ ለማቆየት እንዲረዳ ማንኛውም "ጥሬ ጥጥ" ከኢትዮጵያ እንዳይወጣ በአቶ መለስ ትዕዛዝ እንዲታገድ ተደርጎ ነበር። በእንግሊዝኛ የሚታተመው አዲስ ፎቹን ጋዜጣ በጥቅምት 09 ቀን 2002 ዓም "Government Bans Export of Raw Cotton" በማለት ሁኔታውን ዘግቦታል።

My text:

አቶ መለስ አልመዳ ጨርቃጨርቅ ላይ ትኩረት እንዲሰጠው የፈለገበት ሌላኛው ምክንያት ለትዕምት ድርጅቶች የውጭ ምንዛሪ የሚያስገኝ ዘርፍ እንደሆነ በማስላቱ ነበር። የውጭ ምንዛሬ ለትዕምት እድገት ቁልፍ ሚና የሚጫወት መሆኑ ይታወቃል። ስለሆነም በኤፈርት ውስጥ የውጭ ምንዛሬ የከምችት መጠን ከፍ ሲል በውጭ ምንዛሪ የሚገቡ ዕቃዎች ላይ እከል አይገጥምም የሚል ታሳቢ ወስዶ ነበር።

አልመዳ ጨርቃጨርቅ በገበያ ብቸኛ ተወዳዳሪ እንዲሆን ከተወሰዱት እርምጃዎች መካከል በመንግስት የተያዙ እና ወደ ግል እንዲዞሩ የተደረጉ የጨርቃጨርቅ ፋብሪካዎች እንዲዳከሙና ከገበያ እንዲወጡ ማድረግ ነው። እነዚህን የመንግስት ተቋማት አቅም የሌላቸው ባለሁብቶች እንዲገዙ በማድረግ ድርጅቶቹን መግደል አንደኛው ስትራቴጂ ነው። በተለይም በኢትዮጵያ ህዝብ ዘንድ ታዋቂ የነበሩት አቃቂ፣ አርባምንጭ፣ አዋሳ፣ ድሬዳዋ ጨርቃጨርቅን የመሳሰሉ ፋብሪካዎች እንዲዳከሙ በመደረጉ የሰራተኞች የስራ ዋስትናም ጥያቄ ውስጥ ገብቷል። ሪፖርተር ጋዜጣ መጋቢት 21 ቀን 2008 ዓ.ም. በቢዝነስ እና ኢኮኖሚ አምዱ የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማህበራት ኮንፌደሬሽን ፕሬዝዳንት አቶ ካሳሁን ፎሎን አቅርቧል። ሪፖርተር ወደ ግል የተዛወሩ የጨርቃጨርቅ ፋብሪካዎች እየተዳከሙ ነው" በሚል ርዕስ የሚከተለውን አስነብቧል።

"የአዋሳ፣ አርባምንጭ፣ የድሬዳዋ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካዎችና ቢኤም ኢትዮጵያ የልብስ ስፌትና ጨርቃጨርቅ አክሲዮን ማህበር ከመንግስት ወደ ግል ከተዘዋወሩበት ጊዜ አንስቶ በታሰበው ደረጃ ውጤት እያመጡ አይደሉም።... እነዚህን የጨርቃጨርቅ ፋብሪካዎች የገዙት ባለሀብቶች ተቋማቱ ብቁ፣ ተወዳዳሪና ውጤታማ ሆኖም ከመንግስት ጋር በገቡት ውል መሰረት የተቋማቱን አሠራር ከማሻሻልና ሠራተኞቹን ዘላቂ የስራ ዋስትና ጥቅማ ጥቅሞች ከማክበር ይልቅ፣ በመለዋወጫ መሳሪያዎች እጦትና በጥሬ ዕቃ አቅርቦት እጥረት ምክንያት የፋብሪካዎቹ የስራ እንቅስቃሴ ከቀን ወደ ቀን እየተዳከመ መሆኑ ታውቋል።

ከጋራ ድል ይልቅ ሁልጊዜም ሌሎችን በመድፈቅ ማሸነፍን እንደ ስትራቴጂ የሚከተለው ትዕምት ትላልቆቹንና ፋብሪካዎቹ የተተከሉበት ማህበረሰብ ልዩ ትገዛታ የፈጠሩትን ድርጅቶች በማጥፋት ላይ ይገኛል። እውነት ለመናገር ለድሬ፣ አዋሳ፣ አርባምንጭ፣ ባህርዳርና አቃቂ ነዋሪዎች የጨርቃጨርቅ ፋብሪካዎቹ ትዝታ የሚረሳ አይደለም። እነዚህ ነዋሪዎች ህወሓት በሚከተለው ራስ ወዳድነት በተለበሰ ምቀኝነት እንደሆነ ስለሚያውቁ ለፓርቲውም ሆነ ለትዕምት በጎ አመለካከት

የላቸውም። ህወሓት ስልጣኑን በመጠቀም የአልመዳ ጨርቃጨርቅ ጥቅምን ለማስጠበቅ ሌሎችን ቢቀድ መንገድ እንደሚጎዳ ይገልፃሉ። የታሪክ አጋጣሚ ሆኖ የኢቃቂ፣ አርባምንጭ እና ድሬዳዋ ጨርቃጨርቅ ሠራተኞችን በአዳራሽ ውስጥ የማናገር እድል አጋጥሞኝ ነበር። የሦስቱም ፋብሪካ ሠራተኞች የተመካከሩ ይመስል ቋንቋቸው አንድ አይነት ነበር። ለመናገር እድል ያገኘው የፋብሪካ ሠራተኛ ተናግሮ ሲጨርስ አንኳን የሚያጨበጭቡበት ስታልይ ተመሳሳይ ነው። ከሁሉም የሚገርመው በላይ የተጠቀሱት ፋብሪካዎች ዘበኛ እና ጽዳት ሰራተኞች ሳይቀሩ ስለ አልመዳ ጨርቃጨርቅ ያላቸው መረጃ የአለት ተአለተ ነው። ...በአልመዳ ጨርቃጨርቅ ተቀጥረው የሚሰሩት የትግራይ ተወላጆች ብቻ መሆናቸው ...የሠራተኛው የደሞዝ ስኬል ከአነሱ በሦስት እጥፍ እንደሚበልጥ-የአልመዳ ሠራተኞች የስራ ዋስትና እንድሚያስጨንቃቸው... የሚያገኙት ጥቅማ ጥቅም ከወርሀዊ ደሞዛቸው በመሆኑ ያለድካም ውጤታማ ስራ እንደሚሰራ ...ወዘተ ጠንቅቀው ያውቃሉ። በንግግራቸው መጨረሻ "አልመዳ እስኪለማ ሊላው..." የሚል የቁጭት መፈከር ያሠማሉ።

My text!

በነገራችን ላይ ከላይ የተጠቀሱትም ሆነ በመላው ኢትዮጵያ የሚገኙ የፋብሪካ ሠራተኞች ለህወሓት/ኢህአዴግ ያላቸውን ጥላቻ እንደ ቡድን ለመግለፅ የሚችላቸው የለም። የምርጫ ካሮጆ ተጭበርብሮም ቢሆን በየትኛውም የፋብሪካ አካባቢ ኢህአዴግ አሸንፎ አያውቅም። በዚህም ምክንያት በኢህአዴግ ቢሮ እና ደህንነት ጽ/ቤት ቅንጅት ከኮሮጆ ማጭበርበር በላይ የሆነ ድርጊት እንዲፈፀም ተደርጓል።

በአጠቃላይ መልኩ አልመዳ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ የኢትዮጵያን የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ እንቅሲቃሽ ሞተር ሆኖ እንዲያገለግል የተቀየሰ ነው። ከሃገር ውስጥ ገበያ አንጻር ብቻ ቢታይ 90 ሚሊዮን ህዝብ ያላት ኢትዮጵያ ሰፊ ገበያ መሆን ትችላለች። ምርታማነትን ለማሻሻል ቀን ከሌት የሚተጋው ህወሓት መንግስታዊ ከለላን በመጠቀም የአልመዳ ምርቶችን ወደአለም ገበያ አውጥቶ ለመወዳደር የሚቸግረው አይሆንም። የአልመዳ ሰራተኞች ለፓርቲያቸው እንደሚያገለግሉ ተደርጎ ዘወትር ስለሚሰበኩ ስራቸውን በአብዮታዊ ቁርጠኝነት የሚሰሩ ናቸው። ታጋይ ሰራተኞቹ የአልመዳ ንብረት እንደራሳቸው ንብረት እንዲቆጥሩ ስለተደረገ ለነገ የሚሰስቱት ጉልበት የላቸውም። አልመዳ በሚያዘጋጀው ስልጠና ላይ በትጋት የሚሳተፉ በመሆናቸው ለስራው የሚረዳ መለስተና እውቀቶችን ለመጨመር የሚቸገሩ አይደለም። በዛ ላይ በኢትዮጵያ ሌሎች የማኑፋክቸሪንግ ድርጅቶች ውስጥ ተቀጥረው ከሚሰሩ ሰራተኞች የደሞዛቸው መጠን በአማካይ

ከሁለት እና ሶስት እጥፍ በመሆኑ ምክንያት ታታሪነታቸው እጅግ ከፍተኛ ይሆናል። ይህም ምርታማነታቸውን ለማሳደግ አገልግሏቸዋል። እነዚህን መሰረታዊ ሁኔታዎች በመሟላታቸው ምክንያት አልመዳ ጨርቃጨርቅ ከሃገር ውስጥ ገበያ ተሻግሮ በአለም ገበያ ሰብሮ የሚገባበት ሁኔታ ይፈጠራል። ከቻይና፣ ህንድና፣ ጀርመን ኩባንያዎች ጋር የፈጠረው ጥምረት ገበያውን ሰብሮ ለመግባት የቀለለ መረማመጃ ሆኖ እንዲያገለግለው አድርጓል። በሂደትም የተጠናከረ የአለም ገበያ መረብ ለመዘርጋት መደላደል ፈጥሮለታል።

አቶ መለስ አልመዳ ጨርቃጨርቅ የአልባሳት ኢንዱስትሪውን እንዲመራ የተለዩ ስትራቴጂዎችን ቀይሶ ወደተግባር እንዲመነዘሩ አድርጓል። የመጀመሪያው አልመዳ የሚጠቀምባቸውን ጥሬ እቃዎች በዙሪያው ከሚገኙ አካባቢዎች ማድረግ ነበር። በተለይም በጥጥ ምርታቸው የሚታወቁትን የቀድሞ ትግራይ የማታስተዳድራቸውን ቦታዎች ወደትግራይ ማጠቃለል ቅድሚያ የሚሰጠው ተግባር ነበር። ለምሳሌ እንደወልቃይት እና ሁመራ ያሉ ቦታዎች በትግራይ ክልል እንዲጠቃለሉ የተወሰነው ህወሓት የትጥቅ ትግል ከጀመረ እለት አንስቶ ነበር። በየካቲት ወር 1968 አም የወጣው የህወሓት ማኒፌስቶ በመቅድሙ ላይ "*የትግራይ መሬት በደቡብ አላውሃ፣ በሰሜን መረብ ሲያካልሉት፣ በምዕራብ ደግሞ ወልቃይትንና ጸለምትን ያጠቃልላል*" በማለት በግልጽ አስቀምጧል። በመሆኑም አልመዳ ጨርቃጨርቅ ከወልቃይት፣ ጸለምትና ሁመራ በዘመናዊ መንገድ የሚያመረቱትን የጥጥ ምርቶች በመጠቀም ክር ማምረት ቻለ። የተመረተው ክር በቀጥታ ከመሸጥ ይልቅ ብትን ጨርቆችን የሚመረትበት ፋብሪካ ተቋቋመ። ለጨርቃጨርቅ ፋብሪካው የሚያስፈልጉ የተራቀቁ ቴክኖሎጂዎችን ከቀረጥና ነጻ በሆነ መንገድ ከውጭ እንዲገቡ ተደረገ። በማስከተልም ብትን ጨርቆቹን ወደተሰፉ ልብሶች የሚቀየርበት ዘመናዊ ፋብሪካ እንዲቋቋም ተደረገ። እዚህ ደረጃ እንደደረሰ አቶ መለስ ወደገበያ የሚገባበትን ሌላ እቅድ ነደፈ።

በመጀመሪያዎቹ አካባቢ የተቀየሰው ስትራቴጂ በአገር ውስጥ አስተማማኝ ገበያ እንዲኖረው ማድረግ ሆነ። ለዚህም እንዲረዳ ወደሃገር ውስጥ የሚገቡ ብትን ጨርቆች እና አልባሳት ላይ ከፍተኛ ቀረጥ ተጣለ። ይህ የተደረገው የሃገር ውስጥ ዋጋቸው ከፍ ስለሚል እና አብዛኛው ኢትዮጵያዊ አቅም በላይ ስለሚሆን ገበያቸው ይቀንሳል በሚል ነበር። በተጨማሪ ሌሎች የተሰፉ ልብስ ፋብሪካዎች ብትን ጨርቆችን ከውጭ ከማምጣት ይልቅ ከአልመዳ የብትን ጨርቅ ገዝተው ለመስራት ይችላሉ የሚል ታሳቢ እንዲወሰድ ተደርጎ ነበር። ይህም ሆኖ፣ አልመዳ

የሚያመርታቸው ብት ፣ጨርቆችና የተሰፉ ልብሶች ጥራት የወረደ በመሆኑ ፈላጊ አጡ። ያገኙትን ከለላ ተጠቅመው ዋጋ በመቀነስ ወደገበያው እንዲገቡ ቢደረግም የሚፈልጋቸው ጠፋ። በአልመዳ የተመረተውን ብትን ጨርቅ ገዝተው ወደ አልባሳት የሚቀይሩ ድርጅቶችም በተፈለገው መልኩ ፍቃደኛ ሳይሆኑ ቀሩ። በዚህም ምክንያት አልመዳ መውደቅ ጀመረ። አቶ መለስ ለአልመዳ የቀየሰው ከውጭ የሚወጡ ምርቶችን መተካት (Import Substitution) መሰረት ያደረገ እንቅስቃሴ ድርጅቱን ወደኪሳራ አመራው። የአልመዳ ቆውደቅ እርሱን የሚመግቡት የህወሓት ጉብረቶ የሆኑ እንደ ህይወት የግብርና ሜካናይዜሽን አይነት ኩባንያዎች ተያይዘው ማሽቆልቆል ጀመሩ።

My text!

አልመዳ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ የበራበት ቢጫ መብራት በህወሓት ውስጥ በግላጭ መነጋገሪያ ሆነ። በፓርቲው ጉባዔ እና ማዕከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ ቅድሚያ አጀንዳ ሆኖ መቅረብ ጀመረ። እሳት የሚተፉት የህወሓት ታጋዮች "የሰውእቶች ደምና አጥንት የከሰከሱለት ውጤት አፈር በላ" የሚል ቅሬታ ማቅረብ ጀመሩ። አቶ መለስ በየጉባዔው "ጭቃዎች፣ ገለባዎች፣ አሸሀ አመኬላዎች፣ የጥፋት መልዕክተኞች፣ የትምክህት ጀሌዎች" እያለ ጥንብ ርኩሳቸውን የሚያውጣቸው እነ ስየ አብርሃ እና ገብሩ አስራት ስማቸው እየተጠራ "ማሩን" መባል ተጀመረ። ቀስ በቀስ ካድሬዎች የቀድሞ የህወሓት መሪዎቻቸውን በማወደስ " የቀድሞ ስርዓት ናፋቂ" መሆናቸው አቶ መለስና ተከታዮቹን አስደነገጠ። ውትሮም ቢሆን የቀድሞው ታጋይ እንጃ ተብሎ በተሠየሙት አመራሮች የተሻለ ተቀባይነት ስለነበራቸው ቢናፍቁ የሚገርም አልነበረም። የካድሬውን አእምሮ ጨምድዶ የያዘው "የትግራይ የበላይነት" በግላጭ የተገበሩ በዚህም በኩራት የሚናገር በመሆናቸው ምኞቱ ከባዶ የተነሳ አይደለም። ምንም እንኳን በሁለቱ መካከል ልዩነት ባይኖርም!

እያደር አልመዳ የገባበትን እጣብቂኝ በፋብሪካው ተቀጥረው የሚሰሩ በሺዎች የሚጠጉ "በአብዮታዊ ዲሲፕሊን" ተጠፍንገው የተያዙ ታጋዮች የታሰሩበት ገመድ መፍታት ጀመሩ። የቀድሞ ታጋዮች ጆሮ ደረሰ። ቀድሞም ከትግል በኋላ ኑሮ "ለአንዳንዶች ሁመራ ለሌሎች አስመራ" ሆኗል ብለው በመናገር ቅሬታ የቋጠሩት የቀድሞ ታጋዮች ውስጣዊ እመቃ ማይደራጀት ጀመሩ። በሚጠራው ስብሰባ ሁሉ በንዴት እና ቁጣ መንፈስ መናገር ቀጠሉ። በወቅቱ ቁጣውን ለማብረድ አቦይ ስብሃት ነጋ የሚመራው የ ትዕምት አመራር ቡድን ላብ አደር ታጋዮችን የጠራው ስብሰባ በተቃውሞ ተናጠ። ያለውጤትም ተበተነ። በማስከተል ከአቦይ ስብሃት በኋላ የተላኩትው ወ/ሮ

እዜብ መስፍን ችግሩ በአጭር ጊዜ ለመፍታት እሷና ባለቤቷ ቀን ከሌት እየሰሩ መሆኑን ትናገራለች። ላብአደር ታጋዮች ችግሩ ስር-ነቀል በሆነ መልኩ እንዲፈታ ከፈለጉ ጥቂት ወራት እንዲሰጧት ትማጸናለች። አቦይን "በናፓርቲስት" ብለው ያባረሩት ታጋዮች አመቢታቸውን በማያቋርጥ ጭብጨባና ብሩህ ተስፋ ሸኟት።

በህወሓት ውስጥ አስቀድሞ የሚመጣን አደጋ ለማሸተት የመቻል ተሠጥኦ ያለው አቶ መለስ በይፋ "እልመዳን እናድግ" የሚል ፕሮጀክት ይቀረጻል። የመጀመሪያ ትኩረቱም የመንግስት ተቋማትና የልማት ድርጅቶች ይሆናሉ። ከዚህም በተጨማሪ እልመዳ የሚያመርታቸውን ከሮችና ብትን ጨርቆች የሚጠቀሙበት ፔትሮ ኬሚካል ከቀረጥ ነጻ እንዲገቡ ይደረጋል። በኬሚካል ማምረት ላይ የተሰማሩት ሌሎች የትዕምት ኩባንያዎች ለእልመዳ ልዩ ትኩረት እንዲሰጡ አቅጣጫ ይቀመጣል። ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው ብሩክ ኬሚካል የተባለው የኤፈርት ኩባንያ ነው። ብሩክ ኬሚካል ሲመሠረት እልመዳ ጨርቃጨርቅ የአክሲዮን ባለቤት ነበር። በሰንጠረዥ ቁጥር 7 እንደተመለከተው ብሩክ ኬሚካልን ለማቋቋም 200ሺህ ብር ያዋጣው እልመዳ ጨርቃጨርቅ ነው።

ብሩክ ኬሚካል አክሲዮን ማህበር

ተ.ቁ	የአክሲዮን ባለቤቶች	የአክሲዮን መጠን	የአንድ አክሲዮን ዋጋ	ጠቅላላ የአክሲዮን ዋጋ
1.	ትዕምት	19,399	1,000.00	19,399,000.00
2.	እልመዳ ጨርቃጨርቅ	200	1,000.00	200,000.00
3.	ሜጋኔት ኮርፖሬሽን	200	1,000.00	200,000.00
4.	ሸበ የቆዳ ፋብሪካ	200	1,000.00	200,000.00
5.	አባዲ ዘሙ	1	1,000.00	1000.00

ሰንጠረዥ ቁጥር 7፡ የብሩክ ኬሚካል ኢ.ማ. አክሲዮን ባለቤቶች

መቀመጫውን መቀሌ ያደረገው ብሩክ ኬሚካል የተለያዩ ምርቶችን ያመርታል። ከእነዚህም ውስጥ ኮስቲክ ሶዳ፣ ሃይድሮክሎሪክ አሲድ፣ ክሎሪን፣ ጨው፣ ሃይፖክሎሬት እና የመሳሰሉት ለሃገር ውስጥና ለውጭ ሽያጭ የሚዉሉ ያመርታል። ብሩክ ኬሚካል በመጀመሪያ

የተመሰረተው በአምስት ነባር የህወሓት ታጋዮች ስም ነው። እነዚህም ተከላይ ተስፋዬ እንግዳ፣ በርሄ ሃይለ ዘርፉ፣ ፍሬስላሰ ተ/ሚካኤል ተክለጽዮን፣ ኢሳያስ ደስታ ሃይሉ፣ ግደይ ገ/እግዜር መሸ ናቸው። እያንዳንዳቸው በተናጥል 3 ሚሊዮን ብር እንዲያዋጡ ተደርጎ የተመሰረተ ነው። ግደይ ገ/እግዜአብሄር ከዚህ በተጨማሪ የአልመዳ ጨርቃጨርቅ መስራች አባል ነው። የድርጅቱ ቦርድ ሊቀመንበር በርሄ ሃይሉ ሲሆን፣ ስራአስኪያጁ ፍሬስላሴ ተክለሚካኤል ይባላል። በነሃሴ 21 1988 በተካሄደው ስብሰባ በአምስቱ ነባር መስራቾች የነበራቸውን ሼር ለኤፈርት በስጦታ መልክ እንዲሰጡ ተደረገ። ከመተላለፉ ጋር ተያይዞ የብሩክ ኬሚካል አክሲዮን ማህበር ካፒታል ወደ 20 ሚሊዮን ብር እንዲያድግ ተደረገ።

በያዝነው አመት የመጀመሪያ ወራት ብሩክ ኬሚካል ተጨማሪ አዳዲስ ግንባታዎችን እየሰራ መሆኑን ይፋ አድርጓል። ይህ በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የሆነ የኬሚካል ማምረቻ ኢንዱስትሪ በ5ቢሊዮን ብር ሊገነባ ነው። ግንባታውን የሚያከናውነው የቻይናው CEC ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን ሲሆን ሱር ኮንስትራክሽን እና መስፍን ኢንዱስትሪያል ኢንጂነሪንግ በንዑስ ተቋራጭነት ይሳተፋሉ። ግንባታው የሚካሄደው ከመቀሌ በስተምስራቅ 25ኪሜ ርቀት ላይ ሲሆን ኢንዱስትሪው በዋናኝነት 60ሺህ ቶን ፒቪሲ ሬዞን እና 50ሺህ ኮስቲክ ሶዳ እና ሌሎች ኬሚካሎችን ያመርታል።

My

ወደ ቀደመው ጉዳያችን ስንመለስ ህወሓትና አቶ መለስ አልመዳ በተለያዩ መንግስታዊ መመሪያዎች ታጅቦ የህዝብን ሃብት በቀጥታ እና በተዘዋዋሪ መንገድ የሚዘርፍበትን ሁኔታ አመቻቹ። የአልመዳ ምርቶች ጋር በመንግስት ተቋማት የሚሰራበትን ሁኔታ ወደ መመልከት ተገባ። በምርቱ ጥራት መወዳደር አቅቶትም በመንግስት ድጎማ (የታሪፍ ከለላ፣ የታክስ ነጻ እድል፣ ኮንትሮባንድ፣ ወዘተ) ተንጠልጥሎ የነበረው አልመዳ የትኛው የመንግስት መስሪያ ቤት ላይ ቢከፋፈል የህዝብን ገንዘብ ተቀራምቶ ሊያንሰራራ እንደሚችል ዝርዝር ጥናት ተካሄደ። ትልቅ ገቢ ሊያመጡ የሚችሉ ሚኒስትር መስሪያ ቤቶች እና የልማት ድርጅቶች እንዲለዩ ተደረገ።

አልመዳን ለማዳን ከሚደረገው ርብርብ አኳያ ቅድሚያ እንዲተኮርበት የተመረጠ መስሪያ ቤት "የሃገር መከላከያ ሚኒስቴር" ሆነ። መስሪያ ቤቱ አይን እንዲጣልበት ያደረጉ የተለያዩ ምክንያቶች አሉ። የመጀመሪያው በሚኒስቴር መስሪያ ቤት ውስጥ በርካታ የሰው ሃይል በመያዝ ግንባር ቀደም የሆነ ተቋም ነው። በምድር ሃይል፣ በአየር ሃይል፣ በልዩ ሃይልና ሌሎች ወታደራዊ

My text!

ተቋማት ተቀጥረው የሚሰሩ ወታደርና ሲቪሎች ከ400ሺህ በላይ ናቸው። ከባለማዕረግ ጀምሮ እስከ ተራ ወታደር ያለው የሰራዊት አባል ብቻ 350ሺህ ያህል ይደርሳል። በዚያ ላይ በየአመቱ ከ10ሺህ እስከ 20ሺህ ምልምል ወታደሮች በየማሰልጠኛው የሚገቡበት ሁኔታ ስለሚኖር የሰራዊቱ ቁጥር እየጨመረ እንጂ እየቀነሰ የሚሄድ አይደለም። ከመከላከያ ሚኒስቴር ጋር ተያይዞ በአንድ ላይ ትኩረት የተሠጠው የፌደራል፣ ክልልና አዲስ አበባ የፖሊስ ሠራዊት ነው። ርግጥም ከ100ሺህ በላይ የሆኑትን የፖሊስ ሠራዊት ከመከላከያ ጋር አቀናጅቶ መመልከት በእነ አቶ መለስ አይን ትክክለኛ ቦታ ነው።

የ"አልመዳን እናድን" ፕሮጀክት በመከላከያ ሚኒስቴር ለመተግበር ቀላል የሚሆንበት ሌላኛው ምክንያት ወታደራዊ ተቋም በመሆኑ ከላይ የወረደ ትዕዛዝ ላለመቀበል የሚያከራክር አይደለም። የሰራዊቱ የበላይ አመራሮች ህይወታቸውን ሙሉ የተጠመቁት "አብዮታዊ ዴሞክራሲ" የሚባል ማዕከላዊነት የምያጠብቅ በመሆኑ ለጥያቄ ከታች ወደላይ ክፍት አይደለም። ከፍተኛ የጦር መኮንጅኖቹም ቢሆኑ የሚታዘዙት ቁልፍ ስልጣኑን በጨበጠው አቶ መለስ ስለነበር ሰውየው ለሚገኝ ሌላ ፈላጭ ቆራጭ አድርገው መኖር ግዴታቸው ነበር። እውቀት አልባዎቹ ፈላጭ ቆራጭ መኮንኖች ለአንድ ከበላያቸው ለአቶ መለስ ያለው ታማኝነት ትንሽ ከተጓደለ መገኛ ቦታው የት እንደሆነ ስለሚያውቅ ትዕዛዙን ያለአንዳች ማንገራገር መቀበል እንዳለበት ጠንቀቆ ያውቃል። በአጠቃላይ መልኩ የጦር መኮንኖቹ ተጠሪነት እና ተጠያቂነት ለ"ድርጅቱ" ስለሆነ ውሳኔያቸው ለስልጣን ላበቃቸው አካል መሆኑ አይቀርም።

እነዚህ የጦር አለቆች እና ፖሊስ አዛዦች ለ"አልመዳን እናድን" ፕሮጀክቶች ብሎም ትዕምትን ለመደገፍ ቁርጠኝነት የሚንቀሳቀሱባቸው ሌሎች ፖለቲካዊ ምክንያቶች አሉ። እነዚህ አጠቃላይ ምክንያቶች በሌላ ማስታወሻ የሚዳሰሱ በመሆኑ አልመዳን ለመታደግ የተወሰዱ እርምጃዎች ላይ እናተኩር። የህወሓት ኩባንያዎች በተነሱ ቁጥር ሮሮውን የሚያሰማው ኢትዮጵያዊ ነጋዴና የኢንዱስትሪ ባለቤት የመከላከያ ጦር መኮንኖች የሚያነሳ በመሆኑ ለብቻው ማየት ጠቃሚ ይሆናል። ርግጥም የጦር አለቆቹ ለእነዚህ ኩባንያዎች የሚያደርጉትን እንክብካቤና አድሎ ገለጥ አድርጎ ማሳየት በጉዳዩ ላይ የተሻለ ግልጸኝነት ለመፍጠር ያስችላል።

My text!

አቶ መለስ አልመዳን ከማዳን አንጻር በመከላከያ ውስጥ የወሰደው የመጀመሪያ እርምጃ የዕድም መመሪያዎች በአዲስ መቀየር ነበር። ከዚህም ቀደም ለሰራዊቱ የሚሆኑ ሬንጀሮች፣ ሸሚዞች፣ እንሶላ፣ ብርድልብስና ሌሎች፣ ሎጂስቲክሶች ከውጭ ኢምፖርት ይደረጉ ነበር። በመሆኑም አልመዳ ሊያመርታቸው የሚችሉትን ምርቶች በመለየት ከውጭ እንዳይገቡ ማድረግ ሆነ። ይህንን ውሳኔ ተከትሎ ሬንጀር ጨምሮ ሌሎች ሎጂስቲክሶች አልመዳ በሰፊው እንዲያመርት ተደረገ። በማስከተል ከምልምል ወታደር ማሰልጠኛ ማዕከላት፣ ኮሌጆች እንዲሁም ከፍተኛ መኮንኖች ውጭ የሚጠቀሙባቸው ሎጂስቲክሶች መከላከያ ቀጥታ የሚያመርትበትን ሁኔታ እንዲፈጠር ተደረገ። ወታደሮቹም በቀጥታ ከመከላከያ የሚወስዱበትን ሁኔታ በማስቀረት በግለሰብ ደረጃ ከአልመዳ ጨርቃጨርቅ የሚገዙበት ሁኔታ ተመቻቸ። ሰራዊቱ በስድስት ወር አንድ ጊዜ ሬንጀር፣ ሸሚዝ፣ እንሶላ፣ ብርድልብስ መግዛት እንደሚኖርበት መመሪያ እንዲወጣ ተደረገ። የሎጂስቲክስ ዋና መምሪያ ባወጣው በጀት መሰረት ለግማሽ አመት የሚያስፈልገው የተናጠል ሰራዊት ገንዘብ 500 ብር (ለሬንጀር ግዢ ብቻ 150 ብር) እንዲመደብ ተደረገ።

በዚህ እርምጃ መሰረት አልመዳ ጨርቃጨርቅ ከ200ሺህ በላይ ለሆኑት የመከላከያ አባላት የሚቀርበው ሎጂስቲክስ ከፌዴራል መንግስቱ ከ700 ሚሊዮን ብር ያህል በተዘዋዋሪ እንዲወስድ ተደረገ። ይህ ገንዘብ ከፌዴራል መንግስቱ አጠቃላይ በጀት ከነበረው 34.4 ቢሊዮን ብር (1998 ዓም) ሁለት በመቶ ድርሻ ይሸፍናል። አልመዳ ይህንን እድል እንዲጠቀም በመደረጉ ምክንያት ከአመታዊ ምርቱ 40% የሚያክለውን ያለምንም ተቀናቃኝ ለመከላከያ ማቅረብ አስቻለው።

ለአልመዳ የገበያ እድል የተፈጠረለት ከኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት አባላት ብቻ አይደለም። በምስራቅ አፍሪካ ሀገሮች ሌላ ገበያ ተፈጠረለት። በወቅቱ የሎጂስቲክስ መምሪያ ሃላፊ በነበረው ሜ/ጄነራል ገዛይ አበራ መሪነት በተደረገ ድርድር አልመዳ ሬንጀርና ሌሎች ሎጂስቲክሶችን ለደቡብ ሱዳን እና ሱማሊያ ጸጥታ ሃይሎች የሚያቀርቡበትን ሁኔታ ተፈጠረ። ለደቡብ ሱዳንና ሱማሊያ የሚቀርበው ወታደራዊ አልባሳት ለአልመዳ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ የሚያገኝበት እድል ፈጠረለት። ይህ መልካም አጋጣሚ ለአልመዳ ጨርቃጨርቅ ብቻ አይደለም። ይልቁንስ ከአልመዳ ባልተናነሰ ለእነ ሜ/ጄነራል ገዛይ አበራ በኮሚሽን መልክ ከ50 ሚሊዮን ብር በላይ ማግኘታቸው አደባባይ ወጣ። ዘግየት ብሎም እነ "ወዲ አበራ" ከ450 ሚሊዮን ብር በላይ ይዘው ወደ አውሮፓ እብስ ማለታቸው ተነገረ።

እልመዳን ለማዳን ከሚደረገው ርብርብ አኳያ ሶስተኛ ትኩረት የተሰጠው መስሪያ ቤት "የትምህርት ሚኒስቴር" ሆነ። ሚኒስቴር መስሪያቤቱ ልዩ ትኩረት እንዲሰጠው ያደረጉት በርካታ ምክንያቶች አሉ። ሲጀመር፣ ከኢትዮጵያ ህዝብ ውስጥ አብዛኛው የሚገኘው በትምህርት ቤቶች ውስጥ ነው። ከ10 አመት በታች ያለው ኢትዮጵያዊ ከአጠቃላይ ህዝብ ብዛት 57% ያህሉን ይሸፍናሉ። በ1998 ዓ.ም. ከትምህርት ሚኒስቴር በተጠናቀረ መረጃ መሰረት ከ10 ሚሊዮን በላይ ታዳጊዎችና ወጣቶች በአንደኛና መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ውስጥ ይገኛሉ። በሁለተኛ ደረጃና በቴክኒክ ውስጥም ከአንድ ሚሊዮን በላይ ወጣቶች ይገኛሉ። በአገሪቱ የሚገኙት የመምህራን ቁጥርም ከ100ሺህ በላይ ይሆናሉ። በዚህም ሳይወሰን በየአመቱ ወደ10ሺ የሚቆጠሩ እጩ መምህራን የማስተማር ስራን ይቀላቀላሉ።

345

በመሆኑም ትዕምት ብሎም እልመዳ ጩርቃጩርቅ የሚያደርገው ኢኮኖሚ የማሰባሰብ እንቅስቃሴ አስተማማኝ የሚሆነው የህብረተሰቡን ግማሽ አካል ማሳተፍ የሚችል ስራ በሰራ ይሆናል። እልመዳ የጀመረውን የቁልቁለት ጉዞ በአስተማማኝ ቀልብሶ ተአምራዊ እመርታ ማምጣት የሚቻለው ትምህርት ቤቶችን ማዕከል አድርጎ ከተረባረበ ይሆናል። የሚገኘው የሃብት ምንጭም ለአንድ ጊዜ ብቻ ሳይሆን ቀጣይነት ባለው መልኩ ይሆናል። ስለሆነም እቶ መለስ እልመዳ በዘላቂ ገበያ እንጻር እንዲቃኝ ለማድረግ የትምህርት ተቋማት መምረጡ ትክክለኛ ውሳኔ ነበር። ከዚህም በተጨማሪ በፌዴራሊዝም ሆነ በክልል ባላቸው የሰው ሃይል፣ ፕሮጀክቶች፣ ግዥዎች፣ ሰራተኛ ቅጥር፣ የሚመደበው በጀት ቅድሚያውን ትምህርት ሚኒስቴር መያዙ "መንግስታዊ ሃብትን" ወደ ትዕምት በቀላሉ መውሰድ የሚቻልበትን ሁኔታ ይፈጥራል።

ይህንን ድልብ አቅም ለመጠቀም መጀመሪያ የተወሰደው እርምጃ የትምህርት አመራሩን በህወሓት እና ኢህአዴግ አባላት መሙላት ሆነ። ከላይ እስከ ታች ያሉ የትምህርት ተቋማት አመራር፣ መምህራን፣ ተማሪዎች እና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች (በተለይ ግገር ክፍል) የኢህአዴግ አባላት የሚሆኑበት እቅድ ተነደፈ። ለምሳሌ በአዲስ አበባ ውስጥ የሚገኙት ትምህርት መምሪያ ሃላፊዎች፣ ርዕሰ መምህራን እና አስተዳደር ሃላፊዎች 80% የህወሓት አባላት የሆኑበት አንዱ ምክንያት ይኸ ነው። አስቀድሞ እንደተነገረው በዘመነ እርከበ እቁባይ አዲስ አበባ ካሉት 10 የክፍለከተማ ትምህርት መምሪያ ስምንቱ የበላይ ሀላፊዎች የህወሓት ካድሬዎች ነበሩ። አዲስ አበባ

ሰላት ከ20 ያላነሱ ቴክኒክ ትምህርት ቤቶችና ኮሌጆች 90% ያህሉ ፕሬዝዳንቶችና የስራ አመራሮች የህወሓት አባላት ናቸው።

የትምህርት መዋቅሩን የኢህአዴግ አባላት እንዲሆኑ የማድረግ አስፈላጊነት የግለሰብ ተልዕኮ ለመስጠት ነው። በኢህአዴግ ቢሮ በሚዘጋጀው የአባላት "የግለሰብ ተልዕኮ" ውስጥ አንደኛው ፓርቲው በንብረትነት ከሚያስተዳድራቸው ኩባንያዎች የሚመረቱ ምርቶች ራሳቸው እና ሌሎች እንዲጠቀሙ ማድረግ ነው። አባላትም በመሠረታዊ ድርጅትና የጥናት ህዋሳት የግለሰብ ተልእኮአቸውን መወጣት እና አለመወጣታቸውን ሪፖርት ያቀርባሉ። አባላት ከአልመዳ እንዲር በሚለዩን የሚጠጉ ተማሪዎችና መምህራን የሚለብሱት ልብስ እና ብትን ጨርቆች ከጉና ሱቆ እንዲገዙ ማሳመን ነው። ትምህርት ቤቶችን አልመዳ በሚያመርታቸው እና ጉና በሚሸጣቸ ልብሶች ማጥለቅለቅ የሚቻለው የትምህርት አመራሩንና መምህራንን በድርጅት አባልነት ከታቀ ቀላል ይሆናል።

(እዚህ ላይ አንድ ግለሂስ አውርጄ መሄድ አፈልጋለሁ። ወቅቱ 1998 ዓ.ም. የሃምሌ ወ ነበር። የጉና ማርኬቲንግ ዳይሬክተር (በአሁኑ ሰዓት ስራ አስኪያጅ የሆነው) ጓደኛዬ ታጋይ አተይ ታደለ በጥብቅ እንደሚፈልገኝ ነገረኝ። ጊዜ ሳላጠፋ የዛኑ እለት አመሻሽ ላይ ቦሌ ከለትሮማ የሚገኘው የእሱ ቢሮ ሄድኩኝ። ተያይዘን ወደ ሜክሲኮ ራስ ሆቴል ሄድን። አተይ በጥብቅ የፈለገኝ ምክንያት የጉና 1999 ዓ.ም. እቅድ እያወጣ መሆኑንና እኔ የማግዘው ጉዳይ እንዳለ አጫወተኝ። አዲስ አበባን በተመለከተ ጉና ካወጣቸው እቅዶች ውስጥ ትምህርት ቤቶች ቅድሚያውን እንደሚይዙ ነገረኝ። ተማሪዎች በአዲሱ ዘመን ትምህርት ሲጀምሩ የሚገዟቸው አልባሳትና የትምህርት ቁሳቁሶች ጉና በመላው አዲስ አበባ ካቋቋማቸው ከ20ሺህ በላይ ሱቆች የሚገዙበትን ሁኔታ በአዲስ አበባ ከንፍ እቅድ ውስጥ እንዲካተት መወሰኑን ነገረኝ። ለዚህ እቅድ መሳካት ትብብር ማድረግ እንደሚገባኝ ገለጸ። በሂደትም አልመዳ የተማሪ ዩኒፎርም ለማምረት በእቅድ ደረጃ ስለያዘ ከወዲሁ የትምህርት ቤቱን ማህበረሰብ በአልመዳ ምርቶች ማላመድ እንደ ስትራቴጂ መቀመጡን አጫወተኝ።

ለካስ አተይ እኔን ከማናገሩ በፊት በአዲስ አበባ ትምህርት መዋቅር ያሉትን ከ500 የሚበልጡ የህወሓት አመራሮችና ርዕሰ-መምህራን በእቅዱ ዙሪያ አናግሯቸዋል። እነዚህ ከ80% በላይ የሚሆኑ ... በአብዛኛው ባለስልጣናት ሁሉም የኢህአዴግ አባላት እና የመደናውን የትምህርት አመራር ቦታ የተቆጣጠሩ ባለስልጣናት ሁሉም የኢህአዴግ አባላት እና

My text!

የከተማው ከንፍ እንዲሳተፍ አስተያየት ሰጥተው ነበር። እኔን አግኝቶ ለማናገር የተጣደፈው በዚህ ምክንያት ነበር። በነገራችን ላይ በአዲስ አበባ የሚኖሩ የኢህአዴግ አባላት ከከተማው ኢህአዴግ ከንፍ ፍቃድ ሳይጠይቁ ብሄራዊ ድርጅቶች መሰብሰብ እንደማይችሉ መመሪያ አለ። ይሁን እንጂ ይህ መመሪያ በልዩ ሁኔታ ለህወሓት አባላት የማይሰራ በመሆኑ፤ "ሰብስበናቸው ነበር" ብሉ ሲነግረኝ ብዙም አልገረመኝም።

አቶ ሊያጫወተኝ ያለውን ያለቃለት ጉዳይ በመሆኑ ዝርዝር ጥያቄዎችን ማንሳት አልፈለኩም ከዛ ይልቅ በምን መልኩ ማስፈጸም እንደሚፈልጉ ጠየቁሁት። አልመዳን ማዳን የሚለው ፕሮጀክት እንደሆነ ገለጸልኝ። ለጊዜው አልመዳ የሚያመርታቸው አልባሳት በልዩ ሁኔታ ከሃገሪቱ ገበያ በ20% ቅናሽ መወሰኑን ጨምሮ ገለጸልኝ። በሁለት አመት ውስጥ በመላው ኢትዮጵያ ከ10ሺህ በላይ መሸጫ ሱቆቹን ለመክፈት ዝግጅት መጠናቀቁን አበሰረን። የትግራይ ክልል ተማሪዎች አልባሳት፤ ደብተርና የትምህርት መሳሪያዎች መሉ ለሙሉ የተቆጣጠረው አልመዳ በአጭር ጊዜ አዲስ አበባን እና በዙሪያዋ ያሉ የኦሮሚያ ከተሞች መቆጣጠር የሚያስችለው ሁኔታ መፍጠሩን ነገረኝ። ማህበረሰቡና ልጆቹ የአልመዳን ምርት መለመድ ከጀመሩ በሂደት የተማሪ ዩኒፎርም አምርቶ ለመሸጥ እድል እንደሚፈጥር አጫወተኝ።

እነሆ! የአዲስ አበባ ድርጅት መዋቅር ከሚለው አበይት ስራዎች "አልመዳን ማዳን" የሚለው ፕሮጀክት እንደሚሆን ተስማማን። የአዲስ አበባ ህወሓት አባላት ሆነው የትምህርት አመራሩን የወሰዱ ባለስልጣናት የተሰጣቸውን አረንቴሽን መስራት አድርገው እንዲሉ እንደምናግዛቸው ቃል ገባሁ። የራስ ቲያትሩ ግብዣ አልቆ ተሰነባበትን ስንወጣ "እስቲ ያቺን ሸንብ ያዛት" በማለት የሆነ ነገር አስታቀፈኝ። ከብዙ ማንገራገር በኋላ በርሳውን ስከፍተው አዲስ ላፕቶፕ ነበር።)

***

የአልመዳ ጨርቃጨርቅና ልብስ ስፌት ፋብሪካ ፋይናንስን አስተማማኝ ከማድረግ እኳ የተወሰደው ሌላ እርምጃ የባንክ ብድር በልዩ ሁኔታ እንዲያገኙ ማድረግ ነበር። አቶ መለስ "የአብዮታዊ ዴሞክራሲ የልማት መስመሮችና ስትራቴጂዎች" ብሎ በሰየመው መጽሃፉ ላይ "ትዕምትን የመሳሰሉ ተቋማት ከመንግስት ድጋፍ ይደረግላቸዋል ተብሎ የሚነገረው መሰረት የሌለው አሉባልታ ነው" ብሎ ቢናገርም እውነታው በተቃራኒ ነው። ለዚህም አንዱ ማስረጃ

ለውየው ለ[illegible] ባን[illegible] ጥ[illegible] ትዕዛዝ [illegible] ልዩ [illegible] special loan class [illegible] ብ[illegible] እንዲወስድ [illegible]

My text!

አልመዳ "በልዩ ብድር ማዕቀፍ" እንዲካተት በመደረጉ ምክንያት ከልማት ባንክ ተበዳሪዎች ውስጥ ከፍተኛውን እንዲወስድ አድርጓል። እስከ 2002 ዓም ድርስ ከልማት ባንክ ከተበደሩ 442 መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች መካከል በቁጥር አንድ ከፍተኛ ብድር ያለበት አልመዳ ጨርቃጨርቅ ሆኗል። የሚገርመው ነገር አልመዳ ጨርቃጨርቅ ሲመሰረት ከንግድ ባንክ የወሰደውን 300 ሚሊዮን ብር መመለስ ስላልፈለገ "የተበላሸ አካውንት" ውስጥ ገብቶ እንዲሰረዝለት የተደረገው ብድሩ ወደልማት ባንክ ከተዛወረ በኋላ መሆኑ እየታወቀ በድጋሚ ግንባር ቀደም ተበዳሪ ሆኖ የተመረጠ መሆኑ ነው። አግራሞቱ በዚህ ብቻ የሚያበቃ አይደለም። የልማት ባንክ የብድር መጠን ጠለቅ ብሎ ለተመለከተው አልመዳ የወሰደው ብድር ከባንኩ አጠቃላይ ብድር 10% ያህል መሆኑን ይመለከታል። ይህ የብድር መጠን መንግስታዊ ፕሮጀክት የሆኑት እንደ ተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ያሉትን በሙቶ ሚሊዮን ብር ልቆ የተወሰደ ነው።

(ልማት ባንክ እስከ መጋቢት 2002 ዓ.ም. የሰጠው አጠቃላይ ብድር 7.6 ቢሊዮን ያክል ነው። ከዚህ ውስጥ አልመዳ 762 ሚሊዮን ብድር መንግስታዊ ፕሮጀክት የሆነው ተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ደግሞ 666 ሚሊዮን ብር ብድር ወስዷል። ዝርዝሩን "የ ትዕምት የፋይናንስ ምንጭ" በሚለው ምዕራፍ ይመልከቱ።)

አልመዳ ጨርቃጨርቅ ልብስ ስፌት ፋብሪካ ካላይ በተጠቀሠው መልኩ ያግበሰበሰውን ሃብት ለተጨማሪ ማስፋፊያ ስራ አውሎታል። በማቅለም፣ በማዳወርና በስፌት የተቃናጁ ስራዎች በኢትዮጵያ ብቸኛ ፋብሪካ የሆነው አልመዳ የምርት መጠኑን በአምስት እጥፍ በማሳደግ በ8 ቢሊዮን ብር የጀመረውን የማስፋፊያ ስራ በማጠናቀቅ ላይ ይገኛል። ከማስፋፊያ ፕሮጀክቶቹ በተጨማሪ ዘመናዊ ማሽኖችንና መለዋወጫዎችን ከቻይና፣ ደቡብ ኮሪያ፣ ስዊዘርላንድ እና ጀርመን የሚያስመጣበት ሁኔታ ተፈጥሯል። ለዚህ አባባል አማኝ የሚሆነው የሪፖርተር ጋዜጣ በጥቅምት 11 ቀን 2006 ዓም ያወጣው ዜና ነው። ሪፖርተር "በቢዝነስና ኢኮኖሚ" አምዱ ስር "አልመዳ ጨርቃጨርቅ በስምንት ቢሊዮን ብር በሚጠጋ ወጪ ማስፋፊያ እያካሄደ ነው በሚል ርዕስ ይፋ አድርጎታል። በዚህ የሪፖርተር ዘገባ መሰረት አልመዳ እያደረገ ባለው መስፋፋት ቀድሞ ከነበረው ምርቱ አምስት እጥፍ በማሳደግ በቀን 100 ቶን የማምረት አቅም እንደሚኖረው አሳውቋል።

My text.

ከዚህም በተጨማሪ ፋብሪካው ከተለያዩ ሃገሮች ማሽነሪዎችንና መለዋወጫ እቃዎች ለመግዛት በሂደት ላይ መሆኑን አመላክቷል። ፎንግስ ከተባለ የጀርመን ኩባንያ ያለቀላቸው ምርቶችን ለማምረት የሚያስችሉና የድወራ ስራን የሚያከናውኑ ማሽነሪዎች ለማስመጣት ስምምነት ላይ መድረሱን አስታውቋል።

አልመዳ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ ጠንካራ የገንዘብ ምንጭ እንዲኖረው ከተቀየሱት ስትራቴጂዎች ሌላኛው በኤፈርት ሌሎች ኩባንያዎች የአክስዮን ባለቤት እንዲሆን ማድረግ ነው። ይህ እርምጃ አልመዳን ብቻ ሳይሆን ሌሎች እህት ድርጅቶችንም አብሮ የሚያሳድግና የሚያሰፋፋ ይሆናል። የደህንነት ዋስትናም ይሠጣል። የኤፈርት ኩባንያዎች እንደ አንድ በዝምድናና በጋብቻ የተሳሰሩ ቤተሰቦች አይነት ናቸው። አንዱ ሲነሳ ሌላው ይነሳል። የህይወት ሜካናይዜሽን ገበያው ቢቀንስ፤ የአልመዳም ገበያ ይቀንሳል።... አንዱ ኩባንያ ብድግ ሲል ሌላውም ብድግ ይላል። ለአልመዳ ሠርግና ምላሽ ከሆነ ጉና ሠርገኛ ይሆናል። በአልመዳ ላይ የሚለኮስ እሳት ብዙ ርቀት ሳይሔድ ትራንስን ይለበልበዋል። አልመዳ የአመታዊ ገቢውን በማሻቀብ ከቀረጥ ነፃ ሲያደርግ ጉና የኪሳራ ፋይል በመሙላት ለቀጣይ አመታት ከግብር ነፃ ይሆናል።

በመሰረቱ ኤፈርት የሚያተኩረው አስቀድመው የተፈጠሩ እና በቀጣይ ሀብት ፈጣሪ የሆኑ ንብረቶችን በቁጥጥር ስር በማዋል በየደረጃው መከፋፈል በመሆኑ እንደ ቡድን የሚያጋጥመው ኪሳራ የለም። ሀብት የማከፋፈል ፖለቲካዊና መንግስታዊ ስልጣኑን በኩባንያዎቹ ባለቤቶች እጅ በመኖሩ ያለውድድርና ግልፀኝነት ከድርሻቸው በላይ የሚወስዱበት ሁኔታ ተፈጥሯል። ሌላው ቀርቶ መርፌ ቁልፍና ማጭድ የመሳሰሉ በጥቃቅንና አነስተኛ ነጋዴዎች ሊሸጡ የሚችሉ ቁሳቁሶችን በቁጥጥር ስር በማዋል ፍትሐዊ ያልሆነ ጥቅም በማግኘት ላይ ይገኛሉ። ይህ በመሆኑ ምክንያት የኤፈርት ኩባንያዎች ዋና ዋና የኢኮኖሚ ዘርፎች ብቻ ሳይሆን በመንደር የችርቻሮ ሱቆችም የበላይነት መጎናፀፍ ችለዋል።

ወደ ቀደመው ጉዳያችን ስንመለስ ለአልመዳ የፋይናንስ አቅም አስተማማኝ መሆን እንዲያግዝ፣ በሌሎች የህወሓት ኩባንያዎች አክሲዮን በመግዛት ባለቤት እንዲሆን ተደርጓል። አልመዳ በምህንድስና ከማማከር ጀምሮ የኮምፒውተር ሽያጭ ውስጥ ይሳተፋል።...የአርከበ እቁባይ የቤተሰብ ንብረት ተደርጎ እስከመቆጠር የደረሰው "አዲስ ኢንጂነሪንግ ኮንሰልታንሲ" ውስጥ አልመዳ በአክሲዮን አባልነት ይሳተፋል። ...ከ200 በላይ ትራክተሮች፣ ከ20 በላይ ኮምባይነሮች

My text!

በመያዝ ከ20ሺህ ሔክታር በላይ ሜካናይዜሽን ጥጥ እና ሠሊጥ በሚያመርተው ህይወት ሜካናይዜሽን አልመዳ የአክሲዮን ባለቤት ነው።...

አልመዳና ህይወት የእርሻ ሜካናይዜሽን

ተ.ቁ	የአክሲዮን ባለቤቶች	የአክሲዮን መጠን	የአንድ አክሲዮን ዋጋ	ጠቅላላ የአክሲዮን ዋጋ
1.	ትዕምት	969,999	25.00	24,249,975.00
2.	አልመዳ ጨርቃጨርቅ	10,000	25.00	250,000.00
3.	ጉና ትሬዲንግ	10,000	25.00	250,000.00
4.	ተስፋ የአገልግሎት ሃብት	10,000	25.00	250,000.00
5.	ዮማን ኪዳኔ	1	25.00	25.00

ሰንጠረዥ ቁጥር 8፡ የህይወት ሜካናይዜሽን አክሲዮን ባለቤቶች

የአልመዳን ምርት ገበያ አውጥቶ የሚሸጥለት ጉና ኢንተርፕራይዝ ውስጥ አልመዳ አለ። በዚህም ሳይወሰን የጉና ክፋይ የነበረው "ጉና ቡና ኢንተርፕራይዝ" ውስጥ አልመዳ ከፍተኛ ሼር አለው። በሌላ አነጋገር አልመዳ የደርጋ ጨፌ፣ የከፋ፣ የወሊጋና ጅማ ቡና መድረስ ከማንም በላይ የሚያስጨንቀው ሆኗል። ...አልመዳ በባንክና ኢንሹራንስ አገልግሎት ውስጥ ባለንብረት ለመሆንም አልቦዘነም። የኤፈርት ንብረት በሆነው አፍሪካ ኢንሹራንስ ውስጥ ትልቅ አክሲዮን ካላቸው መካከል አንዱ አልመዳ ሆኗል።

ለማንኛውም አልመዳ ጨርቃጨርቅ የአክሲዮን ባለቤቶች ከሆነባቸው የኤፈርት ድርጅቶች ውስጥ ጥቂቶችን ወደ መመልከት እንሸጋገር። ድርጅቶቹ የተሰማሩበትን ዘርፍ በውፍ በረር እንቃኘው። አስቀድሞ እንደተጠቀሰው የኤፈርት ኩባንያዎች በዝርዝር ማጥናት የፈለገ ሰው እያንዳንዳቸው ኩባንያዎች ራሱን የቻለ ክፍል ይወጣቸዋል። ለምን እላማ እንደተመሰረቱ፤ በታክስና ቀረጥ በኩል እንዴት ልዩ ድጋፍ እንደሚደረግላቸው፤ የገንዘብ ተቋማት በቀላሉ እንዴት ብድር እንደሚሠጧቸው፤ በሜጋ ግዥና ጨረታ እንዴት ተደርጎ አሸናፊ እንዲሆኑ እንደሚደረግ፤ በኢትዮጵያ ነፃና ፍትሐዊ ውድድር እንዳይሰፍን የሚጫወቱት ሚና፣ ህወሓትን በምን መልኩ

My text!

እንደሚደጉሙ ...ወዘተ ራሱን በቻለ መድብል መግለጥ ይቻላል። ስለ ኤፈርት ማውራት ስለ ኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ማውራት ስለሆነ!... ስለ ኤፈርት መፃፍ ስለ ህወሓት የደም ስር መፃፍ ስለሆነ!... ስለ ህወሓት መናገር ስለ ኢትዮጵያ መናገር ስለሆነ!

***

አልመዳና አዲስ ኢንጅነሪንግ ኰንሰልታንሲ ኢማ.

ተ.ቁ.	የአክሲዮን ባለቤቶች	የአክሲዮን መጠን	የአንድ አክሲዮን ዋጋ	ጠቅላላ የአክሲዮን ዋጋ
1	ትዕምት	3,880	1,000.00	3,880,000.00
2	**አልመዳ ጨርቃጨርቅ**	**40**	**1,000.00**	**40,000.00**
3	መሰቦ ህንጻ፣ መሳሪያዎች፣ ማምረቻ	40	1,000.00	40,000.00
4	መስፍን ኢንዱስትሪያል	39	1000.00	39,000.00
5	አርከበ እቁባይ	1	1000.00	1,000.00

ሰንጠረዥ ቁጥር 9: የአዲስ ኢንጂነሪንግ ኮንሰልታንሲ ኢ.ማ. አክሲዮን ባለቤቶች

አልመዳ ጨርቃጨርቅ የአክሲዮን ባለቤት ከሆነባቸው የኤፈርት ኩባንያዎች አንዱ አዲስ ኢንጂነሪንግ ኮንሰልተንሲ ነው። መቀመጫውን አዲስ አበባ ያደረገው አዲስ ኢንጂነሪንግ በምህንድስና ዙሪያ የማማከር አገልግሎት ይሠጣል። በተለይም በአዲስ አበባና ዙሪያዋ የሚገነቡ ህንጻዎች ከጅምሩ እስከ መጨረሻው ሙሉ ሀላፊነት እየወሰደ አስገንብቶ ያስጨርሳል። ለዚህ አላማ ግብ መምታት በማሰብ የአዲስ ኢንጂነሪንግ ኮንሰልታንሲ የቦርድ ሰብሳቢ አርከበ እቁባይ ሆነ። አርከበ እቁባይ የአዲስ አበባ ምድብ ከንቲባ፣ የስራና ከተማ ልማት የበላይ ሀላፊና የጠቅላይ ሚኒስትሩ የከተማ ልማት አማካሪ ሲሆን እንዲያሳካ ከተቀመጠለት ዋና ዋና ስራዎች አንዱ የህንጻ ግንባታ የማማከሩን ስራ በኤፈርት ሞኖፖሊ የሚገባበትን ሁኔታ መፍጠር ነው። ይህ የፈረንጅ ላም እንደማለብ የሚቅቆጠር የስራ መስክ ሊሳካ የሚችለው እንደ አዲስ አበባ እና ፌደራል ስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴርን ያሉ ተቋማት በህወሓት ቁጥጥር ስር ማዋል ከተቻለ ብቻ ነው።

በመሆኑም አርከበ እቁባይ በዚህ ዙሪያ የተሰጠውን የኤፈርት ተልእኮ ለመፈፀም በርካታ ርምጃዎች ወሰደ። ቀደም ባለው ማስታወሻ እንደተገለጠው የአዲስ አበባ መሬት አስተዳደር ሥራ አስኪያጅ የነበረ እና አስተዳደሩ ከግማሽ ቢሊዮን ብር በላይ እንዲያጣ ማድረጉን መረጃ ጋበት ከስራ እንዲሰናበት የተደረገው አርኪቴክት አማረ አስገዶም ወደ ስራ እንዲመለስ ረገው አርከበ እቁባይ ነው። ከዛን በኋላ አማረ አስገዶም የአዲስ አበባ ኢንጂነሪንግ ንሰልታንሲ ብሎም አዳዲስ የህወሓት ባለሀብቶችን የማገዝ ስራ ውስጥ እንዲሳተፍ ተደርጓል። ፈርቱ አዲስ ኢንጂነሪንግ ውስጥ ያሰፉ ስራዎች ያለአንዳች ቢሮክራሲያዊ ውጣውረድ ወደ ስራ ሚገቡበት ሁኔታ ተፈጠረ። የከተማዋ ማስተር ፕላን ቁልፍ በእጃቸው ላይ የሚገኙት አርኪቴክ አማረ እና አርከበ እቁባይ ለአዲስ ኢንጂነሪንግ በእጃቸው ያለውን የግንባታ መረጃ አስረከቡ። ቀስ ቀስ አዲስ ኢንጂነሪንግ ትንሹ ማዘጋጃ ቤት ሆነ። ዋናውና ትልቁ ማዘጋጃ ቤት አዲስ ኢንጂነሪንግ እንዳያስቸግረው ደግሞ ከትግራይ የመጣውና የአርከበ የስጋ ዘመድ የሆነው ታጋይ ሀይሌ ፍሰሀ አዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ስራ አስኪያጅ እንዲሆን ተደረገ።

(የአዲስ አበባን የስልጣን አወቃቀር ጠለቅ ብሎ ለተመለከተ ሰው ሶስት ቁልፍ የስልጣን ቦታዎችን ይመለከታል። መሬት አስተዳደርን ጨምሮ ሌሎች የማዘጋጃ ቤት ስራዎችን የሚመራው ሰው፤...የአዲስ አበባ ኢህአዴግ ጽ/ቤት ሃላፊው እና የፖሊስና ፀጥታ ሀላፊው ናቸው። በአሁን ወቅት ሦስቱም ከትግራይ በመጡ "ምስለኔዎች" በሆኑ የህወሓት ታጋዮች እንዲያዙ ተደርጓል።)

በአዲስ አበባ ያለው በዚህ መልኩ ከተሰራ በኋላ ቀጣዩ በፌደራል መንግስት ደረጃ ያለው የስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር ይሆናል። ሚኒስቴር መስሪያቤቱን በቁጥጥር ስር ለማዋል "ኖሮ የሌለው" ዶ/ር ካሱ ኢላላ በሚኒስትርነት፤ አርከበ እቁባይ በምክትል እንዲመደቡ ተደረገ። ቀስ በቀስ በተቋሙ ውስጥ ያሉት ዳሬክተሮች በሙሉ በህወሓት ካድሬዎች ተሞሉ። ህወሓት በስራና ከተማ ልማት እስተማማኝ የፖለቲካ ጡንቻውን በእጁ አስገባ። ነባር ሙያተኞችንና ሀላፊዎች ተራ በተራ መስሪያቤቱን ለቀው እንዲወጡ ተደረገ።

(በነገራችን ላይ ኮሙዩኒኬሽን ጽ/ቤት ሲቋቋም ከተሰሩት ስራዎች አንዱ በፌደራል ደረጃ በሁሉም ተቋማት ያሉ ሚኒስትሮች ስራ አስፈጻሚዎች፣ ስራ አስኪያጆች፣ ኮሚሽነሮችና ዳሬክተሮችን ዝርዝር ማጠናቀር ነበር። ስራና ከተማ ልማት ከሁሉም ተቋማት በዳሬክተሮች ብዛት ተወዳዳሪ አልነበረውም። ሀላፊዎቹ የሚገኙት ደግሞ ከሌላው መስሪያቤት ሁለትና ሦስት

My text!

አጥፍ ነበር። የሆነ ሆኖ ማስሪያ ቤቱ ካሉት ዘጠኝ ዲሬክተሮች ውስጥ ስምንቱ የህወሓት ካድሬዎች ነበሩ። ዶ/ር አብርሃም ተክስተ፣ አርክቴክት አማረ አስገዶም፣ አርክቴክት ሚካኤል ከበደ ብሩ፣ ገ/ተንሳይ፣ ገ/ህይወት (በአዲስ አበባ ት/ቤር ቴክኒክና ሙያ ሀላፊ የነበረ)፣ ከነዚ ወዘተ ይገኙበታል።... ይህን በመመልከት ነበር የስራና ከተማ ልማት ሠራተኞች የተቋማቸው የስራ ቋንቋ ከአማርኛ ወደ ትግርኛ ተቀይሯል የሚል ቅሬታ የሚያቀርቡት። ህንፃ መገንባት የሚፈልጉ ባለሀብቶችም አዲስ ኢንጂነሪንግ ኮንሰልታንሲን በማካሪነት ሳይቀጥሙ ቀዳሚ ተመራጭነታቸው ያደረጉት በዚህ ምክንያት ነው።)

ጉዳዩ በአዲስ አበባ ኢንጂነሪንግ ኮንሰልታንሲ የሚያቆም አይደለም። በኢትዮጵያ አፈር ላይ ያሉ ሁሉንም ስራዎች በቁጥጥር ስር ለማዋል እንደ ግብ ያስቀመጠው ኤፈርት በዚህም ዘርፍ ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻ የሚሳተፍበትን ድርጅት በባለቤትነት ይዟል። የድርጅቱ ስም "አዲስ ኮንሰልታንሲ ሀውስ" ይባላል። አዲስ ኮንሰልታንሲ ሀውስ ኤፈርት በህወሓት ታጋዮች አክሲዮን ስም እንዲያዙ ያደረጉበት ነው። የሼር ባለቤቶቹ እና የተሰማራበት ዘርፍ በአጭሩ እንደሚከተለው ይመስላል።

አዲስ ኮንሰልታንሲ ሀውስ ኢ.ማ.

ተ.ቁ.	የአክሲዮን ባለቤቶች	ጠቅላላ የአክሲዮን ዋጋ
1.	ትዕምት	1,000,000.00
2.	ሰለሞን ተስፋዬ ገብረአገዚ	500,000.00
3.	ገ/ተንሳይ ገ/ሚካኤል	500,000.00

ሰንጠረዥ ቁጥር 10: የአዲስ ኮንሰልታንሲ ሀውስ ኢ.ማ. አክሲዮን ባለቤቶች

አዲስ ኮንሰልተንሲ ሃውስ የተሰማራበት ስራ የማማከር ሲሆን ከእነዚህም ውስጥ ፕሮጀክቶችን የመለየት (project identification, ቅየሳ (Sector Survey): ቴክኒካል፣ ሜካኒካል እና ኤሌክትሪክ ዲዛይን፣ ፕሮጀክት ሞኒተሪንግ፣ የጨረታ ዶክመንቶች መመርመርና ማዘጋጀት (Preparation and Evaluation of Bid Documents), የኮንትራት ዶክመንቶችን ማዘጋጀትና ስልጠና ናቸው። ይህ በኤፈርት ባለቤትነት የተያዘው ድርጅት በሌሎች የኤፈርት ድርጅቶች ውስጥ

My text!

ተጨማሪ አክሲዮኖች አሉት። ከእነዚህም ውስጥ ብርሃን ኬሚካል እና ኢክስፐረስ ትራንዚት አገልግሎት ይገኝበታል። የድርጅቱ ስራአስኪያጅ ሰለሞን ተሰፋዬ ሲሆን የህዉሓት ማዕከላዊ ኮሚቴ እና የፓርላማ አባል ነበር። ቀደም ባልው ገፅ እንደተገለጠው ብሩክ ኬሚካል በእልመዳ አክሲዮን ድርሻ እንዲቋቋም የተድረገ ነው።

እሁንም የድርጅቱ ትሥምር በዚህ ቢያበቃ ጥሩ ነበር። ነገር ግን "አዲስ ኮንሰልታንሲ ሀውስ" የፕሮጀክት መረጣውን፣ ቅየሳውን፣ ኤሌክትሮኒክ ዲዛይኑን የሚያዘጋጀው በኮምፒውተር ዘመናዊ ኔትወርኪንግ ስርአት ነው። ይህንን ለማድረግ ደግሞ ኤፈርት ተስማሚ ድርጅት ማቋቋም ነበረበት። እልመዳም በአክሲዮን ባለቤትነት የሚይዛቸው ድርጅቶች ማስፋት አለበት። በመሆኑም እልመዳ፣ መስከረም ኢንቨስትመንት እና ሶሉሽን ኢንተርፕራይዝ በጋራ ሆነው "ኮምፒዩተር ኔትወርኪንግ ቴክኖሎጂ" የሚባል ኩባንያ አቋቋሙ። የቴክኖሎጂ ክፍተቱን ለመሸፈን ቻሉ።

እልመዳና ኮምፒውተር ኔትወርኪንግ ቴክኖሎጂ

ተ.ቁ	አክሲዮን ባለቤቶች	የአክሲዮን መጠን	የአንድ አክሲዮን ዋጋ	ጠቅላላ የአክሲዮን ዋጋ
1.	እልመዳ ጨርቃጨርቅ	200	1,000. 00	200,000.00
2.	መስከረም ኢንቨስትመንት	200	1,000. 00	200,000.00
3.	ሶሊሽን ኢንተርፕራይዝ	200	1,000. 00	200,000.00
	ድምር			600,000.00

ሰንጠረዥ ቁጥር ፱፡ የኮምፒውተር ኔትወርኪንግ ቴክኖሎጂ አክሲዮን ባለቤቶች

አልመዳና አፍሪካ ኢንሹራንስ

ተ.ቁ	የአክሲዮን ባለቤቶች	የአክሲዮን መጠን	የአንድ አክሲዮን ዋጋ	ቃል የተገባ /Subscribed/ የአክሲዮን ዋጋ	የተከፈለ /Paid Up/ የአክሲዮን ዋጋ
1.	አልመዳ ጨርቃጨርቅ	6000.00	1,000	3,000,000.00	3,000,000.00
2.	ህይወት ሜካናይዜሽን	6000.00	1,000	3,000,000.00	3,000,000.00
3.	መስፍን ኢንዱስትሪያል	6000.00	1,000	3,000,000.00	3,000,000.00
4.	መስከረም ኢንቨስትመንት	6000.00	1,000	3,000,000.00	3,000,000.00
5.	ተስፋ የቀንድ ከብት	5970.00	1,000	3,000,000.00	2,970,000.00
6.	የማነስ እቁባይ ምትኩ	10	1,000		10,000.00
7.	ቴዎድሮስ ሃጎስ ተስፋይ	10	1,000		10,000.00
8.	ሀጎሼ ገብረኪዳን ሃጎስ	10	1,000		10,000.00

ሰንጠረዥ ቁጥር 12: የአፍሪካ ኢንሹራንስ አክሲዮን ባለቤቶች

ከሠንጠረዥ ቁጥር 12 ማየት እንደሚቻለው ከአፍሪካ ኢንሹራንስ አክሲዮን ባለቤቶች ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ ከያዙት 5 የኤፈርት ድርጅቶች አንዱ አልመዳ ነው። አልመዳ የኢንሹራንስ ባለቤት በመሆኑ በአንድ በኩል ያለምንም ስጋት ስራውን በተቀላጠፈ መንገድ ለመፈፀም ያስችለዋል። ጉዳት ቢደርስበትም የሚፈጽመው ክፍያ ከግራ ኪስ ወደ ቀኝ ኪስ በመሆን ያለምንም ወጣ ውረድ የሚያገኝበት ሁኔታ ፈጥሮለታል። በሌላ በኩል አፍሪካ ኢንሹራንስ ከሚያገኘው ትርፍ ተከፋይ ይሆናል። በመሆኑም አፍሪካ ኢንሹራንስ ለአልመዳ ሌላኛው የሀብት ምንጭ ተደርጎ ሊወሰድ የሚችል ነው።

My text!

በህወሓት ባለቤትነት የተያዘው አፍሪካ ኢንሹራንስ የተሰማራበት ዘርፍ የመድህን ዋስትና መስጠትና ከዚያ ጋር የተያያዙ ተግባራት ናቸው። የአፍሪካ ኢንሹራንስ የቦርድ ሊቀመንበር ዮሃንስ አቁባይ ሲሆን፣ በተከታይነት ቴዎድሮስ ሃጎስና ህቡር ገ/ኪዳን ይመሩታል። ዮሃንስ ዕቁባይ ነባር የህወሓት ታጋይ ሲሆን፣ የአርከበ እቁባይ ታናሽ ወንድም ነው። ቴዎድሮስ ሃጎስ የህወሓት ፖሊት ቢሮ አባል ሲሆን ሌሎች የኤፈርት ኩባንያዎችን በተጨማሪ ያስተዳድራል። ህቡር ገ/ኪዳን ከህወሓት መስራቾች ውስጥ አንዱ ሲሆን፣ የድርጅቱ የደህንነት ጉዳዮች ሃላፊ ነበር። የደህንነት ስራውን ለክንፈ ገ/መድህን ያስረከበ ሲሆን ዘግየት ብሎ የፓርላማ አባል እንዲሆን ተደርጓል።

***

እንግዲህ አቶ መለስ "የአብዮታዊ ዴሞክራሲ የልማት መስመሮችና ስትራቴጂዎች" በሚለው መጽሃፍ እልመዳን የመሳሰሉ የህወሓት ኩባንያዎች "ከመንግስት ያገኙት ወይም የወሰዱት ሰባራ ሳንቲም የለም። ለወደፊትም አይኖርም። ይሄ መሰረተ ቢስ ስም ማጉደፍ ነው።" በማለት በድፍረት ይጽፋል። በድፍረት ይናገራል። እኛም ጹሁፉንና ንግግሩን መርምረን፣ የሃገሬው ህዝብ ምን እንደሚል ሳናዳምጥ እንደበቀቀን እንደግመዋለን። ከአዳራሽ አልፈን ከጓደኞቻችን ጋር በመጠጥ ቤት ስንገናኝ እንኳን "መለስ እንዳለው፣ አብዮታዊ ዴሞክራሲ እንዳለው " እያልን እናነበንባለን። ጓደኞቻችን " ኧረ አባካችሁ! አብረን አያደግን አይደለም" በማለት ሲከራከሩን "ጥገኞች፣ ኪራይ ሰብሳቢዎች፣ የጦማር ጋዜጣ አንባናቢዎች፣ ያለፈው ስርዓት ርዝራዦች፣ የአዲሲቷ ኢትዮጵያ ጠላቶች፣ ወዘተ" እያልን እንወቅሳቸዋለን። የእኛን ስድብ ወደጎን ትተው በሚታዩ የቁጥርና ሌሎች መረጃዎችን ሲያቀርቡ ደግሞ "ጠባቦች ትምክህተኞች፣ የትግራይ ህዝብ ጠላቶች፣ የጠነባ ኋላቀር አመለካከት ተሸካሚዎች፣ የአርማጌዶን ነጋሪት ጎሳሚዎች፣ እያልን በድጋሚ እናሸማቅቃለን።

ያልተሄደበት መንገድ ጉዞውን አላጠናቀቀም፣ ከአቶ መለስ የህይወት ፍጻሜ በኋላ በህዝብ ወዝ የተገኘው ንብረት ህወሓት የተለያዩ ስልቶችን በመቀየስ ወደራሱ ካዝና በማስገባት ላይ ይገኛል። በትናንት እና ዛሬ መካከል ልዩነት የለም። "ለሰው ልጆች ምቾት የተፋለመ የዘመን ስብዕና" ብለው የሚጠሩት መለስ በህይወት ባይኖርም አስተምህሮቶቹ አልተቀየሩም። ለአቶ መለስ በየጊዜው አዳዲስ ስያሜ የተሰጠው ታሪክ እየተፈጠረለት ነው። አባቶቻችን ታሪክ ሰሪው ህዝብ በማለት ደጋግመው ቢነግሩንም የምናነበው ታሪክ ግን ይሄንን አያመላክትም። የሚነገረውም ተመሳሳይ ሆኗል። ፈጠራና ኩሸት የወለደው ታሪክ የኢትዮጵያን አየር ሞልቶታል። ሌላው ቀርቶ

የአቶ መለስ የበልቀ ጅረፍ ለሁለት አስርተ አመታት ሲገርፋቸው የነበሩት የአዲስ አበባ ወጣቶች "ሳናውቅ ጠላንህ፣ ስናውቅ አጣንህ" በማለት እንባ እንደተራጩ የሚያመላክት ታሪክ ተጽፎ እያነበብን ያለንበት ወቅት ነው።

ያለማጋነን ከየትኛውም የኢትዮጵያ ማህበረሰቦች የአዲስ አበባን ወጣቶች ጠንቅቄ አውቃቸዋለሁ። የአዲስ አበባ ወጣት ስንልበናም እንደራሴ አውቀዋለሁ። የመዲናይቱን ወጣት በሰበሰብን ቁጥር የሚነግረን በትግራይ ውስጥ ለሚካሄዱት ኢንቨስትመንቶች፣ የትዕምት ኩባንያዎች ለወጣቱ የፈጠሩለት የስራ ዕድል ጋር የተያያዘ ቢባል ማጋነን አይሆንም። ወጣቱ በአንድ በኩል እንደአለመዳ ጨርቃጨርቅ ያሉ ፋብሪካዎች የፈጠሩት የስራ እድል እያነሱ በሌላ በኩል ከፍተኛ የህዝብ ከምችትና የተፈጥሮ ሃብት ያለባቸው እንደኦሮሚያ ያሉ ከልሎች ወደኋላ መቅረት እያነሱ ሞግተውናል።

እርግጥም የአዲስ አበባ ወጣት በአቶ መለስ አይን በጥላቻ የሚታይ እና ብዙ ችግር የደረሰበት ነው። አቶ መለስ በሚያራምደው አግላይ ፖሊሲ ምክንያት ውኝርንብር ውስጥ የገባ፣ የተገደለ፣ እስር ቤት የገባ እና የተሰደደ ነው። "አብዮታዊ ዴሞክራሲ" በዛሬው የጥላቻ ፖለቲካና አድሎዓዊ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ምክንያት ህይወታቸው ወደ አዘቅት ወርዷል። በዚህም ምክንያት ከአቶ መለስ ጋር ያለው ጠብ መሰረታዊ እና በቀላሉ የሚሽር አይደለም። "ድርጅቱ" ጥሎት ያለፈው ጠባሳ ከትውልድ ትውልድ የሚሸጋገር እንጂ በአንድ የወጣትነት ዘመን አይቆምም። የመንዲ ወጣት አቶ መለስን "አውቆ ጠልቶታል፣ አውቆ በደስታ ሸኝቶታል" ...እንደ እርሞ ወጣቶች ህዝባዊ እምቢተኝነቱን በተደራጀ መንገድ ሲያቀጣጥል አቶ መለስ የተሰቀለበትን ቢል ቦርድ እያነሳ ማቃጠሉ የጊዜ ጉዳይ ብቻ ይሆናል። እስከዚያው ድረስ የአቶ መለስ ገድል ከተገለጸበት የኢህአዴግ መጽሄፍ ውስጥ " መለስ ሳያውቁት የጠሉት፣ ሲያውቁት ደግሞ ያጡትን የወጣቶች ሮል ሞዴል በሚለው ርዕስ የተጻፈው አንቀጽ ምን እንደሚል በማሳየት ወደሌላ የትዕምት ኩባንያ እንሸጋገር።

እነሆ በገጽ 30 ላይ "ሳያውቁ የጠሉት፣ ሲያውቁት ያጡት" የሚለው ክፍል እንዲህ ይላል።

"መለስ ለኢትዮጵያ ወጣቶች ምን ማለት እንደሆነ የአዲስ አበባ ከተማ ወጣቶች በህልፈተ-ህይወቱ ማግስት "ሳናውቅ ጠላንህ፣ ስናውቅ አጣንህ" ብለው በእንባ እየተራጩ በሚገርም መንገድ

ከዘፈኑበት መንገድ የተሻለ ሊገልጸው የሚችለው ነገር የለም። በእርግጥም መለስ የኢትዮጵያ ወጣቶች ሳያውቁት ያገለገላቸው፣ ሳያውቁት የጠሉት፣ ማወቅ ሲጀምሩ ደግሞ ያጡት ታላቅ ሰው ቀዩ አስጠባቂ ሰብዕና ነበር" በማለት ይገልጻል።

የአዲስ አበባ ወጣቶች አቶ መለስን አያውቁትም ነበር የሚል ደፋር ግምገማ የለኝም። አስከማውቀው ድረስ የአዱገነት ልጆች አቶ መለስን እስከ ዶቃ ማሰሪያው ያውቁታል። በአዲስ አበባ የፕሮፓጋንዳ ስራ ውስጥ ለአስርተ አመታት ስላሳለፍኩ ከእንዲህ አይነት የፈጠራ ድርሰትና ሃቅ ወሬ በስተርጀባ እነ በረከት ምን እንዳሰቡ ይገባኛል። አቶ መለስ በስልጣን ላይ በነበረበት ሀያ አመታት "በወርቅ ዘር" እና "በአደገኛ ቦዘኔ" መካከል ያለውን ፍረጃ ሲገልጥ አጠገቡ ነበሩ። አቶ መለስ የትግራይ ወጣቶችን ለብቻ ሠብስቦ "የአባት እና አያቶቻችሁን ዙፋን ተረከቡ!" ሲል "በዝሆን ጆሮአቸው" አዳምጠዋል። የአዲስ አበባ ወጣቶች ደግሞ "በአህያ ጆሮአቸው" ሠምተው በሠሙት ንግግር በጣም አዝነዋል።

የአዱገነት ወጣቶች አቶ መለስን የሚያውቁት ከአንደበቱ በሚወጣው ቅጥፈት ነው። በሚያዝያ 10 ቀን 93 በአዲስ አበባ በተነሳው ግርግር ከ40 ወጣቶች በላይ ሞተው፣ ከ20ሺህ በላይ የከተማዋ ተማሪዎች ወደ ኦሮሚያ እና ሌሎች ማጎሪያዎች ተልከው (ልደቱ አያሌውና ሙሼ ሠሙን የመሳሰሉ የፖለቲካ መሪዎች የነበሩትን ይጨምራል) አቶ መለስ የሠጠው ጋዜጣዊ መግለጫ ያንን ያመለክታል። በተለይም ለቢቢሲ ጋዜጠኛ የሠጠው ቃለ- መጠይቅ እኛን ላይቀር በአዳራሽ ውስጥ መዘባበቻ አድርጎን ነበር። አቶ መለስ ከበታቹ ያሉ ካድሬዎችና ባለስልጣናት ያቀረቡለትን ኢንፎርሜሽኖችን ወደ ጎን በመተውና ሀቅን በመሸሸ የሠጠው መግለጫ በከፊል እንዲህ ይላል፣

"በአዲስ አበባ የተከሰተው ሁኔታ በአጭር ጊዜ ውስጥ ከቁጥጥር ውጪ እየሆነ በመሄዱ ያንን ለማርገብ እርምጃ መውሰድ አግባብ ነበር። በከተማዋ ህግና ስርአት ለማስከበር ያንን የሐይል አማራጭ መጠቀም አማራጭ ያልነበረው ነው።...እኔ የማውቀው በወቅቱ አንድም ተማሪ እንዳልተያዘ ወይም በቁጥጥር ስር እንዳልዋለ ነው።... እኔ አሁንም ላረጋግጥ የምችለው በወቅቱ በከተማዋ ውስጥ ተፈጥሮ ከነበረው ረብሻ ጋር በተያያዘ ተሳትፎ የነበራቸውንና ተደጋጋሚ የወንጀል ሪከርድ ያለባቸው ቦዘኔዎች ማሠራችንን ነው። የወንጀል ሪከርድ ካለባቸው ውጭ የያዝነው የለም። የፖለቲካ ፓርቲ አባላት የሆኑትም ከአራት አምስት አይበልጡም" ነበር ያለው።

(አቶ መለስ ይህን መግለጫ በሠጡ እለት በቁራ (ወረዳ 20)፣ ሊደታ (ወረዳ22)፣ ቂርቆስ (ወረዳ 21)፣ ኮልፌ (ወረዳ 24) ብቻ 500 የሁለተኛ ደረጃና ቴክኒክና ሙያ ተማሪዎች በአፈሳ ተይዘው ሸዋሮቢት ተወስደዋል። ወደ ሸዋሮቢት ከተጋዙት ተማሪዎች መካከል ወደ 20 የሚጠጉት በወባ እና ተቅማጥ በሽታ ህይወታቸው አልፏል።...አቶ መለስ በመግለጫው ፖለቲካ ፓርቲ አባላት ውስጥ የታሰሩት ከአራትና አምስት አይበልጡም ቢልም፣ ከዞን ሁለት (ወረዳ 21, 22, 23, 24) ብቻ 56 በስም ዝርዝር የተገለጡ የተቃዋሚ አመራሮች ቤት ለቤት ተለቅመው ወደ ሸዋሮቢት ሔደዋል።)

My text!

ምዕራፍ **10**

“ገብረየስ ኬኛ!”

“ለእዚህ ተቋማት የሚቀርበው አንድ መሠረታዊ አሉባልታ ከመንግስት ድጋፍ ይደረግላቸዋል፤ የባለሀብቶችን እንቅስቃሴ ለማፈንና ኢኮኖሚውን ለመቆጣጠር የተፈጠሩ ናቸው የሚለው ነው።”

መለስ ዜናዊ

የአብዮታዊ ዴሞክራሲ የልማት አቅጣጫዎች

***

ጥቅምት 23/2016 አሌክሳንድሪያ ቨርጂኒያ

የምሳ ሰዓት ደርሷል። ከኢሳቱ ጋዜጠኛ ሲሳይ አጌና ጋር በመሆን የአንድ “ኢትዮጵያዊ ቁርካ” ምሳ ግብግብ ላይ ለመታደም እየተጓዝን ነው። ለእኔ ከደረሰኝ የክብር ምሳ ግብግብ በላይ ከጋባዤ አዛውንት ጋር ቁጭ ብሎ ለማውራት ጓጉቻለሁ። የአባቴ ሀገር ሰዎች “የጌጃ ንጉስ” እያሉ የሚጠሩት አዛውንት ገብረየስ ቤኛ (“ገብረየስ ኬኛ”) ይባላሉ። የአባቴ ሀገር “ገጃ” በየዓመቱ የታህሳስ ገብርኤል ንግስ ሰንሔድ ከምሰማው እና የህሊና ግድግዳዬ ላይ ተጣብቆ የቀረው ቃል “ገብረየስ ኬኛ” የሚለው ነው።

ገብረየስ የኛ! ገብረየስ ኬኛ!

ከጋዜጠኛ ሲሳይ ጋር እየተጓዝን ሳለ ኤፈርት የመሳሠሉ የህወሓት ኩባንያዎች አማልጋሜትድ እና ሌሎች ሐገራዊ ከበርቴዎችን በተጠና መንገድ ከኢትዮጵያ ምድረ-ገፅ እንዲጠፉ የተደረገበትን አቅጣጫ እያነሳን ተጫወትን። በአብዮታዊ ዴሞክራሲ ውስጥ “ዴሞክራሲያዊ መሳሪያዎች” እና “ኢኮኖሚያዊ መሳሪያዎች” የሚባሉ አቅጣጫዎች እንዳሉ አወጋሁት። የአማልጋሜትድ ባለቤት ገብረየስ ቤኛ ግብርና ወለድ በሚባሉ “ኢኮኖሚያዊ መሳሪያዎች” አማካኝነት ከጥቅም ውጭ እንዲወጣ መደረጉን ጨምሬ ነገርኩት። እንደዚህ አይነት አቅጣጫ

በግልፅ ተቃውሞ ሲያበቃ አቶ መለስ በፃፈው መጽሐፍ "ኢፈርትን የመሳሰሉ ኩባንያዎች ከተቋቋሙበት አንዱ አላማ የግል ባለሀብቶችን ለማበረታታት ነው" በማለት እንደገለጠ አስታወስኩት።

ሲሳይ የሰውየውን አይን ደረቅነት ቢያውቅም በዛ ርቀት ሐዶ ኢፈርት የግል ባለሀብቶችን ለማበረታታት ተቋቋመ የሚለው አባባል በጽሁፍ መገለጡ አስገረመው። በኢትዮጵያ ምድር ነባር ባለሀብቶችን ለማፈን የተሔደው ርቀት የሚዘገንን ሆኖ ሳለ ድጋፍ እናደርጋለን ብሎ በመጽሐፍ መልክ ማዘጋጀት የስርዓቱን ትክክለኛ ባህሪ እንደሚያሳይ ተናገረ። እነዚህ ሰዎች በዚህ ደረጃ በቅጥፈት እንደተሞሉ ህዝብ እንዲያውቅ መደረግ እንዳለበት ጨምሮ ገለጠ።

እኔም ለመንገዳችን መግፊያ እንዲሆነን አቶ መለስ "የአብዮታዊ ዴሞክራሲ የልማት አቅጣጫዎች" ብሎ ከፃፈው መጽሐፍ ውስጥ ጥገኞችና አንዳንድ የውጭ ኃይሎች ኢፈርትን በመሳሰሉ ኩባንያዎች እንዴት ጠላት እንደሆኑ የገለጠበትን አውጥቼ አሳየሁት። የመኪናውን መሪ የጨበጠው እሱ በመሆኑ እንደሚከተለው አነበብኩለት፤

"በእነዚህ ተቋማት (ኤፈርት) የሚቀርበው አንድ መሠረታዊ አሉባልታ ከመንግስት ድጋፍ ይደረግላቸዋል፤ የባለሀብቶችን እንቅስቃሴ ለማፈንና ኢኮኖሚውን ለመቆጣጠር ተብለው የተፈጠሩ ናቸው የሚለው ነው። እነዚህ ተቋማት እንደማንኛውም ባለሀብት ተቋም በህግ ተመዝግበው በህግ የሚሰሩ ተቋማት ናቸው። ሁሉም የመንግስት ሰራተኛ ደግሞ ለማንኛውም አካል ልዩ ድጋፍ እንዳይሰጥ በህግና በመመሪያ ይታዘዛል። ከዚህም በላይ እነዚህ ተቋማት ሲመሰረቱ ጀምሮ ከማንኛውም የግል ኩባንያ በላይ ህግና መመሪያን አክብረው መሄድ እንዳለባቸው ጠንቅቀው ያውቃሉ። ስለሆነም የሚቀርበው አሉባልታ መሰረተቢስ ነው" በማለት እንባቡ ሳልጨርስ ጋዜጠኛ ሲሳይ "የሚገርም እኮ ነው!" እያለ መሳቅ ጀመረ።

61

እብሬ እየሳኩ ቀጣዩን አንቀጽ ጮክ ብዬ እንደሚከተለው አነበብኩለት፣

"እነዚህ ተቋማት የአካባቢ ልማትን ለማፋጠን፤ ልማታዊ ሚና ካላቸው ባለሃብቶች ጋር ተደጋግፈው ለመስራትና እነርሱንም ለማበረታታት እንጂ እነርሱን ለማጥፋት ወይም ለማፈን ሲባል የተቋቋሙ አይደሉም። ተግባራዊ እንቅስቃሴያቸው የሚመሰክረውና የሚያረጋግጠው ነገርም ይህንኑ ነው። ኢኮኖሚውን ለመቆጣጠር የሚባለው ጉዳይ ደግሞ የእነሱ አቅም በጣም ውሱን የአገሪቱ ድልብ አቅም ግን ሰፊ በመሆኑ እንደዚያ ማድረግ ቢፈልጉም በአቅም ማነስ ሳቢያ

ሊፈፅሙት አይችሉም። በተግባርም ኢኮኖሚውን ሊቆጣጠሩ፣ ባለሃብቶችን ሊያሳፍኑ ነው የተጀነሱት በማለት የሚናፈሰው አሉባልታ ምንም መሰረት እንደሌለው ያሳያል።"

ሲላይ አንገቱን ከግራ ወደ ቀኝ እየነቀነቀ መኪናውን መንዳት ቀጠለ። ሩብ ሰዓት ከማይሞላ የመኪና ጉዞ በኋላ አንድ ገዘፍ ያለ የቻይና ሬስቶራንት ሲደርስ መኪናውን አቆመ። አድራሻውን ካረጋገጥን በኋላ ተያይዘን ወደ ውስጥ ገባን። ፊት ለፊት በሩ ላይ አንዲት በቻይና ቀይ ደማቅ ልብስ ያሸበረቀች አይነ ትንንሽ ሴት ፊታችን ተደቀነች። እድሜ ለቻይና የሳምንት ቆዞ "ኒሃ-ሃ" አልኳት፡ እሷም በፈገግታ የአፀፋ መልስ ሰጥታን እንድንከተላት አደረገች። መመገቢያው ክፍል ስንደርስ በፈገግታና ክብር የሚመለከተን ሰው ተመለከትኩ። ሰውየው ገና እኛን ሲመለከት ከመቀመጫው ተነስቶ ቆመ። እሁንም ድረስ ምላሽ ያላገኘሁለት ሰውነቴን ውርር የሚያደርግ ስሜት ተሠማኝ። እንደምንም ራሴን ለመቆጣጠር ጥረት እያደረኩ ሒጄ ተጠመጠምኩበት። ከመቅፅበት በርካታ ትዝታዎች አእምሮዬ ላይ መንከላወስ ጀመሩ። በትዝታ ይዞኝ ነጎደ።...ኃይለኛዋ እናቴ እቴነሽ ቸርነት፣ የአብርሃም በግ የነበረው (የሆነው) አባቴ ለገሰ ዋቅጅራ፣ የአባቴ ወንድሞች (ቤኛ፣ ለሜቻ፣ ጃንቦ፣ ተሬሳ)፣ የጌጃ ሽማግሌዎች፣ አዋሽ ወንዝ... መጥፎ ትዝታ። ዛሬ ብዙዎቹ የሉም። እናቴ፣ አባቴ፣ ቤኛና ለሜቻ ያለጊዜያቸው ሔደዋል። የእናቴ በርሜሎች በአፋቸው ተገልብጠዋል። ያለምንም ጥርጥር ብዙዎቹ የጌጃ ሽማግሌዎች ከመሬት በታች ውለዋል። ምን አልባት በህይወት ያለው የአዋሽ ወንዝ ሊሆን ይችላል። በድሮ ክብሩና ውበቱ መኖሩን ግን እጠራጠራለሁ። አዋሽ እንደትላንቱ የጌጃን ህዝብ "እካእ ያቢራ" እያስባለ ያስጨፍር ይሆን? ...ብንበስ ግድያ የሚፈላለጉ የህገሬውን ሰዎች እያማማለ ያስታርቅ ይሆን? ...ወይንስ እሱም እንደዘመኑ "የሰው ግብር" እየበላ ዝም ብሎ ይጓዝ ይሆን? ...አላውቅም።

እናም አጭሩ ሰው ባልጠበኩት ትዝታ እንድመታ አደረገኝ። ከማልቀስ በመለስ ባለ ስሜት ውስጥ ሆኜ እቅፍ አደረኩት። ጨመኩት። ወደ ጆሮው ተጠግቼ "ገብረየስ ኬኛ! ገብረየስ የኛ!" አልኩት። ድሮ የምንተዋወቅ ይመስል የአባትና የልጅ ሠላምታ ተለዋወጥን። ለጥቂት ጊዜያት ወጋችን በሙሉ አዋሽ-ጌጃ ሆነ። ...የጌጃ ህዝብ የኩራት ምንጭ እንደሆነ ነገርኩት። እርግጥም በአንድ ጊዜ ከሁለት መቶ በላይ የገበሬ ልጅን ከአፈር መገፋት አላቆ ላብአደርና ከተሜ እንዲሆኑ ጥረት ያደረገ ሰው ቢመኩበት የሚያስደስት ነው። ...እርግጥም ለገበሬው ማዳበሪያ ማጭድና ዶማ የመሳሰሉ የእርሻ ግብአቶች ለመላው ኢትዮጵያ የሚያቀርብ ሰው ልጃቸው መሆኑ የሚያኮራ ነው። የጌጃ አዛውንቶች ለልጆቻቸውና የልጅ ልጆቻቸው እንድ እነሱ ያሳደጉት ሰው ከአንዲት የደሃ

ሳሎን የሚታከል ክፍል፣ አንድ ጠረጴዛና ወንበር ተነስቶ በግል ጥረት የበርካታ ኩባንያዎች ባለቤት መሆን እንደ ስኬት ማስተማሪያ ሲያቀርቡ የልብ ሙላት እየተሰማቸው ነው።

በሌላ በኩል የህወሓት ቋንቋ መናገር ባለመቻሉ ምክንያት ኢንቨስትመንቱ እንደ አውሬ እየታደነ እንዲከስም መደረጉ ድፍን ለጌጃ ህዝብ የእግር እሳት መሆኑ አልቀረም። ስለ ኢትዮጵያ ህዝብ ራዕይ የሌላቸው ህወሓቶች እነሱ የከፈቷቸው የንግድ ድርጅቶች እንዲፋፉ "በኢኮኖሚያዊ መሳሪያዎች" በመጠቀም ከገበያ ውጭ ሆኖ መመልከት በጣም ያናድዳል። ያስቆጫል። ህዝቡ "የገብረየስ ቤኛ ስም ገረንቹል ኪሮስ ቢሆን ኖሮ ይሄን ያህል መከራ አይደርስበትም ነበር" በማለት የሚናገረው ውሳኔው በዘር ላይ የተሞረኮዘ እና ፖለቲካዊ ስለሆነ መሆኑ የሚያጠያይቅ አይደለም። እውነትም በገብረየስ ቤኛ ላይ የተሰራው የኢኮኖሚ ሻጥር ከአዋሽ ወዲህ ማዶ ለሚኖረው ህዝብ ለዘመናት በምሬት የሚታወስ ነው።

363

ከአዛውንቱ ኢትዮጵያዊ ገብረየስ ቤኛ ጋር ከነበረኝ ቆይታ እንደተረዳሁት ታሪኩን በመጽሐፍ መልክ እያዘጋጁ መሆኑ ነው። ይህ ለትውልድ ማስተማሪያ እንደሚሆን የምጠብቀው መጽሐፍ በርካታ ቁም ነገሮችን እንደሚዳስስ ተስፋ አደርጋለሁ። በዚህም ምክንያት ከአዛውንቱ ጋር የነበረኝ ቆይታ ራሱን በቻለ መድብል ልዳስሰው የነበረኝን ፍላጎት እንድተወው አድርጎኛል። ...ባይሆን ኖሮ ቀዳማዊ ኃይለስላሴ "እኛ ከትልቅ ሠው ከመወለድ ይልቅ ከስራ መወለድ የምንለውን የፈጸምክ ነህ! በማለት ገብረየስ ቤኛን የተናገሩት ራሱን የቻለ ምዕራፍ ይሆን ነበር። እዛው ሳለ የንጉሱ ስርዓት እና ብሔራዊ ክበርቴው የነበራቸውን ተዛምዶ በሠፊው እመለከት ነበር። ...ባይሆን ኖሮ "ከሻንቆ ወደ ፈይሳ፤ ከፈይሳ ወደ ገብረየስ" የሚል የስም ለውጥ እንዴት እንዳደረገ እመለከተው ነበር።

(በነገራችን ላይ የጌጃ ሰው ለልጆቹ የቤት ስም ማውጣት ልማዳዊ ይመስላል። በጥናት ያረጋገጥኩት ባይሆንም ቅፅል ስም የሌለው ሠው ማግኘት አይቻልም። ለምሳሌ የአባቴ ሀገር ሰዎች እኔን "ካዬ" ብለው ይጠሩኛል። ከጌጃ ተሻግሮ የወይራ ሰፈር ሰውም "ካዬ" በሚለው ስም ይጠሩኝ ነበር። አሁንም በዚህ ስያሜ የሚጠሩኝ አሉ። 'ካዬ' ቀጥተኛ ትርጉሙም ባይሆን 'አላማ' ማለት እንደሆን የጠየኳቸው ሠዎች ነግረውኛል።)

የሆነው ሆኖ የአዛውንቱ ገብረየስ ቤኛ ታሪክ ባህር ነው። በትምህርት ቤት እያለን ስለ ኢንተርፐንር ጭንቅላት" የተማርነው የንድፈ-ሃሳብ ትምህርት በተግባር ገብረየስ ላይ ይገኛል። በአጭር ሰዓት ውስጥ ስለ ራዕይ፣ ስለ ሁኔታዎችና አዋጭነት ጥናት፣ ስለ ስትራቴጂና ታክቲክ፣ ስለ ተባብሮ መስራት፣ ስለ ጤናማ ውድድርና አሸንፎ የመውጫ መንገዶች፣ ስለ ሙያተኛ መጠቀም... ወዘተ በአዛውንቱ የሕይወት ጉዞ ውስጥ የእለት ተእለት ክስተቶች መሆኑን በአጭር ጊዜ መረዳት ይቻላል። ሰውየው! የዋዛ አይደለም። ውሳኔ ሲሰጥም ቆራጥ ነው። የውሳኔው ማዕከል ሥጋዬ፣ ዘመዴ፣ የመንደሬ ልጅ በሚል ሳይሆን ስራና ስራን ብቻ ማዕከል ያደረገ ነው። መደበኛ ስራውን ያለከበረና ተደጋጋሚ ጥፋት የሰራ ይባረራል- Zero-tolerance!

(ሙቹም ስለ ጌኝ ሰው ኃይለኛነት ነዋሪውን የሚያውቅ ሁሉ ይመሰክራል። ይህን ቢያውቅም ገብረየስ ቤኛ የአካባቢውን ነዋሪ ለመጥቀም ካለው ፍላጎት በመነሳት 200 ለብአደር ከጌኛ አምጥቶ ታሜ ፋብሪካ ያስገባል። የገጠሩ ኃይለኝነት ያልለቀቀው የጌኛ ሰው ለዓትና ጊዜ ሳይመርጥ በዱላ ይከታከታል። በዚህም ምክንያት የፋብሪካው ስራ ማበደል ይጀምራል።ቆራጡ ሙሪ ከረጅም ጊዜ ትዕግስትና ምክር በኋላ የተለወጠ ነገር ባለመኖሩ 200 ከጌኛና ጌኛ ሠፈር ያመጣቸውን ሠራተኞች ከስራ አሠናበተ። ለጥቂት ቀናት በአዋሽ ወንዝ ውስጥ ያለው ድንጋይ ውሃውን አናገረ። አዋሽ ድምፅ አሠማ!!)

ገብረየስ ኬኛ! በቤተሰባዊ ሕይወቱም ስኬታማ ነው። ሁሌም አዲስ ሕልም አዲስ አቅጣጫ ለመያዝ የማያንገራግረው ሰው ቤተሰቦቹንም በዛ መንገድ ለመምራት አስችሎታል። ዘማየት ብዬ ማጣራት እንደቻልኩት ሴት ልጁ ፀጋ ገብረየስ "የአፍሪካ ስኬታማ ባለፀጋዎች" የሚለው ሊስት ውስጥ በግንባር ቀደምትነት ትገኛለች። ለአፍሪካ ዴሞክራሲ መምጣት የሚያበረታታው የሱዳናዊው ሞህ ኢብራሂም "ሞህ ፋውንዴሽን" የአመራር አባል በመሆን ታገለግላለች። እንደሚታወቀው "ሞህ ፋውንዴሽን" ጊዜያቸውን ጠብቀው መሪነታቸውን ለሚለቁ የአፍሪካ ፕሬዝዳንቶች (ርዕሠ- መንግስታት) በርካታ ሚሊዮን ዶላር ሽልማት የሚሰጥ ተቋም ነው። የአፍሪካ የዴሞክራሲ ጉዞንም በየጊዜው እየተከታተለ ሪፖርት ያቀርባል።

ስለ ገብረየስ ኬኛ! ለመንደርደሪያ ይሔን ያህል ካልኩኝ ወደ ሚቀጥለው ጉዳያችን እንመለስ። መነሻችን ህወሓት "ኢኮኖሚያዊ መሳሪያዎች" በሚል አገላለጥ ቀድሞ የነበሩ ብሔራዊ ከበርቴዎችን እንዴት ገፍትሮ ከኢትዮጵያ ኢኮኖሚ እንደሚያስወጣ የገለጥንበት ነው። እነዚህ

ኢኮኖሚያዊ መሳሪያዎች እንደ ኤፈርት ያሉ የህወሓት ኩባንያዎች (የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ኃይሎች) ሌሎች ሀገራዊ ባለሀብቶችን እንዴት ከገበያ እንዲወጡ በማድረግ በምትካቸው እነሱ ብቻ በሞኖፖሊ ጠቅልለው የሚይዙበት ሁኔታ የሚፈጥሩበት አሠራር መሆኑን ተመልክተናል። በዚህ መልኩ በተቀነባበረ ሴራ ከሀገር እንዲወጡ ከተደረጉት ኢትዮጵያውያን መካከል ገብረየስ ቤኛ ይገኙበታል።

ታሪኩ በአጭሩ ይሔን ይመስላል፡-

ገብረየስ ቤኛ በንጉሱ ዘመነ መንግስት በ1956 ዓ.ም. ላይ አንድ ሃሳብ ይመጣበታል። የኢትዮጵያ አማልጋሜትድ ኩባንያ ማቋቋም። ኩባንያውን ለማቋቋም ከሦስት ሰዎች ጋር ሽርክና ይፈጥራል። ሀሳቡ ትልቅ ቢሆንም ኢትዮጵያ አልጋሜትድ በአንዲት ከኩሽና በላይ የዘለለ ስፋት በሌላት ክፍል ውስጥ በአንድ ወንበርና ጠረጴዛ ተጀመረ። የኩባንያው ስራ አስኪያጅ ገብረየስ ቤኛ ሆኑ፡፡ እንግዲህ በዚህ መልኩ የተቋቋመው ድርጅት በአጭር ጊዜ ውስጥ እድገት በሚሳየት በእርሻ ኢንዱስትሪ ምርትና አገልግሎት፣ በወጪ ገቢ ንግድ፣ በማዳበሪያ አቅርቦት፣ በጎማ ንግድ፣ በምፅዋ፣ አሰብና ጅቡቲ እቃ ማስተላለፍ (ትራንዚት) አገልግሎት፣ በብረታ ብረት አገልግሎት (ኢትዮጵያ ሜታል ቱልስ)፣ ... ወዘተ ኢንቨስትመንቶች ግንባር ቀደም ሆነ፡፡ ኩባንያዎቹ እንደ ሚስትቡሺ ያሉ የውጭ ኩባንያዎች ጋር ሽርክና በመፍጠርና የውጭ ባለሞያ በመቅጠር ገበያቸውን በኢትዮጵያ ብሎም በአፍሪካ ማስፋት ቻሉ። የንጉስ ነገስቱ አስተዳደር በኢንቨስትመንቱ በመደነቅ በርካታ ማበረታቻዎችን መስጠት ጀመሩ። በአካልም እየተገኙ ያጋጠማቸውን ማነቆ እስከ መፍታት ደረሱ። በተለይም የጎማ ፋብሪካው ሲቋቋም ቀዳማዊ ኃይለስላሴ በቦታው በመገኘት የጌጃውን መመኪያ አሞካሹ። "እኛ ከትልቅ ከመወለድ ከስራ መወለድ የምንለውን የፈፀምክ ነህ!" በማለት ታሪካዊ ንግግር አደረጉ።

በዚህ መልኩ እየተመነደገ የሔደው አማልጋሜትድ በደርግ ዘመን እክል አጋጠመው። ደርግ የሚከተለው አይዲዮሎጂ የግል ኢኮኖሚን የሚያቀጭጭ የእዝ ስርዓት በመሆኑ የተለያዩ አዋጆችን በማውጣት የአልጋሜትድ ኩባንያዎችን ወረሠ። በከፍተኛ ኢንቨስትመንት ውስጥ እንዳይሳተፉ የስራ ፈቃዳቸውን ሠረዘ። ይህም አልበቃ ብሎ ገብረየስ ቤኛን "አቆርቋዥ ነጋዴ" በማለት ወደ ወህኒ ቤት ወረወረ። የመንግስቱ ኃይለማሪያም ስርዓት የነበረውን እንዳልነበረ አደረገ። እስከ አፍሪካ ዘልቆ በመሔድ የማዳበሪያ ስርጭት ሲያደርግ የነበረው አማልጋሜትድ የጭካኔ በትር አረፈበት።

የሆነው ሆኖ ደርግ ያደረገውን አድርጎ ገብረየስ ቤኛን እስር ቤት ወረወረ። እንደሌሎች ፖለቲካ እስረኞች የፍርድ ቀኑን ሲጠባበቅ ያልተጠበቀ ነገር ተፈጠረ።

“የጊጃው ንጉስ” የነበረውን አጋጣሚ ለእኔ እና ሲሳይ አጌና እንዲህ በማለት አጫወተን፣

“ልጆቼ! የእኔ ሕይወት በመጥፎም ሆነ በጥሩ ከማዳበሪያ ጋር የተያያዘ ነው። ሚሊኔየር በመሆን ወደ አለም ገበያ እንድገባ ካደረጉኝ ምርቶች ዋነኛው ማዳበሪያ ነው። የአገሬ ገበሬ ማዳበሪያ ተጠቅሞ ምርቱ ሲትረፈረፍለት የሚሰማኝ ደስታ በቃላት የሚገለፅ አይደለም። የኢትዮጵያ አርሶ አደር የኩባንያችንን ማጭድ፣ ዶማ፣ የመሳሰሉትን የእርሻ መሳሪያዎች ተጠቅሞ ሲሰራ ስመለከት የሚሰማኝ ጥሩ ስሜት ወደር የለውም። ...በተለይ ማዳበርያ የኢትዮጵያን ጠቅላላ ህዝብ የመኖር ጥያቄ ስለሚያስነሳ ከሕይወቴ ውጣ ውረድ ጋር መተሳሰሩ ተገቢነት ያለው ይመስለኛል።...

“እናም! ከሕይወቴ ጋር የተጣበቀው ማዳበሪያ ከእስር አስፈታኝ። ከደርግ እስር ቤት የወጣሁት ከማዳበሪያ ጋር በተያያዘ ነው። በዚያን ዘመን በእስራኤልና አረቦች ጦርነት ምክንያት የነዳጅ እቀባ ተደርጎበት ነበር። የማዳበሪያ እጥረት በመከሰቱ ምክንያት ደርግ ማግኘት ተሳነው። ችግር ላይ ወደቀ። ስለዚህ አማልጋሜትድ ቀድሞ በፈጠረው አሠራርና አስቀድሞ የሚያዝ ገንዘብ ስለነበረው ማዳበሪያውን ወደ ሀገር ቤት እንድናመጣ ደርግ ጠየቀኝ። የእኔ በቦታው መገኘት ግዴታ ስለነበር ከእስር ቤት ለቀቁኝ። በእርግጥም ገበሬው እንዳይጎዳ ማዳበሪያውን ማምጣት አለብኝ የሚል ውሳኔ በውስጤ አንግቤ ወደ ውጭ ሀገር ሔድኩኝ። ይሁን እንጂ ውጭ ሀገር በደረስኩ በሁለተኛው ሳምንት አስደንጋጭ ዜና ሰማሁ። ከእኔ ጋር ታስረው የነበሩት የ60ዎቹ የንጉሰ-ነገስቱ ባለስልጣናት መረሸናቸው ተነገረ። የኮሎኔል መንግስቱ ኃይለማሪያም ጭካኔ ጭንቅላቴን በጠበጠው። እነዚያን የመሰሉ ታላላቅ ሰዎች መረሸን የጤነኛ አእምሮ ውሳኔ እንዳልሆነ ተገለጠልኝ። ከዚያ በኋላ ስደት ምርጫዬ አድርጌ ከኢትዮጵያ እንደወጣሁ ቀረሁ” በማለት ተናገረ።

ከጥቂት ደቂቃዎች ዝምታ በኋላ የአባቴ ሀገር ሰው እንዲህ በማለት ቀጠለ፣

“ልጆቼ! ...ሕይወቴ ከማዳበሪያ ጋር የተጣበቀ ነው። ደርግ በአማልጋሜትድ ኩባንያ ምክንያት ከርዕዮተ አለሙ ተነስቶ አሰረኝ። የሚይዘው የሚጨብጠው ሲያጣ ከእስር ፈቶ

እንድሰደድ ሆንኩኝ። ዛሬ ደግሞ በኢህአዴግ ዘመን ("ነፃ ገበያ ቢታወጅበት!") በድጋሚ ሀገር እስጥሎ አሰደደኝ" በማለት ገለፀ።

እንደ እውነቱ ከሆነ የህወሓትን አብዮታዊ ዲሚክራሲ የእስተሳሰብ ልዕልና ከማረጋገጥ አኳያ "የማዳበሪያ ፖለቲካ" ወሳኝ ነው። ከኢትዮጵያ ህዝብ ውስጥ 85 ሚሊዮን የሚሆነውን አርሶ አደር ማዕከል ያደረገ የፖለቲካ እና የኢኮኖሚ ስራ በአመለካከትም ሆነ በገንዘብ ምንጭነት እጅግ በጣም ከፍተኛ ነው። የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ዋነኛ የኢኮኖሚ ኃይል የሆኑት ኢፈርትና የመሳሰሉት ኩባንያዎች በዚህ ህብረተሰብ ላይ የሚፈጥሩት ገበያ አጠቃላይ እድገታቸውን የሚወስን ተደርጎ ሊወሰድ የሚችል ነው። የአርሶ አደሩ ሰፊ እና የማያቋጥር የማዳበሪያ ፍላጎት እዛው ላለ የብድር ጥያቄን እንግበ ስለሚመጣ የገበሬውን ምርት በቀላሉ ለመመዝበር እድል ይከፍታል። በዚህም ምክንያት በአርሶ አደሩ ምርት ዋነኛ ተጠቃሚዎቹ ማዳበሪያ እና ብድሩ የሚሰጡት ይሆናሉ። በመሆኑም በአምራችና ሸማች መካከል የሚኖረው የገበያ ህግ የሚመራው በእነዚህ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ኃይሎች ወሳኔ ይሆናል። ገበሬው ሳይወድ በግድ እህሉን ለእነዚህ ኃይሎች አሊያም እነሱ ባስቀመጡለት የገበያ ዋጋ ይሸጣል።

ገብረየስ ቤኛ እንደገለጠልን ከሆነ የኢትዮጵያ ገበሬ አመታዊ የማዳበሪያ ፍላጎት 14 ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን ያህል ይሆናል። ይህን የማዳበሪያ ፍላጎት መሟላት የሚችለው ከውጭ በማስገባት ብቻ ነው። ማዳበሪያውን ለማምረት ጥሬ እቃ በኢትዮጵያ ገና ባልተገኘበት ሁኔታ በአገር ውስጥ ምርት መሸፈን አይቻልም። በሌላ በኩል የገበሬው የማዳበሪያ ፍላጎት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ሄዷል። በአሁን ሰዓት የገበሬ ምርት ይጨምር ከተባለ የግድ፟ታ ማዳበሪያ ያስፈልገዋል። እንደዚህ በመሆኑ ምክንያት በኢትዮጵያ የገበያ ሁኔታ የማዳበሪያ አቅርቦት ከአገሪቱ ፍላጎት ጋር የሚጣጣም አይደለም። አቅርቦቱ ዝቅተኛ በመሆኑ ምክንያት ገበሬው በውድ ዋጋ ማዳበሪያውን እንዲገዛ ይደረጋል። በዱቤ እና ከፍተኛ ዋጋ በመግዛቱ ምክንያት ገበሬው እህሉን ወደ ገበያ አውጥቶ ሲሸጥ በውድ ዋጋ ስለሚሆን ሸማቹም በተመሳሳይ ይጎዳል። በእነዚህ መሀል ዋነኛ ተጠቃሚ የሚሆነው የማዳበሪያ አከፋፋዮቹ ናቸው። የማዳበሪያ ግዥውንና የማከፋፈሉን ስራ በሞኖፖሊ መያዝ የሚችሉ ድርጅቶች እያንዳንዱ ገበሬ ኪስ በመግባት የማይነጥፍ ንዋይ መሰብሰብ ይችላሉ። በተለይ ሀገራዊ ፍቅር የሌላቸው፣ ትርፍ ከማግበስበስ ውጪ የሞራል ለከት የሌላቸው ድርጅቶች ከሆኑ የገበሬውንና ቤተሰቡን እጥንት እስከመጋጥ ይደርሳሉ።

እንግዲህ የኤፈርት ኩባንያዎች የሆኑት እነ ጉና ኢንተርፕራይዝ "ኢኮኖሚያዊ ኢንስትሩመንት" አማልጋሜትድ ላይ ለመጠቀም ያነሳሳቸው ከላይ የሰፈረው እውነታ ነው። መጀመሪያ አካባቢ የአሊጋሜትድ ኩባንያን መልካም ስም ለማጥፋት በመለስ ዜናዊ የተቀነባበረ ፕሮፖጋንዳ ተጀመረ። የኢትዮጵያ አማልጋሜትድ የኢምፔሪያሊዝም እና ጥገኛ ካፒታሊዝም ቅጥረኛ ነው የሚል ስም ማጥፋት በውስጠ ድርጅትና በመንግስት መዋቅሩ እንዲዛመት ተደረገ። ምዕራቡ አለም (ኒዮ-ሊብራል) የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ኃይሎችን ለመድፈቅ ግዙፍ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ አቅሙን በአማልጋሜትድ አማካኝነት ሊጭን እንደሆነ ተነገረ። ኪራይ ሰብሳቢው ኃይል የአብዮቱ ማህበራዊ መሰረት የሆነውን አርሶ አደር በተዘዋዋሪ ተቆጣጥሮ ዘላቂ ህልውናችንን ሊያጠፋ እነደሆነ በውስጡ ድርጅት ሰነድ ተዘጋጅቶ ኢንዶክትሪኔሽን እንዲሰራበት ተደረገ። የመንግስታዊ ስልጣኑን "ለኢኮኖሚ መሳሪያዎች" ከመጠቀም አኳያ ጠቅላይ ሚኒስትሩ "የኢትዮጵያ አማልጋሜትድ ከፍተኛ የስነ-ምግባር ችግር ያለበት ድርጅት ነው" የሚል ማዕከላዊ መልዕክት የያዘ ደብዳቤ ለሚመለከታቸው የመንግስት ተቋማት እንዲደርስ አደረገ።

የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስትሩ አቶ ግርማ ብሩ በኢትዮጵያ ቴሌቭዥንና ሬዲዮ ላይ ቀርቦ የድርጅቱን ቃል ሳይጨምርና ሳይቀንስ "የኢትዮጵያ አማልጋሜትድ ህገወጥ እንቅስቃሴ እያደረገ ነው" የሚል መግለጫ ሰጠ። ጥብቅ መመሪያ የተሰጣቸው የመንግስት ተቋማት አማልጋሜትድ ኩባንያን እየተከታተሉ ማጥቃት ጀመሩ። ኩባንያው ከ100 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ አውጥቶ ወደ ኢትዮጵያ እያመጣ ያለው ማዳበሪያ ገና ፖርት ሳይደርስ የተበላሸ እንደሆነ ተነገረው። "የትኛው የኢትዮጵያ የደረጃ መዳቢ ነው በውቅያኖስ ላይ እየተጓዘ ያለን ማዳበሪያ ደረጃውን ያልጠበቀ ሊል የሚችለው?" የሚለው ጥያቄ ምላሽ ሳይሰጠው ቀረ። በእንደዚህ አይነት ህጉወጥ እርምጃ ማዳበሪያው ሀገር ውስጥ እንዳይገባ ተደርጎም ብድር የሰጠው የመንግስት ባንክ አዳውንና ወለዱን መቁጠሩን አላቆመም። የሒሳብ መዝገቡ እና የኦዲት ሪፖርቱ የኪሳራውን ሁኔታ በግልፅ እያመለከተ ብድር ሰጠሁ ያለው ባንክ በወለድ የተቆጠረውን ከ140 ሚሊዮን ብር በላይ እንዲከፍል አማልጋሜትድ ማንቋርት ላይ ቆመ።

በመንግስት ተከታታይ እርምጃ ቅሬታ የገባው ንብረየስ ቤኛ የውሳኔውን ፍትሐዊነት ማጣት እና ኢ-ህጋዊነት ለማሳየት "ለተወዳጁ ፓርላማ!" በጽሑፍ አቀረበ። ድርጅቱ ለኪሳራ በመዳረጉ ምክንያት የኩባንያው ሰራተኞች ወደ ስራ አጥነት እየሄዱ በመሆኑ በእነርሱ ሆነ በቤተሰቦቻቸው ላይ የተደቀነው አደጋ "ተወዳጁ ፓርላማ!" ትኩረት ሰጥቶ እንዲወያይበትና

አስፈጻሚው አካልን ጠርቶ (እነ አቶ መለስን ማለት ነው) ምላሽ እንዲሰጡ እንዲያደርጉ ይማፀናል። ፍትህ እንዳይጓደል፤ ከተጓደለም እንዲስተካከል ተብሎ የተቋቋመው "ፍትህ ሚኒስቴር" በደሉን በጥሞና እንዲመለከትና የፍትህ አጡቱን እንዲቀርፍ ይጠይቃል። ለዚህ ጥያቄ ቢሆን የመንግስት ምላሽ የውሃ ሽታ ይሆናል።

ሁኔታዎች እየከፉ ሲሄዱ የአማልጋሜትድ ባለቤቶች ወደ አለም አቀፍ ተቋማት ቅሬታቸውን ይዘው ይሔዳሉ። የአቶ መለሰ መንግስት ለአለም አቀፍ ሕግጋትና የንግድ ነፃ መርሆዎች እንዲያከብር ጣልቃ ገብተው እንዲናገሩ ተማጽኖ ያቀርባሉ። ለማዳበሪያ ግዥ ብድርና እርዳታ የሚሰጡት የአለም አቀፍ ተቋማት ስለነበሩ የኢትዮጵያ መንግስት ላይ ተጽእና ሊያሳድሩ እንደሚችል ተስፋ ይሰንቃሉ። ቢያንስ በአይ. ኤምኤፍ እና አለም ባንክ ታዛቢነት በኢትዮጵያ መንግስት የተካሄደ ግልፅ ጨረታ አማልጋሜትድ አሸናፊ ሆኖ ከቀናት በኋላ የተሰረዘውን ወደ ነበረበት እንደሚመለስ እምነት ያሳድራሉ።

የሆነው ግን ሌላ ነበር።

አቶ መለሰ በአለም አቀፍ ተቋማት ፊት ተወቃሽ ሆኖ መቅረቡ የቆሰለ አውሬ አደረገው፡ የኒዮ- ሊብራሎች ጣልቃ መግባት እንደመደፈር ቆጠረው። ይህች ባቂላ እንዲሉ በእነዚህ የኪራይ ሰብሳቢነት ትሮይ ፈረሶች መሸነፍ ማለት ነገ ከነገወዲያ የእነሱ ተቀጥላ መሆንና በገመዳቸው ተጠልፎ ከመውደቅ ጋር እንደሚስተካከል አድርጎ ወሰደው። ከዚህ በመነሳት የአለም አቀፍ ተቋማቱን ጥረት ውጤት አልባ አደረገው።

ከእለታት በአንዱ ቀን ገብረየስ ኬኛ! አንዷት አፍሪካ ሀገር የሚደረግ አለም አቀፍ ስብሰባ ላይ ይጋበዛል። በስብሰባው ላይ የአፍሪካ ሀገር ሚኒስትሮችና የሚመለከታቸው ባለስልጣናት የሚገኙበት ነበር። ገብረየስ ይህን በልማትና እድገት ላይ የሚመከር ስብሰባ ለመሳተፍ በሰማዩ ጋሪ ጉዞ ይጀምራል። የኢትዮጵያ ልዑካንን በመወከል የሚሳተፉት ዶ/ር ካሱ ኢላላም በተመሳሳይ አውሮፕላን ይሳፈራሉ። የአጋጣሚ ነገር ሆኖ የዶ/ር ካሱ እና የገብረየስ መቀመጫ አንድ ላይ ይሆናል። ይህን የተመለከተ አንድ ባለስልጣን ወደ ሚኒስትር ካሱ እና ገብረየስ በመቅረብ "ክቡር ሚኒስትር! አጠገብ ያሉት እኮ የኢትዮጵያ አማልጋሜትድ ኩባንያ ባለቤት የሆኑት ክቡር አቶ

ገብረየስ ቤኛ ናቸው። የምትተዋወቁ መስሎኝ ነበር" በማለት እየተሟወቱ መንገዱን እንዲያዘጋው ይናገራሉ።

በለስልጣኑ ገና ንግግሩን እንደጨረሰ የሚኒስትር ካሱ ኢላላ ፊት ሳንባ ይመስላል። እንደ ፈረስ ማናፋት ይጀምራል። እንደ ህጻን ልጅ ተቆናጥሮ ከተነሳ በኋላ የምንተአፍረቱን ፊቱን አዙሮ ይቆመጣል። ከጳጳሱ ቁሱ የሆነበት የአዋሽ-ጊጃው ልጅ ግራ በመገባት ይከታተለዋል። ከትንሽ ዝምታ በኋላ ሚኒስትር ካሱ ፊቱን ማልሶ በማዞር ቁጣና ስድቡን ያወርዳል። "በአለም አቀፍ ተቋማት ፊት ለምን ታሳጣናለህ?" በማለት ይናገራል።አብዮታዊ ዴሞክራሲ ሰማይ ዝቅ ምድር ከፍ ቢል የሚፈራው ነገር እንደሌለ አስረግጦ ይናገራል። ገብረየስ በበኩሉ መንግስትን አክብሮ በአካልና በደብዳቤ ደጋግሞ ቢጠይቅም ምንም ምላሽ እንዳላገኘ ይገልጣል። " ክቡር ሚኒስትር!" የሚመሩት ቢሮም መቅረቡን ጨምሮ ይናገራል። ሆኖም ግን "ክብር ሚኒስትሩ!" የሚያገለግሉት መንግስት ለፍትህና አለም አቀፍ ህግጋት ተገዢ መሆን ባለመቻሉ ለሚመለከታቸው የውጭ ተቋማት አቤቱታውን እንዳቀረበ በጥሞና ያስረዳል።

"ክብር ሚኒስትሩን!" የሚያስጨንቃቸው የፍትሕ መጓደሉ ሳይሆን እንደ አምላክ የሚመለከቱት ሰው በመሆኑ ከብስጭታቸው መውጣት አልቻሉም። ሚኒስትር ካሱ አማሊጋሜትድ መንግስት ሆነ ብሎ ወደኪሳራ እንዲሄዱ አድርጎና የወለድ ቁልል ከምሮ ከገበያ እንዲወጡ መደረጉን ቢያውቁም የሚሰጡት ምላሽ የላቸውም።...በኢትዮጵያ ኢኮኖሚያዊ ህይወት ውስጥ ወሳኝ ሚና ያላቸው እንቅስቃሴዎች በኤፈርት ቁጥጥር ስር እንዲሆኑ የተቀመጠውን አቅጣጫ ስለሚያውቁ በእውነተኛ ህሊናቸው ሊናገሩ አይችሉም። ...ዶክተር ካሱ ኢላላ በኢህአዴግ ጉባኤ የፀደቀውን "የውጭና የገቢ ንግድ፣ በጅምላ ሽያጭ ...ወዘተ ቁልፍ ሚና ያላቸው ምርቶች በአብዮታዊ ዴሞክራሲ ኃይሎች ቁጥጥር ስር መዋል አለባቸው" የሚለውን ፕሮግራም ግራ እጃቸውን አውጥተው ስላፀደቁ ለገብረየስ ቤኛ ተገቢውን መልስ መስጠት አይችሉም።

"ክቡር ሚኒስትር!" ፊታቸውን እንደቀለሉና እንዳኮረፉ ምድር ደረሱ። ለገብረየስ ሰላምታ ሳይሰጡና በጥላቻ አይን እየተለመከቷቸው ኤርፖርቱን ጥለው ሄዱ።

ኮንፈረንስ ተጀመረ።

እነሆ! በአፍሪካ ኢንቨስትመንትና ልማት ላይ የሚያተኩረው ኮንፈረንስ ተጀመረ። ዶ/ር ካሱ ከተወሰኑ ተናጋሪዎች በኋላ "የክቡር ዶክተር ሚኒስትር!" ካሱ ኢላላ ተራ ደረሰ። ዶ/ር ካሱ

ስለኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ሰፊ ማብራሪያ ከሰጡ በኋላ እጃቸውን ወደ ገብረየስ ቤኛ አየዘረጉ፣

"የኢትዮጵያ መንግስት የሀገሪቱን ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ነፃነት የሚያረጋግጥ፣ ድህነትና ኋላ ቀርነትን የሚያስወግድ፣ የህዝቡን መሰረታዊ ፍላጎት ለማሟላት ቀን ከሌት የሚሰራ ነው። ይህንን ትልቅ አላማ ከግብ ለማድረስ የግል ባለሀብቶችና ኢንቨስተሮች የማይተካ ሚና ያላቸው የኢኮኖሚው ሞተር እንደሆኑ ያምናል። በዚህም ምክንያት የግል ባለሀብቶች የካፒታል ገደብ ሳይደረግባቸው ካፒታላቸውን አስማርተው ተጠቅመው እንዲጠቅሙ ሰፊ እድል ሰጥቷቸዋል። ለዚህ አባባል ጥሩ ምሳሌ የሚሆኑት በዚህ ስብሰባ ላይ የተገኙት የኢትዮጵያ አማልጋሜትድ ኩባንያት ባለቤት የሆኑት ክቡር አቶ ገብረየስ ቤኛ ናቸው። መንግስት በፈጠረላቸው እድል ኢትዮጵያ ውስጥ ኢንቨስት አድርገው ተጠቃሚ ሆነዋል" በማለት ተናገሩ።

የሌባ አይነደረቅ..!!

አሁን ሊነሳ የሚገባው ጥያቄ ማዳበሪያ አስመጥቶ ማሰራጨት ላይ የተሰማራው አማልጋሜትድ ለምን በኪሳራና ከአቅም በላይ በሆነ ወለድ ከገበያ እንዲወጣ ተደረገ የሚለው ነው። አስቀድሞ እንደተገለጠው የማዳበሪያ ጉዳይ በኢትዮጵያ ውስጥ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ እንድምታው ከፍተኛ ነው። በአንድ በኩል የኢትዮጵያን ገበሬ ማዳበሪያ በመስጠትና በመንፈግ ወደሚፈልገው የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ፍላጎት መውሰድ ይቻላል። በመሆኑም ለገበሬው በዱብ መልክ በመስጠትና በመከልከል ማዳበሪያን እንደ አንድ ቁልፍ የፖለቲካ መሳሪያ መጠቀም የሚቻልበት እድል አለ። በሌላ በኩል በኢትዮጵያ ያለው የማዳበሪያ አቅርቦት ከፍላጎቱ ጋ የማይጣጣም ከመሆኑም በላይ ፍላጎቱ ከአመት አመት የሚያቋርጥ አይደለም። ስለዚህም ማዳበሪያን ከአቅርቦቱ እስከ ስርጭቱ በሞኖፖሊ መቆጣጠር ከፈተኛ ትርፍ ያስገኛል። የማይነጥፍ የገንዘብ ምንጭ ሆኖ ያገለግላል።

ይህን የተገነዘቡት ህወሓቶች የማዳበሪያ አቅርቦትና ስርጭቱን "በአብዮታዊ ዴሞክራሲ ኃይሎች" ቁጥጥር ስር መዋል እንዲገባው ተገነዘቡ። የኤፈርት ኩባንያ አካል የሆነው ጉና ኢንተርፕራይዝ ብቻውን ለማቅረብና ማሰራጨት እንደማይችል ሲረዳ የብአዴን፣ ኦህዴድና ደኢህዴግ ድርጅት የሆኑት አምባሰል፣ ዲንሾና ወንዶ በሞኖፖሊው እንዲሳተፉ አደረጉ። ከማዳበሪያውም በተጨማሪ እንደ ማጭድና ዶማ የመሳሰሉትን የግብርና ቁሳቁሶች እንዲያመርቱና እንዲያሰራጩ ተደረገ። ጉና ወደ ኢትዮጵያ የማስመጣቱን የአንበሳ ድርሻ በመውሰድ ሞኖፖሊውን

My text!

አረጋገጠ። የዋጋ[illegible] መ[illegible]ካት መሪ[illegible] ከንጻ ገበ[illegible] አ[illegible]ር ባይሆን [illegible]ርቲያ፣ ኩ[illegible]ንያዎች የትርፍ ፍላጎት ላይ የተመሰረተ እንዲሆ[illegible] አደረጉ። ሁሉም ነገር በቁጥጥር ስር ነበ[illegible]።

ገብረየስ በድጋሚ ተሰደደ። ይኸው ነው!

***

ከምሳ ግብዣው በኋላ ወደ መጣሁበት የተመለስኩት በፍጹም ብስጭት ውስጥ ነበር። እቶ መለስ ኤፈርትን የመሳሰሉ የፓርቲ ኩባንያዎች ባለሀብቶችን ለመደገፍና ለማበረታታት የተቋቋሙ ናቸው ብሎ ሲፅፍ ለምን አእምሮውን ሲቆንጥጠው እንዳልቻለ ራሴን ጠየኩ። በተለይም "የኩባንያዎቹ ተግባራዊ እንቅስቃሴ የሚመሰክረውና የሚያረጋግጠው ነገር ይህንን ነው" ማለቱ የልቡን ደንዳናነት ቁልጭ አድርጎ አሳየኝ። ገበሬውን ለመቆጣጠርና ገደብ የለሽ ትርፍ ለማግበስበስ እነ ጉና ኢንተርፕራይዝ መንቀሳቀሳቸው ፀሐይ የሞቀው እውነት ሆኖ ሲያበቃ "የኤፈርት አቅም ውሱን ነው። ኢኮኖሚውን ሲቆጣጠሩ አይችሉም" ማለቱ የኢትዮጵያን ህዝብ እንዴት እንደሚንቅ አመላከተኝ።

በግብዣው ላይ የተገኘው ጋዜጠኛ ሲሳይ አጌና ብዙ የፊት ለውጥ አይታይበትም። ለነገሩ መደሰቱንም ሆነ መበሳጨቱን በውስጡ የማመቅ ልዩ ችሎታ እንዳለው በመታዘቤ የስሜት ለውጥ አለማየቴ አልደነቀኝም። ምን አልባትም ከጌጃው ዋርካ ጋር በተደጋጋሚ የመገናኘት እድል ስላጋጠመው ሊሆን እንደሚችል ጠርጥሬያለው።

እናም ከጥቂት ዝምታ በኋላ ገብረየስ ቤኛን ከጨዋታ አለወጥቶ ከሚወዳት አገሩ ኢትዮጵያ ስላባረረው የኤፈርት ኩባንያ አካል ስለሆነው ጉና ኢንተርፕራይዝ መነጋገር ጀመርን። የአገሪቷን ቁልፍ የኤክስፖርት ኢምፖርት ጨዋታችንም ጉና እንዴት እንደተመሰረተ፣ እንቅስቃሴዎች እንዴት እየተቆጣጠረ እንደሄደ የሚያመለከት ሆነ።

ከፊል ጨዋታችን እንደሚከተለው ነበር።

***

በዘሪያቆብ ተስፋዝጊ ስራ አስኪያጅነት ሲተዳደር የነበረው ጉና ትሬዲንግ ሃውስ በስድስት ነባር የህወሓት ታጋዮች ስም እንዲቋቋም የተደረገ ነው። እነዚህም ግርማይ ገብረመድህን፣ ግደይ ገብረሚካኤል፣ ህቡር ገብረኪዳን፣ ሰለሞን ገብረህይወት ሙሉ ሃጎስ እና ጸጋዬ ጣምያለው የሚባሉ

ናቸው። ግርማይ ገብረመድህን ምክትል ስራ አስኪያጅ ሲሆን ጉና ትሬዲንግ ሃውስ ከውጭ የሚያስገባቸውን ምርቶች በበላይነት የሚመራ ነው። ግርማይ ገብረመድህን (በበርሃ ስሙ "ግርማይ ዳቦ") ከጉና ትሬዲንግ ወደ ትራንስ ኢትዮጵያ ተዘዋውሮ እንዲሰራ ተደርጓል። በመጨረሻም የግሉን ድርጅት በመክፈት ወደ ኢንቨስተርነት ተሸጋግሯል።

ሁለተኛው የጉና ትሬዲንግ ሃውስ ባለድርሻ ግደይ ገ/ሚካዔል (በበረሃ ስሙ "ግደይ ፎሮ") የሚባል ሲሆን፣ በትጥቅ ትግሉ ወቅት የህወሓት ኢኮኖሚ ዲፓርትመንት ውስጥ ሃላፊ ነበር። በተለይም በኤርትራ ጦርነት "ፍሮ" በሚባል አካባቢ ቢሮ በመክፈት የማጨበርበር (TPLF. tax smuggle) በበላይነት ሲመራ የነበረ ግለሰብ ነው። ግደይ በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ወቅትም ከውጭ የተገዙ መሳሪያዎችን ከስዬ አብርሃ ጋር በመሄድ የገዛ ነው። ኤፈርት ለኢትዮጵያ መንግስት ከ 3 ቢሊዮን ብር በላይ አበደረ በሚል የጦር መሳሪያ እንዲገዛ የተደረገ በግደይ እና ስዬ አብርሃ አማካኝነት ነው። ሌላው የጉና ትሬዲንግ ሃውስ ሼር ባለቤት ሙሉ ሃጎስ ሲሆን ለረጅም ጊዜ የህወሓትና የኢህአዴግ ጽ/ቤት የፋይናንስ ሃላፊ ነበር። ህወሓት አዲስ አበባን ከተቆጣጠረ በኋላ የገንዘብ ሚኒስቴር ውስጥ የፋይናንስ ሃላፊና የሚኒስትር መስሪያቤቱ የፖለቲካ ጉዳዮች ሃላፊ ሆኖ ተመድቧል። ህወሓት የትግራይ ክልልን ነጻ ባወጣ ሰዓት ለህዝቡ መድሃኒት ያከፋፈለበትን 4 ሚሊዮን ብር ከአዲስ አበባ ጤና ቢሮ ተቀንሶ እንዲሰጥ ትእዛዝ ያስተላለፈው ታጋይ ሙሉ ሃጎስ ነበር።

My text!

ሦስተኛው የጉና ትሬዲንግ ሃውስ ባለድርሻ ህቡር ገ/ኪዳን ይባላል። ታጋይ ህቡር ከሽማግሌው ስብሃት ነጋ ቀጥሎ ለህወሓት ታጋዮች "የጡት አባት" ተደርጎ የሚቆጠር ሰው ነው። በበረሃ ዘመኑ የስለላ እና የሰውር ግድያ ኮማንደር በመሆኑ በርካታ ህይወት ማጥፋቱ በታጋዩ ዘንድ የሚመሰከርለት ነው። ከትጥቅ ትግሉ በኋላ የፓርላማ አባላ በመሆን ሽንጎውን በሰውር እንዲመራ ተደርጓል። ከዚህ በተጨማሪ የኢህአዴግ ብሎም የህወሓት ቁጥጥር ኮሚሽን በመሆን ተመድቦ ሲሰራ ነበር። እንጃዎቹን በመወገን የአቶ መለስን ህግ-ወጥነት በደብዳቤ ያሳወቀው እሱ ነበር። በሂደት እድል ወደ አቶ መለስ እያዘነበለች ስትሄድ ጥፋተኛ ነኝ በማለት ድርጅቱን ተማጽኖ ለመመለስ ችሏል። የቋጠረውን ቂም ካልተበቀለ ወደ ኋላ የማይመለሰው አቶ መለስ ሁላችንም በተሳተፍንበት ጉባኤ አወረደው። ጉባኤው እስኪጠናቀቅ ድረስ የቁጥጥር ኮሚሽን ሰብሳቢው የሆነውን ህቡር ገ/ኪዳን ጥንብ እርኩሱን አወጣው። በጉባኤተኛው ፊት የኮሚሽኑን ሪፖርት ታጋይ ህቡር ላይ ወረወረበት። "እጥንት የሌለው ስጋ ተሸክመህ የምትዞር" በማለት ተሳለቀበት።

በኢህአዴግ ታሪክ ለመጀምሪያ ጊዜ የቁጥጥር ኮሚሽን ሪፖርት ሙሉ ለሙሉ ውድቅ ተደረገ። ታጋይ ህቡርም ከጉና ትሬዲንግ ሀውስና ከአፍሪካ ኢንሹራንስ የቦርድ አባላነት እንዲባረር ተደረገ።

ጉና ትሬዲንግ ሀውስ በተመሰረተ የመጀመሪያዎቹ አካባቢ በሦስት ቁልፍ ስራዎች ላይ እንዲሰማራ ተደርጎ ነበር። እነዚህ ኢምፖርት/ኤክስፖርት፣ የጅምላ ንግድና የኮንስትራክሽን ስራዎች ነበር። ይህንን ተልዕኮ ለመፈጸም በሁለት ትላልቅ ክፍሎች (subsidiaries) የተደራጀ ሲሆን የመጀመሪያው በመንገድና ህንጻ ግንባታ እቃዎች ላይ የሚያተኩር እንዲሆን ተደረገ። ሁለተኛው በማዳበሪያ ግዥና ስርጭት ላይ ትኩረት ሰጥቶ የሚንቀሳቀስ ሆነ። የመንቀሳቀሻ ማዕከላቸውም ሁሉም የአክሲዮን ባለቤቶች ነዋሪ የሆኑባት አዲስ አበባ እንድትሆን አደረጉ።

በከፍተኛ የንግድ ስራ ላይ የተሰማራው ጉና ትሬዲንግ ሀውስ በነሐሴ 1987 ዓ.ም. ላይ በድጋሚ መልሶ በመዋቀር "ጉና ቡና ኢንተርፕራይዝ" እና "ጉና የንግድ ስራዎች ድርጅት ኢ.ማ." በሚሉ እንዲደራጅ ተደረገ። በህወሓት ታጋዮች አክሲዮንነት መያዙ ቀርቶ በኤፈርት ኩባንያዎች የአክሲዮን መዋጮ እንደተደራጀ ተደርጎ ተገለጠ። አልመዳ ጨርቃጨርቅ፣ ትራንስ ኢትዮጵያ፣ መሶበ የህንጻ መሳሪያዎች ማምረቻ እና ሸማግሌው ስብሃት ነጋ የአክሲዮኑ ባለቤቶች ሆኑ። የአክሲዮን መጠናቸውም በሰንጠረዥ 13 እንደሚታየው ሆነ፤

ጉና ትሬዲንግ ሃውስ

ተ.ቁ.	የአክሲዮን ባለቤቶች	የአክሲዮን መጠን	የአንድ አክሲዮን ዋጋ	ጠቅላላ የአክሲዮን ዋጋ
1.	ግርማይ ገ/መድህን	1,700.00	1,000.00	1,700,000.00
2.	ግደይ ገ/ሚካኤል	1,700.00	1,000.00	1,700,000.00
3.	ህቡር ገ/ኪዳን	1,700.00	1,000.00	1,700,000.00
4.	ሰለሞን ገ/ህይወት	1,700.00	1,000.00	1,700,000.00
5.	ሙሉ ሃጎስ	1,700.00	1,000.00	1,700,000.00
6.	ፀጋዬ ጣምያለው	1,700.00	1,000.00	1,700,000.00

ሰንጠረዥ ቁጥር 13፡ የጉና ትሬዲንግ ሀውሱ አክሲዮን ባለቤቶች

My text!

...ና ቡና ኢንተርፕራ...

ተ.ቁ	የአክሲዮን ባለቤቶች	የአክሲዮን መጠን	የአንድ አክሲዮን ዋጋ	ጠቅላላ የአክሲዮን ዋጋ
1.	ጉና ንግድ ስራዎች ድርጅት	21,780	500.00	10,890,000.00
2.	አልመዳ ጨርቃጨርቅ	70	500.00	35,000.00
3.	ትራንስ ኢትዮጵያ	70	500.00	35,000.00
4.	መሶቦ የህንጻ መሳሪያዎች ማምረቻ	70	500.00	35,000.00
5.	ሰብሃት ነጋ	10	500.00	5,000.00

ሰንጠረዥ ቁጥር 14: የጉና ቡና ኢንተርፕራይዝ አክሲዮን ባለቤቶች

ጉና የንግድ ስራዎች ድርጅት አ.ማ.

ተ.ቁ	የአክሲዮን ባለቤቶች	የአክሲዮን መጠን	የአንድ አክሲዮን ዋጋ	ጠቅላላ የአክሲዮን ዋጋ
1.	ትዕምት	9,699	1000.00	9,699,000.00
2.	አልመዳ ጨርቃጨርቅ	100	1000.00	100,000.00
3.	ትራንስ ኢትዮጵያ	100	1000.00	100,000.00
4.	መሶበ የህንጻ መሳሪያዎች ማምረቻ	100	1000.00	100,000.00
5.	ስብሃት ነጋ	1	1000.00	1,000.00

ሰንጠረዥ ቁጥር 15: የጉና የንግድ ስራዎች ድርጅት አ.ማ. አክሲዮን ባለቤቶች

እንደ እውነቱ ከሆነ ስለ ጉና ትሬዲንግ ያለኝ ግንዛቤ በፓርቲ ጽ/ቤት ተመድቤ ከሰራሁት የሚተናነስ አይደለም። የሚገርመኝ ነገር ሆኖ የኤፈርት ማርኬቲንግ ዳሬክተር፤ በኋላ ላይ የጉና

ትሬዲንግ ዋና ስራአስኪያጅ የሆነው ታጋይ አተይ ታጀለ የቅርብ ጓደኛዬ መሆኑ ድርጅቱን በቅርበት ለመፈተሽ አግዞኛል። ብዕርና ወረቀት ማዋደድ የሊማሊሞ መንገድ የሚሆንበት ታጋይ አተይ የሩብ፣ ግማሽና አመታዊ የጉና እቅዱን እንዲያዘጋጅ በሚጠየቅ ሰዓት ድጋፍ መጠየቁ የማይቀር ነበር። የእቅድ አፈጻጸሙን ለማጠናቀርም የጎንዮሽ እርዳታ ስለሚያስፈልገው እኛን ፈልጎ ማግኘቱ ከስራዎቹ አንዱ ነበር።በዚህም ምክንያት ለኤፈርት ማርኬቲንግ ዲፓርትመንት እና ጉና ቤተኛ ነበርኩ ብል ማጋነን አይሆንብኝም። አንዳንዴም ለአገልግሎቴ ሽርፍራፊ ሳንቲሞች አገኝበት ነበር።

ወደ ጉና በተመላለስኩ ሰዓት በርካታ ነገሮች መታዘብ ችያለሁ። የመጀመሪያው በኩባንያው ውስጥ "ከትግራዋይነት ይልቅ "አውራጃዊነት" ተንሰራፍቶ ይገኛል። በአንድ ወቅት የተመደበው የጉና ስራ አስኪያጅ ከአድዋ የመጣ ከሆነ ሁሉንም መምሪያዎች በአድዋ ልጆች እንዲያዙ ያደርጋል። ስራ አስፈጻሚው ከአክሱም ከመጣ ደግሞ እስከ ፀሀፊ ድረስ የአክሱም ታጋዮችን ይጠቀጥቃል። የማኑኝነት መስመሩም የህወሐትን አላማ ባልተከተለ መልኩ መንደርተኛ ይሆናል። የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ከመነሳቱ በፊት የጉና ስራ አስኪያጅ የነበረው ኤርትራዊው ዘርአያቆብ የኤርትራ ደም ያላቸውን ኒቆዲሞስ ዜናዊ (የመለስ ዜናዊ ወንድም) እና እልጋነሽ ገ/እግዚአብሔርን የጉና ፈላጭ ቆራጭ አድርጎአቸው ነበር። እልጋነሽ ወደ ኤርትራ እንድትባረር ስሟ ይፋ ሲሆን "እኔን የምታባርሩኝ ከሆነ ኒቆዲሞስ ዜናዊ መባረር አለበት። እሱም በምርጫ ተሳትፏል" የሚል ሙግት አንስታ ከመባረር ድናለች።

ከዘርአያቆብ ቀጥሎ የጉና ስራ አስኪያጅ የሆነው የአድዋ ተወላጅ ወርቁ ግደይ ነበር። በተመሳሳይ መንገድ ታጋይ ወርቁ ከአድዋ ውጭ ያሉ የመምሪያ ሀላፊዎችን አባሮ ቤቱን አድዋ በአድዋ አደረገው። በወርቁ ግደይ ከተባረሩት መካከል የስብሃት ነጋ የእከስት ልጅ እንደሆነ የሚነገረው ግርማይ ገ/ሚካኤል ይገኝበታል።

(የጉና የሰው ሃይል አስተዳደር የነበረው ግርማይ ገ/ሚካኤል ከስራ ሲባረር መላ ዘየደ። በኢትዮጵያ ምድር ታይቶ የማይታወቅ ፕሮጀክት ይፋ አደረገ። ፕሮጀክቱ ከኢትዮጵያውያን በነብስ ወከፍ እስከ 37ሺህ ብር በመቀበል የደቡብ አፍሪካ አለም ዋንጫ እንዲመለከቱ መላክ የሚል ነበር። እንደታቀደው ፕሮጀክቱ በመላካቱ ምክንያት ታጋይ ግርማይ የ42 ሚሊዮን ብር ባለቤት ሆነ። ደቡብ አፍሪካ እሔዳለሁ በማለት ቋምጦ የነበረው ኢትዮጵያዊ ወንዝን ሳይሻገር ቀረ።

My text!

ሆኖም ግን የተቆጨው ህዝብ ማዕበል ማስነሳቱ አልቀረም። ህወሓት ኪደሙ ነፃ እንደሆን ለማሳየት በዛውም የህዝብ ግኑኝነት ለመስራት ግርማይን በኢንተርፖል ሳይቀር አያስፈለገው እንደሆነ ገለጠ። ለመውሰድ የተቃረበች ሚስቱን በመያዣነት መቆጠሯን ለግርማይ እንዲደርሰው አደረጉ ...ግርማይ ከህወሓት ጋር ባደረገው ድርድር ወደ አገር ቤት ተመለሰ። እንደተጠበቀው ኢንተርፖል እየተጠቃሰ ሰፊ ፕሮፖጋንዳ ተሰራበት።...ግርማይ ተፈረደበት። እስሩን ሳይጨርስ በአመካር ተለቀቀ።)

የኋላ ኋላ አሸናፊነቱን ያረጋገጠው ስብሃት ነጋ መጀመሪያ ወርቁ ግደይን ቀጥሎ ገ/እግዜአብሔር ግደይን ከጉና ስራ አስኪያጅነት ተራ በተራ ያባርራል። የወንድሙን ልጅ የሚያገባውን ሙሉአለም ብርሃኔ የጉና ስራ አስኪያጅ ያደርጋል። ሙሉአለም የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የፋይናንስ መምህር በመሆኑ ጉና የሚያደርገውን የህገራዊ ሁብት ዘረፋ ወደ ላቀ ደረጃ እንዲሸጋገር ያደርጋል። ይህም ሆኖ የሙሉአለም ሚና በሂደት ጎልቶ መታየት እና ወጣ ወጣ ማለት ለወይዘሮ አዜብ ጤና የሰጠ አልነበረም። በሴትዮዋ ወንጭፍ እንዲመታ አደረገው። በምትኩም ማስተርሱን ከገኛ ክፍል የሰራው የቅርብ ወዳጇ አተይ ታደለ የጉና ስራ አስኪያጅ ሆኖ ተሾመ። ያለማጋነን የወይዘሮ አዜብ የእውቀት ደረጃ ከአተይ የሚሻል በመሆኑ ስልጣኑ ብዙም አይጋ እንደማይገጥመው አተይ ግንዛቤ ነበረው።

***

ወደ ጉና ስመላለስ ሁለተኛ የታዘብኩት ነገር የድርጅቱ ባለስልጣናት እንዲሆኑ የተደረጉት ታጋዮች በሙሉ በጎንዮሽ የራሳቸው ቢዝነስ እንዲኖራቸው ተደርጓል። ጉና በመላው አገሪቱ ከከፈታቸው 10ሺህ የችርቻር ሱቆች መካከል ከ500 የማያንሱት የታጋይ ባለስልጣናቱ የግል ንብረቶች እንዲሆኑ አድርጓል። ኤፈርት ያስቀረጥ ከሚያስገባቸው ላንድክሩዘር መኪኖች ውስጥ በነብስ ወከፍ አንድ ለጉና የመምሪያ እና ከዛ በላይ ለሚገኙ ሀላፊዎች በግል ንብረት የሚያዝ ነው። እነዚህ ታጋይ ባለስልጣናት ጉናን ለቀው ቢወጡ እንኳን ፖለቲካዊ ችግር እስካልፈጠሩ ድረስ በግላቸው የተሰጣቸውን ንብረት አይነጠቁም። እንዳንዶቹም በተጨባጭ ኢንቨስትመንት እና ማህበራትን የሚመሩበት ሁኔታ ይፈጠርላቸዋል። ለዚህ አባባል ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው ታጋይ ሃይሌ በርሔ ነው።

ታጋይ ሃይሌ በርሔ የጉና ኤክስፖርት መምሪያ ሃላፊ በመሆን ለረጅም አመታት አገልግሏል። ከጉና ሳይወጣ የቅባት እህሎች የሚልክ ትንሽ ድርጅት ከሌሎች የትግራይ ተወላጆች ጋር በማቋቋም በጎንዮሽ የራሱን ቢዝነስ ያጧጡፋል። በሂደትም ጉናን በመወከል የኢትዮጵያ ቅባት እህሎች ላኪ ማህበር (EPOSPEA) ፕሬዝዳንት እንዲሆን ይደረጋል። ከኢትዮጵያ ወደ ውጪ የሚወጡ የቅባት እህል ኤክስፖርተሮች በሚመራው ስር ይወድቃሉ። በአጭር ጊዜ ውስጥ ታጋይ ሃይሌ የሚሊዮን ብሮች የሀብት ጋር ላይ ይወጣል።

***

ወደ አተይ ታደለ ስመላለስ በሦስተኛ ደረጃ የታዘብኩት ነገር ከኤፈርት ኩባንያዎች ውስጥ ከተቋቋመ አለት አንስቶ ከፍተኛ ትርፍ እና የውጭ ምንዛሪ የሚያስገኘው ጉና የንግድ ስራዎች ድርጅት ነው። ከኢትዮጵያ ቡና፣ የቅባት እህሎች የሆኑትን ሰሊጥ፣ ሱፍና ኑግ የመሳሰሉትን የግብርና ምርቶች ወደ ውጭ ይልካል። ወደ ውጭ ከሚላኩ ምርቶች ቀዳሚውን የሚይዘው ቡና በመሆኑ ለብቻው "ጉና ቡና ኢንተርፕራይዝ" የሚል ኩባንያ እንዲቋቋምለት ተደርጓል። የዚህ ኢንተርፕራይዝ የአክሲዮን ባለቤቶችም ራሱ ጉና ንግድ ስራዎች ድርጅት፣ አልመዳ ጨርቃጨርቅ፣ ትራንስ ኢትዮጵያ፣ መሰቦ የህንፃ መሳሪያዎች ማምረቻ እና ሸማግሌው ስብሃት ነጋ ናቸው። በሌላ አነጋገር ቀደም ባለው ክፍል በአልመዳ እንዳየነው ሁሉ ትራንስ እና መሰቦ የቡና ገበያ ጉዳይ ከሚያሳስባቸው የኤፈርት ኩባንያዎች አንዱ ሆነዋል። በትግራይ ክልል ይህ ነው የሚባል የቡና ተከል በሌለበት ሁኔታ በኢትዮጵያ ትልቅ የቡና ኤክስፖርተሮች እነሱ ናቸው። ለዚህ ማስረጃ የሚሆነው የብሉንበርግ የዜና ወኪል የጉና ንግድ ስራዎች ባለስልጣናትን ጠቅሶ በ2001 ዓ.ም. ያወጣው ሪፖርት ነው። ብሉንበርግ እንደሚከተለው ይላል፤

"Guna plans to be the biggest coffee exporter in Ethiopia. The company began shipping the beans in July and aims to export at least 12,000 metric tons of coffee."

ከኢትዮጵያ የውጭ ንግድ ከ30 በመቶ በላይ የሚሸፍነውን ቡና ኤክስፖርት ማድረግ እንደሚያወጣ የተገነዘበው ኤፈርት የቡና ንግዱን በሀገ-ወጥ መልኩ ከሚያከናውኑ ድርጅቶች ግንባር ቀደም ነው። በአንድ በኩል የቡና አምራቾችና የጅምላ ሻጮች ከፊል ምርታቸውን የኢትዮጵያ ኮሞዲቲ ኤክስቼንጅ (ECX) ሳያስገቡ በቀጥታ ለጉና የሚሸጡበት አስገዳጅ ሁኔታ እንዲፈጠር ተደርጓል። በሌላ በኩል (ECX) ውስጥ የገባውን ቡና ከፍተኛ የጨረታ ዋጋ በማቅረብ

My text!

ሌላው ተጫ[illegible]ች [illegible]ሬ ተ[illegible]ፋ ቆ[illegible] ከንግዱ [illegible]ዲ[illegible] የ[illegible]ርጉ[illegible]ል። [illegible]ህ[illegible] [illegible]መ[illegible]ገድ ያፀ[illegible] በውድ ዋጋ ጉና ገዝቶ እንደሚሸ[illegible] ለማሳየት ሰፊ የህዝብ ግኑኝነት ስራ ይሰራል። በዚህ መልኩ ህጋዊና ህገ-ወጥ አሰራሮችን በመቀላቀል የቡና ኮንትሮባንዱን ያጧጡፈዋል። ይህን በተመለከተ አቶ መለስ ጉና ብሎ ባይጠራም ከ10ሺህ ቶን በላይ ቡና የሚጠፋበትን ሁኔታ እንደተፈጠረ የተናገረው ዛሬም ድረስ በኢትዮጵያውያን ዘንድ እንደ ተአምር የሚነገር ነው። አቶ መለስ ኤክስፖርተሮችንና ባለሀብቶችን በጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ትንሿ አዳራሽ ሰብስቦ የሰጠው መግለጫ ከፊል ቃላት እንዲህ ይላል፤

"10ሺህ ቶን ቡና ኤክስፖርት ተብሎ በመጋዘን ተይዞ የነበረው የት እንደገባ አይታወቅም። ይህን በተመለከተ የሚመለከተው አካል አርምጃ መውሰድ ይኖርበታል። እንደተባለው ተነፃ የተባለው ቡና ተናም ከሆነ መረጃው መቅረብ አለበት።...እንደዚህ አይነት የቡና ኮንትሮባንድ ውስጥ የሚገባ እጅ ካለ ሌላ ጊዜ እንዳይገባ አድርገን እንቆርጠዋለን" በማለት ነበር የተናገረው።

(ይህ የአቶ መለስ መረጃ ለህዝብ ከተገለጠ በኋላ በኢህአዴግ ቢሮ ሐይለማሪያም ደሳለኝ፣ ብርሃኑ አደሎና አባይ ፀሀዬ የሚመራ ቡድን በሚስጥር እንዲመረምር የውስጡ ድርጅት ትዕዛዝ ተሰጥቶ ነበር። ቡድኑ የማጣራቱን ስራ የተወሰነ ርቀት ከሄደ በኋላ እንዲቋረጥ ተደረገ። ከእለታት አንድ ቀን በዝዋይ ህፃናት አምባ (አላጌ) ካድሬዎች ለማሰልጠን የተገኘው ሬድዋን ሁሴን፣ ካሚል አህመድና ፀጋዬ በሞቀ ሐሜት ውስጥ ሐይለማሪያምን ለምን እንደተቋረጠ ጠየቅነው። ህወሓቶችን ከጀርባ ሆኖ በማማት ተወዳዳሪ የሌለው ሐይለማሪያም ደሳለኝ በፈገግታ ውስጥ ሆኖ፣

"ብዙ ርቀት ሳንሔድ አብዛኛውን ቡና በኮንትሮባንድ ያሻገረው ሽማግሌው ስብሃት ነጋ የሚመራው ጉና የንግድ ስራዎች መሆኑን ደረስንበት" በማለት ምላሽ ሰጠ። ከሐይለማሪያም ምላሽ በኋላ የኢህአዴግ ቁልፍ ካድሬዎች ጉና ቡናና ሰሊጥ ምርቶችን ወደ (ECX) ሳያስገባ በቀጥታ ኤክስፖርት እንደሚያደርግ ተራ በተራ ያዩትን ተናገሩ።እኔም በበኩሌ የጉና ዋና ጽ/ቤት የሚገኝበት ቦሌ ገርጂ ሰሔድ የተመለከትኩትን መረጃ አቀረብኩ። እነ ሐይለማሪያም የተጋረጡበት የማጣራት ስራ ተንገራግጮ እንደሚቆም አስቀድሜ አውቅ እንደነበር ጨምሬ ተናገርኩ።)

ወደ ቦሌ ገርጂ የጉና ቢሮ ስመላለስ በአራተኛ ደረጃ የተረዳሁት ነገር ቢኖር ከሁሉም የኤፈርት ኩባንያዎች ውስጥ ተቀናጅቶ እና ሲነርጂ ፈጥሮ ከመስራት ረገድ ተወዳዳሪ የሌለው ኩባንያ ጉና ትሬዲንግ ነው። ጉና ትሬዲንግ የግብርና ምርቶችን በተለይም ቡና እና የቅባት እህሎችን ኤክስፖርት ለማድረግ የህይወት ሜካናይዜሽን አክሲዮን ባለቤት ነው። በአንድ ወቅት

አቶ መለስ ባወጣው ህግ መሰረት የራሳቸው የእርሻ ምርት ቻላቸው ተቋማት ኤክስፖርት ማድረግ ከፈለጉ ራሳቸው ማድረግ ይችላሉ የሚል ነበር። በዚህ ህግ መሰረት ህይወት ሜካናይዜሽን (ECX) ማስገባት ሳይጠበቅበት በእህት ድርጅቱ ጉና ትሬዲንግ አማካኝነት በቀጥታ ኤክስፖርት ማድረግ ችሎ ነበር። በሌላ ጊዜ ደግሞ አምራቹ ዋጋውን ወስኖ የሚመርጠው ኤክስፖርተር ይውሰዱልኝ ማለት እንደሚችል ሌላ ህግ እንዲወጣ ተደረገ። ይህ የተደረገበት ምክንያት ህይወት ሜካናይዜሽን አሁንም ምርቱን ጉና ኢንተርፕራይዝ ወስዶ እንዲሸጥለት ስለተፈለገ ነበር።

በተመሳሳይ መንገድ ጉና የኤፈርት ኩባንያ አካል የሆነውና በትራንስፖርት ዘርፍ የሚሰተፈው ትራንስ ኢትዮጵያ ሼር ባለቤት ነው። ጉና ከትራንስ ባለቤቶች አንዱ በመሆኑ በትራንስፖርቱ ዘርፍ የሚኖረው ሲነርጂ በተሟላ መንገድ እንዲተገበር ያደርገዋል። ለዚህ አገላለጥ አንድ ምሳሌ ብንወስድ ጉና ማዳበሪያ ከውጭ ለማስመጣት ማዳበሪያውን ወደብ ላይ ያራግፋል። ከወደብ ላይ የትራንስ ኢትዮጵያ የጭነት መኪኖች ወደ ገበሬው አቅራቢያ (ለምሳሌ ሰቲት ሁመራ) ይወስዳሉ። የኤፈርት የጡብታ ኢኮኖሚ ተጠቃሚ የሆነው ደደቢት የብድርና ገንዘብ ቁጠባ ድርጅት ለገበሬው የብድር አገልግሎት ይሰጣል። የሁመራ ገበሬ ምርቱን ሲያመርት የተቆለለበትን እዳ ለመክፈል ለጉና (ህይወት) ይሸጣል። ትራንስ ኢትዮጵያ የገበሬውን (ህይወት) የግብርና ምርት በማጓጓዝ ሂደቱን የተሟላ ያደርጋል። ይህንን ሉደት እንቅፋት ለመፍጠር የሚሞክሩ ተፎካካሪዎች "በኢኮኖሚክ መሳሪያዎች" አማካኝነት ልክ እንዲገቡ ይደረጋል።

(በሰሊጥ ምርት ተፎካካሪ እየሆነ የሔደው ሐገራዊ ከበርቴ ኩሩማ ከበደ (ኬኬ) "በኢኮኖሚክ ኢንስትሩመንት" ተመቶ ዘብጥያ መውረዱ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው። ይህ በአንድ ወቅት በአቶ መለስ "ኮከብ ታክስ ከፋይ" በሚል የተሸለመ ሰው ኢምግሩን በማስፋት በድርና ማግ፣ በጨርቃጨርቅ፣ በቡናና ሰሊጥ ኤክስፖርት፣ በመኪና አስመጪነት የተሰማራ ባለሃብት ነበረ። በኢህአዴግና ህዝቡ ውስጥ ጥያቄ ያነሱ (በተለይም እንደ አርአያ የሚመለከቱት የመራህቤቱ ሰዎች) የተሳሳተ መረጃ እንዲሰጣቸው ተደረገ። ለውየው የደርግ ስርአትን ለመመለስ በግልፅና ሀብሉ እያደራጀ ስርዓቱን ለመበርበር እንደሚሰራ ተነገረ። ከትራንስ ጋር ተያይዞ የህወሓት ኢኮኖሚክ ኢንስትሩመንት ከተነሳ አይቀር የስታር ቢዝነስ ግሩፕ አባላት የሆኑት እነ ምንውየለት እና አበባው መሐሪ ባላንስ የሙሉወንጌል ኢድባር ትጠይቀኛለች!!)

በተጨማሪ ጉና የኤፈርት ኩባንያ የሆነው "ተስፋ የእንስሣት ሀብት ልማት ድርጅት" ባለቤት ነው። ተስፋ የእንሣት ሀብት ልማት ድርጅት የተቋቋመው ህወሓት "የአቀራረብ ማሻሻያ አድርጌያለሁ በማለት "ከመንግስታዊ ካፒታሊዝም" ወደ "ፓርቲ መር ካፒታሊዝም" ሽግግር በተደረገበት 1985 ዓ.ም. ላይ ነው። በመጀመሪያው የምስረታ ጊዜ የአክሲዮን አባል እንዲሆኑ የተደረጉት አምስት የህወሓት ነባር ታጋዮች ነበሩ። ታጋዮቹ ሮማን ገ/ስልሴ፣ ሺሻይ አሰፋ፣ ኪዱ ተከለሃይማኖት፣ ምህረት ወ/ሚካኤል እና መኮንን ተስፋሁን ሲሆኑ እያንዳንዳቸው አዋጡ የተባለው ገንዘብ 4 ሚሊዮን ብር ያህል ነበር። በ1989 ዓ.ም. "ፓርቲ መር ካፒታሊዝም" ሲሆን ታጋዮቹ በስማቸው የተቀመጠው ገንዘብና የአክሲዮን ድርሻ ለጉና፣ ህይወት፣ ሸባ የቆዳ ፋብሪካ እና ትዕምት በስጦታ መልኩ እንዲሰጡ ተደረገ። ተስፋ የእንሣት ሀብት ልማት በተጠናከረ ሁኔታ የከብት ማደለብና መሸጥ፣ የሲጋና የወተት ውጤቶች በማምረት ለሀገር ውስጥና ለውጭ አቀረበ። የድርጅቱ አክሲዮን ባለቤት የሆነው ጉና የጅምላና ችርቻሮ ንግዱን ተረከቦ መስራት ቻለ።

የጉና አክሲዮን ባለቤትነት በዚህ ብቻ አያበቃም። የኤፈርት ኩባንያ አካል የሆነው አዲግራት መድሐኒት ፋብሪካ ባለቤቶች ከሆኑት ትዕምት፣ ትራንስ ኢትዮጵያና አዲስ ኢንተርናሽናል ውስጥ ጉና የንግድ ስራዎች ድርጅት ይገኝበታል። አዲግራት መድሐኒት ፋብሪካ (አዲስ መድሐኒት) ሲቋቋም 69 በመቶ የሚሆነው ገንዘብ (116 ሚሊዮን) ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በመበደር ነበር። ዘግየት ብሎ በአቶ መለስ ቀጭን ትዕዛዝ የተበላሸ አካውንት ውስጥ እንዲገባ ተደረገ። በስተመጨረሻም ልማት ባንክ ሊሰበስብ የማይችል በማለት ከብድር አካውንቱ እንዲሰረዝ አደረገው። ከዚህም በተጨማሪ አዲግራት መድሐኒት ፋብሪካ ሲመሰረት 25.5 ሚሊዮን ብር መዋጮ ያዋጡት ኢትዮጵያዊ ሙሉጌታ ጓዴ የሚባሉ ነበሩ። አቶ ሙሉጌታ ጓዴ በኤፈርት ታሪክ ውስጥ የትግራይ ተወላጅ ያልሁኑ ብቸኛ የአክሲዮን ባለቤት የሆኑ ሰው ነበሩ። ቅንጅቱ ሲያልቅ አያምር ቢሆንም!!

አዲግራት መድሐኒት ፋብሪካ ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኙት መድሐኒት ፋብሪካዎች በግዝፈት ምርቱ የመጀመሪያውን ቁጥር የሚይዝ ነው። በምስራቅ አፍሪካ ደረጃም በቁጥር አንድ ከሚጠቀሱት የመድሐኒት ፋብሪካዎች አንዱ ሆኗል። ጉሉኮስን ጨምሮ በርካታ መድሐኒቶችና የህክምና መሳሪያዎችን የሚያመርተው አዲግራት መድሐኒት ፋብሪካ በየጊዜው በሚገኘው ትርፍ ምክንያት የምርት አይነቱንና መጠኑን በጥቂት አመት ውስጥ ብቻ በአስር እጥፍ አሳድጓል፡

መድሐኒት ምርት ከተሰማሩ የቻይና ፋብሪካዎች ጋር ሽርክና በመፍጠር ምርቱን ኤክስፖርት ለማድረግ የሚያስችለው አቋም ላይ እንዲደርስ አድርጓል።

አዲግራት መድሐኒት ፋብሪካ ምርቱን ከመሸጥ አንፃር በልዩ ሁኔታ ከተመቻቸለት አንዱ መንገድ ለመንግስታዊ ተቋማት በቀጥታ እንዲያቀርብ መደረጉ ነው። በተለይም የመድሐኒት አቅርቦት ኤጀንሲ በመባል የተቋቋመው መንግስታዊ ተቋም የአዲግራት መድሐኒት ፋብሪካ አብዛኛውን ምርቶች በቀጥታ በመቀበል ለፋብሪካው እድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክቷል። የኤጀንሲው ዳሬክተር የነበረውና የቅርብ ጓደኛዬ የሁሉ ደነቀ እጅግ በጣም ከሚበሳጭባቸው የህወሓት ውሳኔዎች አንዱ ይሔ ነበር። ኤጀንሲው ከአዲግራት መድሃኒት ፋብሪካ ለመግዛት ከፍተኛ ኮታ ስለሚጣልበት አንዳንድ ጊዜ መድሃኒቶችና የህክምና ቁሳቁሶች ያለመጠን ተከማችተው ጊዜው ያልፍባቸዋል። እናም በዚህ ትርፍ የሚያጋብሰው የአዲግራት መድሐኒት ፋብሪካ ቋሚ ካፒታሉ ብቻ 900 ሚሊዮን ብር ደርሷል።

(የኤፈርት ኩባንያ አባል የሆነው አዲግራት መድሐኒት ፋብሪካ አንድ አማሩ መሬት ከቆነጠጠ በኋላ "የኢኮኖሚክስ ኢኒስትሩመንት" ካሰረፈባቸው የፋብሪካው መስራች የነበሩት አቶ ሙሉጌታ ጋር የገባበት ሰጣገባ ከኢትዮጵያ አልፎ በእንግሊዝ ፍርድ ቤት በመድረሱ ምክንያት ፓርቲው በሚስጥር የያዛቸው ነገሮች ይፋ ወጥተዋል። በኢትዮጵያ ህግ መሰረት የፖለቲካ ፓርቲዎች በንግድ መሰማራት ባይችሉም ህወሓት ግን በንግድ ስራ ያውም በውጭ ሀገር መሰተፉ ይፋ ሆኗል። ዘማየት ብሉ ሽማግሌው ስብሃት ነጋ ከቪኦኤ ጋዜጣኛ አዲሱ አበበ ጋር በነበረው ቆይታ በለንደን ህወሓት የንግድ ድርጅት እንዳለው አምኗል። ምርጫ ቦርዱም መረጃውን ሰምቶ እንዳልሰማ ሆኗል።)

***

ጉና የንግድ ስራዎች ድርጅት የሀገሪቷን የንግድ እንቅስቃሴ በችርቻሮ ሱቅ ደረጃ ለመቆጣጠር ያወጣው እቅዱም ወደ ተግባር እየተመነዘረ ነው። እነዚህ የችርቻሮ ሱቆች ዘርፈ ብዙ አላማ ያላቸው ናቸው። በአንድ በኩል ከአስር ሺህ በላይ ሱቆችን በመክፈት የኤፈርት ምርቶችን (ቬባ፣ አልመዳ፣ መሶበ፣ ኢዛና ወርቅ...) በመንደርና ቀበሌ ደረጃ መሸጥ የሚችሉበት ሁኔታ ይፈጥርላቸዋል። ይህም በሂደት የኤፈርት ምርቶች እየተለመዱ በመሔድ ህብረተሰቡ ዘወትር የሚሸምታቸው ይሆናሉ። በሌላ በኩል የችርቻሮ ሱቆቹ ህብረተሰቡ በህወሓት አገዛዝ ላይ

My text:

የሚያነሳውን ቅሬታ እና ዝንባሌ ለመመልከት ያግዛሉ። ሱቆቹ በግልጽ አካባቢዎች የሚከፈ
በመሆኑ የመረጃ እና ስለላ ስራ ለማከናወን አመቺዎች ናቸው።

ይህ በዋና ዋና ከተሞች የሚከፈት ሲሆን በተቋም ደረጃ ልዩ ትኩረት የተሰጣቸውም አሉ
ከእነዚህ ተቋማት ውስጥ የትላልቅ ሆቴል መለስተኛ ሱቆች፣ በተለያዩ ተቋማት ውስጥ ያሉ የስጦታ
ሱቆችና የንግድ መደብሮች በቅድሚያ የሚጠቀሱ ናቸው። በተለይም በኢትዮጵያ አየር መንገ
ውስጥ ያሉ ሱቆችና መዝናኛዎች ልዩ ትኩረት ተሰጥቷቸዋል።

ከአየር መንገዱና ኤርፖርቶች ድርጅት አንፃር ያለውን ሁኔታ ስመለከት በአንድ ወቅ
እኔና የኢህአዴግ ቢሮ ስራ ባልደረባዬ የነበረው ፀጋዬ ሐይለማርያም ያጠናነው ጥናት አደረሰኝ።
በጥናታችን መጨረሻ ላይ "የኢትዮጵያ አየር መንገድ የማነው?" የሚል ጥያቄም አንድናነ
አድርጎናል። በአየር መንገዱና ኤርፖቶች ድርጅት የሚካሔደው የቅጥር ሁኔታ፣ በተለያ
ተርሚናሎች ውስጥ የሚገኙት የንግድ ድርጅቶች ማን እንደተቆጣጠራቸው፣ የንግድ ተቋማ
ከመሸጥ ባሻገር ያላቸው ተልዕኮ፣ በአየር መንገድ ሰራተኞች የሚነገረው ቋንቋ፣ የተቋመ
አመራሮችና የቦርድ አባላት ማንነት ማወቃችን ነበር "አየር መንገድ የማነው?" ለማለት ያስገደደን።

***

"አየር መንገድ የማን ነው?"

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ተነጻጻሪ ነጻነቱን ጠብቆ የኖረ፣ የሁሉም ኢትዮጵያዊ መኩሪያ
መመኪያ ድርጅት ነበር። የአየር መንገዱን የአለም አቀፍ ተወዳዳሪነት እና የእለት ተእለት
እንቅስቃሴ በአንክሮ የማይከታተል ኢትዮጵያዊ በጣም አናሳ ነው። አየር መንገዱ ላይ የሚደረ
ጥቃትም ሆነ ውድቀት በግለሰብ ደረጃ የደረሰ እስኪመስል ድረስ ሁሉንም ያንገበግባል
ያስቆጫል።

ይህ ሀገራዊ ስሜት የፈጠረ ተቋም ኢህአዴግ አዲስ አባን በተቆጣጠረ ማግስት ጀምሮ
እንቅልፍ የነሳው ይመስላል። በተለይም የህወሓት ባለስልጣናት አየር መንገዱን ለማዳከም
ያልቆፈሩት ጉድጓድ አልነበረም። በመጀመሪያዎቹ የስልጣን ዘመናት ተቋሙ ከአብዮታዊ
ዴሞክራሲ አመለካከት የራቀ እና የኢምፔሪያሊዝም ተጽእኖ ያረፈበት ስለሆን መንኮታኮት አለበት
የሚል "የሚካ አቋም" በመውሰድ ድርጅቱን ለማፈራረስ የተቀናጀ እንቅስቃሴ አድርገዋል። ይህ

My text!

የጓላ ሆግ የውጭውወ[illegible] ተጸ[illegible]ና ብ[illegible] ሳይሆን ራሰ[illegible]የር [illegible] ብ[illegible]ሆት[illegible] የ[illegible] ተ[illegible]ድ፣ የአማራ ብሔር ቋንቋና ባህል ብቻ[illegible]ደ ኢትዮጵያ ባህል አድርጐ የሚወሰድ ተደርጐ የተወሰደበት ነበር። በኢህአዴግ የውስጠ ድርጅት ስብሰባዎችም ሲንፀባረቁ የነበሩት አመለካከቶች ይህን በግልጽ የሚያመላክቱ ነበሩ።

ህወሓት ለሁለት የተሰነጠቀ ሰሞን "ተሀድሶ" የሚል ስያሜ በተሰጣቸው ረጃጅም ስብሰባዎች የህወሓት ባለስልጣናት እንዲሁም የሌሎቹ ድርጅት አመራሮች አየር መንገዱ ላይ ያላቸው ጥላቻ በግልጽ ይታይ ነበር። በካርታ ስራ ድርጅት መሰብሰቢያ አዳራሽ በአቶ መለስ የተመራው የኢህዴድ ስብሰባ የፈረደበት አየር መንገድ ሲቀጠቀጥ ነበር። አንዳንድ የኢህዴድ ከፍተኛ ባለስልጣናት ጥያቄ የመጠየቅ እድል ሲያገኙ " የአየር መንገዱ አመራርና ሰራተኛ የትግራይ የበላይነት ለምን ሰፈነ?፣ የኦሮሞ፣ የጋምቤላ፣ ሱማሌ፣ አፋርና ሌሎች ብሄረሰቦች ለምን በአመራርነት፣ በአብራሪነት፣ በሆስቴስነት አናያቸውም?" የሚሉ ይገኙበት ነበር።

እዚህ ጋር የነበረውን እውነት መስከሮ መሄድ ተገቢ ስለሆነ በወቅቱ የአቶ መለስ አቋም የተለየ እንደነበር መናገር ያስፈልጋል ። ሰውየው በተደጋጋሚ የተናገራቸው ቃላት "አየር መንገዱ ከእነ ንፍጡም ቢሆን እጅግ በጣም ያስፈልገናል፤ አየር መንገዱ በትግራይ በአንድ ቤተሰብ እንዲታጠር ያደረጉት አንጃ ውስጥ ያሉ ሰዎች ናቸው" የሚል ነበር። ርግጥም ስየ የአየር መንገድ የቦርድ ሰብሳቢ በነበረ ሰዓት ብዙ ግፎች ፈጽሟል። ሊገዙ ትእዛዝ የተላለፈባቸው አውሮፕላኖች እንዳይገዙ አዟል። ለምን ተብሎ ሲጠየቅ "እኛ የገበሬ ድርጅት ነን" የሚል ኋላቀር ምላሽ ሰጥቷል። ለአውሮፕላን ግዥ የሚወጣው ወጪ ለግብርና ስራ ይውላል በማለት ከዘመኑ ጋር የማይሄድ ንግግር አድርጓል።

ከዛም በኋላ የቦርድ ሰብሳቢነቱን የተረከበው በአመራር ብቃት በጣም ደካማ ተደርጎ የሚወሰደው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበረው ስዩም መስፍን ነው። ስዩም መስፍን ይህንን ድክመቱን ለመሸፈን ከሚጠቀምባቸው ዘዴዎች ዋነኛው የቤተዘምድና የጥቅም ትሥሥር (ኔትወርክ) መፍጠር ነው። የውጭ ጉዳይ መስሪያቤት በኢህአዴግ ካድሬዎች ዘንድ "ገዛና ስዩም!" የሚባል ስያሜ እስኪሰጠው ድረስ ኔትወርኩን ዘርግቷል። በከተማ ቀመስ ካድሬዎች ዘንድ የስዩም መስፍን ስም የተረሳ እስኪመስል ድረስ "ኔትወርካሙ!" በመባል ይጠራ ነበር። ገብሩ አስራት በመጽሐፉ ላይ "ሰሚ ያጣው የአምስተኛው የህወሓት ጉባኤ" በሚለው ርዕስ ስር ስዩም መስፍንን በተመለከተ

My text!

ውሳኔዎችን የሚወስነው ከሰዎች ጋር ያለውን ቅርበትና ግኑኝነት መሰረት በማድረግ እንጂ በመርህ፣ ደንብና መመሪያ ተከትሎ እንዳልሆን በመረጃ አስደግፎ አሳይቷል። የህወሓት ማዕከላዊ ኮሚቴ ባደረገው ግምገማ ላይ የስዩም የአድልዎና የአሰራር ችግር በሰፊው ተነስቶ ከፖሊት ቢሮ እንዲባረር ሐሳብ ቀርቦ እንደነበር ያስረዳል። ከብዙ ክርክር በኋላ እንዲባረር የውሳኔ ሀሳብ ያቀረቡ ሰዎች ሀሳባቸውን እንዴት እንደሳቡ ሲገልጽ፣

"ሀሳባችንን የለወጥነው ሥዩም ለወደፊቱ ይሻሻላል ከሚል ሳይሆን ከአሁን ቤት አውሬ ሆኖ በድርጅቱ ይኸን አይነት ጥብቅ ውሳኔ ተሰጥቶበት ስለማያውቅ ነበር። የሆኖ ሆኖ ስዩም የቆሰለ አውሬ ሆኖ በድርጅቱ ማዕከላዊ ኮሚቴና ፖሊት ቢሮ ሊቆይ ቻለ" በማለት ይገልፃል።

"የቆሰለው አውሬ" የኢትዮጵያ አየር መንገድ የቦርድ ሰብሳቢ ሲሆን የአየር መንገዱን አመራር በዘመድ አዝማዶቹና ከእሱ ጋር የጥቅም ትሥሥር ባላቸው የትግራይ ተወላጆች ጠቀጠቀው። ከመምሪያ ጀምሮ የሚገኙት ወሳኝ የስልጣን ቦታዎች በአንድ አካባቢ ሰዎች ተሞሉ። ሲፓይለት፣ ቴክኒሻን እና ሆስቴስነት የሚመጡ ሰልጣኞች ከግማሽ በላይ የሚሆኑት የህወሓት ሊግ አባላት ሆኑ። በሌሎች የአየር መንገዱ የስራ ዘርፎችም የቅጥር ሁኔታው ተመሳሳይ ሆነ።

በነገራችን ላይ የኢትዮጵያ አየር መንገድና ኤርፓርቶች ድርጅት ከምርጫ 97 በኋላ የቀጠራቸው በሺህ የሚቆጠሩ ወጣቶች ሙሉ ለሙሉ የቅጥር ስርአቱ የተፈፀመው አራት ኪሎ በሚገኘው ኢህአዴግ ቢሮና ደህንነት ቢሮ ነበር። ከዚህ በተጨማሪም አልፎ አልፎ ጣል ጣል ከሚደረገው በስተቀር በአየር መንገዱ ሰልጥነው የሚቀጠሩ ግራውንድ ቴክኒሻኖችና ፓይለቶች በኢህአዴግና ደህንነት ጽ/ ቤት የጋራ እውቅና ማግኘት አለባቸው። ምልመላውን ያካሄዱት የኢህአዴግ ወጣቶች ፎረምና ሊግ በጥምረት ነበር። ወጣቶች ወደ አየር መንገድና የኢትዮጵያ ኤርፓርት ኢንተርፕራይዝ ለመቀጠር የኢህአዴግ አባልነት ግዴታ ይጣልባቸው ነበር። እነዚህ ወጣቶች ከእቃ ፍተሻ ጀምሮ የህወሓት ባለስልጣናትና ጉና በሚስጥር የሚያስተዳድራቸውን በአየር መንገዱ ውስጥ የሚገኙ የንግድ ተቋማት ተቀጥረው ይሰራሉ። ይሄ ስራ እኔ በቀጥታ ስከታተለው ከነበረው የወጣቶች ፎረምና ሊግ ጋር የተያያዘ በመሆኑ የእለት እንቅስቃሴውን በቅርበት ለማወቅ አስችሎኛል። በሊግ አደረጃጀት ታቅፈው በአየር መንገዱና ኤርፓርቶች ድርጅት የተቀጠሩት የኦሮሞና አማራ ወጣቶች ሳይቀሩ በተቋሙ የሰፈነውን ዘረኝነት፣ ዝርፊያና የወሲብ ቅሌት በመለስተኛ ግምገማ ያቀርቡ ነበር።

My text:

በአየር መንገዱ የሚነሳው ቅሬታ እየተባባሰ ሲሄድ በ1999 ዓ.ም... በኢህአዴግ ቢሮ የሙስና ጉዳዮችን የሚከታተለው ፀጋዬ ሐይለማርያም፣ የወጣቶች ሊግ ፕሬዝዳንት የነበረው ውብሸት ገ/እግዚአብሄርና እኔ የዳሰሳ ጥናት በሚስጥር እንድንሰራ ተደርጎ ነበር። በጥናቱ ሂደት ማስፈራሪያዎች ሲደርሰን የነበረው ከሩቅ ሳይሆን በፓርቲው ጽ/ ቤት አብረውን ከሚሰሩ ጓደኞቻችን ጭምር ነበር። በተለይ ይላቅ አበራ (ቆሪጥ) የሚባለው የህወሓት ታጋይ ከወጣቶች ሊግ ፕሬዝዳንቱ ጋር በነበረው ሚስጥረኝነት የተነሳ የስአታት ሪፓርት ይደርሰው ነበር። የደረሰውንም መረጃ ለቀድሞ መስሪያቤቱ ለሆነው ደህንነት ቢሮ ሳይውል ሳያድር ያስተላልፍ ነበር። የጉና ስራ አስኪያጅ የሆነው የቅርብ ጓደኛዬ አተይ ታደለ አይናችንን ከአየር መንገዱ ላይ እንድናነሳ ጓዳዊ ማስጠንቀቂያ አድርሶኛል።

የሆነ ሆኖ በብዙ ጫናዎች ውስጥ አልፈን ያገኘነው ውጤት በራሱ አስደንጋጭ ነበር። ከብዙ በጥቂቱ የሚከተሉት ናቸው፣

ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በአየር መንገድና ኤርፓርቶች ድርጅት ቅጥር የሚከናወነው በኢህአዴግና ደህንነት ቢሮ ቅንጅት ነው። ሂደቱም በመጀመሪያ የፓርቲው ጽ/ ቤት ከወጣትና ሴት ሊግ አመራሮች ለስራው የተመለመሉትን ይቀበላል። ይህንን ተግባር በበላይነት ስመራ የነበረው እኔና የድርጅት ጉዳይ ሀላፊ የነበረው ካሚል አህመድ ነበርን። በማስከተል እኛ የተቀበልነውን ስም ዝርዝር ለደህንነት ቢሮ አሸገን እንልካለን። የደህንነቱ ጽ/ ቤት በአሱ እጅ ያሉትን ጨምሮ የጀርባ ታሪካቸውን ያጠናል። በማጣራቱ ላይ ተመስርቶ የመጨረሻዎቹን ተቀጣሪዎች በቀጥታ ወደ አየር መንገድና ኤርፓርቶች ድርጅት ይልካል።

እንግዲህ ከገዚያቶች በኋላ ባደረግነው የናሙና ጥናት የመጀመሪያ ችግር ያገኘነው የቅጥር ሂደቱ ላይ ነበር። የደህንነቱ ቢሮ እኛ ከሁሉም ብሔረሰቦች መልምለን የላክንለትን ወደ ጎን ትቶ 75% የሚሆኑ ተቀጣሪዎችን የህወሓት ወጣት ሊግ አባላት አድርጓል። ለምሳሌ በ1999 ዓ.ም. ኢጋማሽ ላይ በጅምላ ከተቀጠሩት 400 ወጣትና ሴቶች ውስጥ ከ300 በላይ የህወሓት ሊግ አባላት መሆናቸውን ደረስንበት። በዚህ ሳይወሰን ከተቀጠሩት ሰዎች መካከል በተመሳሳይ ፐርሰንቴጅ ወደ መምሪያና ቡድን ሀላፊነት የመጡት የህወሓት ሰዎች ሆኑ።

በዚህ ምክንያት የተቋሙ ኢመደበኛ ቋንቋ አዋጅ ሳያስፈልገው ተቀየረ። የቋንቋው መቀየር እርስ በራስ በሚደረግ ምልልስ ቢሆን ባልከፋ ነበር። ነገር ግን ተቀጥረው የሚሰሩ የሌላ ብሄረሰብ

My text!

ተወላጆች ዘንድ የፈጠረው ጫና ማል አልነበረም። አንድ ስሙን መጥቀስ የማልፈልገው ከኤርትራ በሄረሰብ የተወለደ ወጣት ሰራተኛ ቃለመጠይቅ ስናደርግለት የነገረንን ቁምነገሮች እዚህ ጋር ላንሳ። በአንድ ወቅት ወጣቱ ባጋጠመው ችግር ምክንያት የእዝ ሰንሰለቱን ጠብቆ ከቅርብ አለቃው እስከ ሶስተኛ እርከን ሄዶ ነበር። በየደረጃው ያሉት አለቆች ቅሬታውን ከሰሙ በኋላ እርስ በራስ የሚጨቃጨቁት እሱ ባይተዋር በሆነበት የትግርኛ ቋንቋ ሆነ። ከዚህ ወጣትም ሆነ ከሌሎች ሰራተኞች መገንዘብ የቻልነው ሌላው ነገር የአየር መንገዱ ደንበኞች ሳይቀር "ቡሔር ተኮር" እድሉ እንደሚፈፀምባቸው ነው። በተለይ ከምእራቡ አለም የሚመጡ ኢትዮጵያውያን ስም ከአነ እያታቸው እየታየ ለያዙት እቃ ቀረጥ እንዳይከፍሉ ይደረጋል።

በናሙና ጥናቱ ሁለተኛ ችግር የተመለከትነው በቦሌ አየር ማረፊያው የተለያዩ ተርሚናሎች ውስጥ የሚገኙት የንግድ ድርጅቶች በግልጽ ጨረታ እንደማይከራዩ፣ የቲወሰኑት ማን ባለቤት እንደሆናቸው የማይታወቁና ለመንግስት ማስገባት የሚገባቸውን የቦታ ኪራይና የንግድ ግብ እንደማያስገቡ የሚያመላከት ነበር። እነዚህ ነጋዴዎች የጌጣ ጌጥ፣ የህትመት ውጤቶች፣ ባህላዊ ቁሳቁሶችና ሌሎች አገልግሎቶችን የሚሸጡ ናቸው። መረጃው የደረሰው የደህንነት ቢሮ የኤርፖርቶች ድርጅትን በማቻኮል በዛው አመት "ኤሮቲካል ያልሆኑ የገቢ ምንጮችን ለማስተዳደር የወጣ መመሪያ" የሚል መመሪያ እንዲወጣ ተደረገ። ይህም ሆኖ የተወሰኑት በንግድ ስም የስለላ ስራ የሚሰሩ ናቸው በማለት በዜሮ ዋጋ በኮድ ስም እንዲከራዩ ተደረገ። በጥልቀት ምርመራውን ስንቀጥል በአነስተኛ ዋጋ የተከራዩት ሱቆች የጉና ሆነው ተገኙ። ጉና በቅጥር እንዲሰሩ ያደረጋቸው ሴቶች አብዛኞቹ የደህንነት ቢሮ ሀላፊዎች የቅርብ ዘመዶችና ውሽማዎች ናቸው። ቃለ መጠይቅ ያደረግንላቸው ሰራተኞች በተርሚናልና በትሰማሩበት የንግድ ዘርፍ እየጠቀሱ " እከሊት የእከሌ ናት! ለሊቱን ሙሉ እዚህ የምሽት ከሰብ ሲጨፍሩ ያድራሉ" የሚሉ ጥቆማዎችን ሰምተናል። ገላቸውን ሸጠው ከሚተዳደሩ የቡና ቤት ሰራተኞች ውስጥ ከደህንነት ሀላፊዎች ጋር በፈጠሩት ቅርበት የጉናን ሱቅ ባለቤት የሆኑም ጭምር ይገኙበታል። እነዚህ በልዩ ሁኔታ ንግዱን ብቻ ሳይሆን የስለላ ስራውን የሚሰሩት እንስቶች ሙሉ ለሙሉ በሚባል መልኩ የትግራይ ተወላጆች ናቸው።

እንግዲህ ጉና በዚህ መልኩ በቦሌ አየር ማረፊያ ተርሚናል ውስጥ የሚገኙ የንግድ ቤቶችን ተቆጣጥሯል። በትግራይ የሚገኙት ኤርፖርቶችም ተመሳሳይ እጣ ደርሷቸዋል። እነ አተይ ታደለ

My text:

በእቅድ ደረጃ በመላው ኢትዮጵያ የሚገኙ ኤርፖርቶችን በሞኖፖሊ ለመያዝ አልመው ተነስተዋል። በዚህ ፍጥነታቸው ከቀጠሉ የማይቆጣጠሩበት አንዳችም ምክንያት አይኖርም።

ምዕራፍ **11**

My text!

“ኪድሬዋ ጓደኛዬ”

“እነዚህ ተቋማት ሲመሰረቱ ጀምሮ ከማንኛውም የግል ኩባንያ በላይ ሆነና መመሪያን አክብረው መሔድ እንዳለባቸው ያውቃሉ። ስራቸውም በዚህ የሚመራና ከማንኛውም ተቋም በላይ በዚህ ተመርተው የሚሄዱ ናቸው።”

መለስ ዜናዊ

የአብዮታዊ ዴሞክራሲ የልማት አቅጣጫ

“ሜጋ ኪነጥበብ ማዕከል አመታዊ ዝቢውን ባለማሳወቅ፣ ትርፍ አግኝቶ እያለ ከስሬያለሁ በማለቱ፣ ቫት ሰብስቦ ባለመክፈሉ በሦስት ወንጀሎች ጥፋተኛ ተባለ።”

ሪፖርተር ጋዜጣ

ጥር 23 ቀን 2005 ዓ.ም.

***

የካቲት 10 ቀን 2015 ዓ.ም_

በጠዋት ከአንቅልፈ ስነሳ በፌስቡኬ የውስጥ ገጽ ውስጥ አንድ መልእክት ተቀምጧል። መልእክቱን ያስቀመጠችልኝ በኢህአዴግ ቢሮ አብረን ስንሰራ የነበረች የቀድሞ የስራ ባልደረባዬ ነበረች። በመረጃ ደረጃ በኢህአዴግ ቢሮ የሴቶችን ጉዳይ የሚከታተሉት ሁለት ከፍተኛ ካድሬዎች ሀገር ለቀው ተሰደዋል የሚል ስለሰማሁ በደረሰኝ የውስጥ መልእክት ብዙም አልተገረምኩም። ከእለታት በአንዱ ቀን እንደሚያገኙኝ ተስፋ አድርጌያለሁ። እንደ እውነቱ ከሆነ የሚከዱ እሊያም በተለያየ ምክንያት ሀገር ጥለው የወጡ ካድሬዎች መረጃ ሊያቀብሉኝ ስለሚፈልጉ መዳረሻቸው መሆኔ ውስጤን ያስደስተዋል።

በውስጥ በኩል ባስቀመጠችልኝ ስልክ ደወልኩ ። ካድሬዋ ጓደኛዬ ስልኳን አነሳች። ለሰዓታት የድሮ ድርጅታችንን ውስጠ-ገመና ተጫወትን። ሀገር ጥዬ ከወጣሁ በኋላ በኢህአዴግ ውስጥ ብዙ ለውጦች መኖራቸውን፣ በተለይም ከአቶ መለስ በኋላ የፓርቲው ጉዞ ከድጡ ወደማጡ እንደሄደ አጫወተችኝ። የመጀመሪያው ማስታወሻዬ "የመለስ ትሩፋት ባለቤት እልባ ከተማ" በኢህአዴግ ውስጥ የብርጭቆ ማዕበል አስነስታ እንደነበር ነገረችኝ። "ጓድ በረከት ስምኦን" የአዲስ አበባ ኢህአዴግ ጽ/ቤትን ልዩ ትዕዛዝ በመስጠት የከተማይቱን መሬት የጨረሱት ህጎችና መመሪያዎች ተሠንደው እንዲሰጡት በማድረግ መውሰዱን አጫወተችኝ። ተሰንደው ከተሰጡት ሰነዶች መካከል መመሪያ ቁጥር አንድ፣ አቶ አባይ ፀሀዬ (በአሊ አብዶ ውስጥ አድሮ) ከአያት መኖሪያ ቤት ስራ ድርጅት ጋር የተፈራረመውና አያት መሬት ሸንሸና የመሸጥ ኢ-ህገመንግስታዊ መብት የተሰጠውን ስምምነት፣ የአዲስ አበባ ዙሪያ የሚገኙ አርሶ አደሮች መብታቸው ሙሉ ለሙሉ የተነጠቀበት ሁከት ይወገድልኝ አዋጅ፣ መመሪያ ቁጥር ሁለት፣ አቶ መለስ ከኮረኔል በላይ የሆኑ የጦር መኮንኖች አዲስ አበባ ላይ 500ካ.ሜ. ቦታ እንዲሰጣቸው ያዘዘበት መመሪያ፣ በምርጫ 97 ማግስት ሐምሌ ወር በፓርላማ የወጣው የመሬት አሊቃቀቅ አዋጅና መመሪያ ቁጥር ሶሶት እንደሚገኝበት ነገረችኝ። እነዚህ ሁሉ ህጎች፣ አዋጆች መመሪያዎችና ውሎች የአዲገንትን መሬት ለመውረር የወጡ መሆናቸው በፓርቲው ውስጥ መነጋገሪያ እንደነበር አጫወተችኝ።

ወጋችን በስልክ ማለቅ ስላልቻለ በአካል ለመገናኘት ተቀጣጠርን። ያረፈችበት አካባቢ ሔጄ አገኘኋት። ካድሬዋ ወዳጄ ብዙም አልተቀየረችም። እርግጥ ኢህአዴግ ቤት መቆየት በራሱ ከሚፈጥረው የህሊና መላሸቅ ገና ያልተላቀቀች መሆኑ ያስታውቅባታል። በዛ ላይ የነበረን እንዳልነበር አድርጎ ኑሮን በአዲስ መልኩ የሚያስጀምረው ስደት የሚፈጥረው ጫና ቀላል አይደለም። በስደት የሚኖርበትን ሀገር የአኗኗር ዘይቤ ከራስ ባህልና አስተዳደግ ጋር ለማጣጣም ጊዜ መፍጀቱ አይቀርም። በተለይ እንደ አሜሪካን ያለ ለየት የሚል ባህልና አስተሳሰብ ካላቸው ማህበረሰቦች ጋር በቀላሉ መዋሀድ ያስቸግራል።

ከካድሬዋ ወዳጄ ጋር ቤተሰባዊ ህይወት ከተጠያየቅን በኋላ፣

"ከመለስ ሞት በኋላ አርከበ እቁባይ አዜብን ለመበቀል ተንቀሳቅሷል የሚባለው ምን ያህል እውነት ነው? ማለቴ በኢህአዴግ ቢሮ የነበረው ድባብ ምን ይመስል ነበር?" በማለት ጠየኳት።

ከአፌ ተቀብላኝ፣

"መብቀል ብቻ ! ከሐይለማርያም ጋር ተመሳጥሮ ሊያሳስራት ነበር። እድሜ [illegible] ባረከት፡ ስምአን ትብል።" አለችኝ፣

"እንዴት? ሐይለማርያም ደግሞ ምን አገባው?"አልኳት።

በመገረም ውስጥ ሆና፣

"አቴጌ አዜብ ባሏ የሞተ ሰሞን ጨርቋን ጥላ መብረር ነበር የቀራት። መለስ የተቀመጠበትን ወንበር ተዋርዶ ማየት አልፈልግም ብላ ፓርላማ አልገኝም በማለት የተናገረችው ሐይለማርያምን አበሳጭቶት ነበር። የሚገርምህ መለስ ከሞተ በኋላ ፓርላማ ተገኝታ አታውቅም። ኢቲቪ ዜና፣ የፓርላማ ፕሮግራምና ድሮ ባሏ ይገኝበት የነበረ ፕሮግራም ላይ ጓድ ሐይለማርያም ተገኝቶ ካየች ቴሌቪዥኗን በጓደኞቿ ፊት ድርግም ታደርገዋለች። የሐይለማርያምን መብሳጨት ያወቀው አርከበ መንግስታዊ ስልጣኑን እንዲጠቀም በሚስጥር በፀረ ሙስና የተጠና መረጃ ሰጥቶት ነበር። መረጃው አቴጌን እስከ 15 አመታት የሚያሳስር ነበር" አለችኝ።

"እኔ እኮ ከፓርላማ ወንበሯን ለቃ ወደ አዲስ አበባ ምክር ቤት ስትገባ ለከተማው ከንቲባነት ታጭታ እንደሆነ የተነገረው እውነት መስሎኝ ነበር።"

'እንገቷን በእሉታ እየነቀነቀች፣

"አይደለም። ከንቲባነት ከኦሮሞና አህዴድ አባልነት ውጭ እንደማይታሰብ የተወሰነው አንተ እያለህ እኮ ነው። አረሳኸው እንዴ?..." በማለት ጠየቀችኝ።

"ኧረ! አልረሳሁትም። ምን አልባት የተለወጠ ነገር ካለ ብዬ ነው"

"እንዴት ይለወጣል? ይህን ማባባያ መቀየርማ በአህዴድ ዘንድ ቅሬታ ሊፈጥር ይችላል። ያም ሆነ ይህ አዜብ ወደ አዲስ አበባ ምክር ቤት የመጣችው ፓርላማ እንገቴ ቢቆረጥ አልሄድም በማለቷ እንጂ ለከንቲባነት ታስባ አይደለም" አለኝ።

ሁኔታዎችን ማያያዝ ሲያቅተኝ፣

"አዜብን ተለይቶ የሚያሳስራት የሙስና ወንጀል ከየት ተገኘ? አርከበ በምን የሞራል ልእልና አዜብን ሊከሳት ተነሳ?" በማለት ጠየኳት።

አተኩራ እየተመለከተችኝ፣

My

"ጓድ አርከበ ቀላል ሰው እንዳይመስልህ። አቴጌ ላይ በጀርባ በኩል ነበር እንደ እጥብ ሊጠመጠምባት የነበረው። የሚጋ ስራአስኪያጅ የነበረውን ጓድ እቁባይ በርሄ ታውቀዋለህ አይደል?" አለችኝ።

ጭንቅላቴን እየወዘወዝኩ፣

"በደንብ አውቀዋለሁ። የኪነጥበብ ሙያተኞች ላይ የሚሰራውን የድርጅትና ፖለቲካ ስራ በበላይነት ሲመራ የነበረው እሱ ነበር። ከምርጫ 97 በኋላ በአሙቴ የተከበረውን የግንቦት ሀያ በአል ለማክበር የተቋቋመው ሽብርቅ ኮሚቴ ውስጥ አብረን ሰርተናል" አልኳት።

እቁባይ በርሄ ከህወሓት ኩባንያዎች አንዱ የሆነውን ሚጋ የኪነጥበባት ማእከል በስራ አስኪያጅነት ሲመራ የነበረ ሰው ነው። ይህ ከተማ ቀመስ ካድሬ በብዙዎቹ የኢትዮጵያ ኪነ ጥበብ ባለሙያዎች ዘንድ በሰፊው የሚታወቅና የማይደፈር ሰው ነው። ርግጥም እቁባይ የገባበት ነገር በአብዛኛው ከፍፃሜ ደርሶ በመመልከታቸው ለሰውየው የተለየ ቦታ ቢሰጡት የሚገርም አይደለም። ነብሱን ይማረውና አርቲስት ጥላሁን ገሰሰ ሳይቀር ጉዳዩች ሲንቀራፈፉ " እቁባይ የት አለ? እሱ ቢኖር ኖሮ ቶሎ ያልቃል" በማለት አርቲስቶች በተሰበሰቡበት እንደሚናገር ኑሮውን በአገረ አሜሪካ ያደረገ አንድ ተወዳጅ የሙዚቃ ባለሙያ አጫውቶኛል።

በዚህም ምክንያት ከህወሓት ተልእኮ እየወሰደ የኪነጥበብ ባለሙያዎችን ይሰልላል። ኤ፣ ቢ፣ ሲ፣ ዲ የሚል ደረጃ እያወጣ ለኢህአዴግ ቢሮ ያቀርባል። የሰጠውን ደረጃ መሰረት አድርጎ ገዥው ፓርቲ እና መንግስት በሚያዘጋጃቸው ኮንሰርቶች ላይ እነማን መሳተፍ እንዳለባቸው የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል። እናም እንደዚህ አይነት ስራዎችን ሲሰራ በቅርበት ተመልክቸዋለው። በተለይ በ1998 ዓ.ም. የኢህአዴግን የልደት በአል ለማክበር በተቋቋመው ኮሚቴ ውስጥ ቢጋራ በሰራን ወቅት እያንዳንዱን የኪነ ጥበብ ባለሙያ በፈርጅ በፈርጅ እያስቀመጠ ለኮሚቴው ሰብሳቢ ለነበረው የማስታወቂያ ሚኒስትር ብርሃን ሀይሉ ሲያቀርብ በስብሰባው ተገኝቻለሁ። በዚህም ሳይወሰን መገኘት የሌለበት ስብሰባ ላይ እየተገኘ ድርጅታዊ መመሪያ ሲያስተላልፍ እንደነበር አውቃለሁ። በተለይም የድምፃውያን ማህበር ሲቋቋም በአንዳንድ ድምፃውያን ዘንድ ቅሬታ እየቀረበም እንዲሳተፍ ተደርጓል።

ከድራዳዋ ጓደኛዬ የያዘችውን ቡና እየተጎነጨች፣

"አርከበ ሜጋ ኪነጥበባት ማዕከል ስራ እስኪያጅ የነበረውን ጓድ አቁባይ በመለና እንዲከሰስ ያቀነባበረው ነበር። ሜጋን በበላይነት የምትመራው ደግሞ አቴጌ መሆኗን ታውቃለህ፡ በማለት ስትናገር ድንገት አቋርጫት፣

"አቁባይና ወይዘሮ አዜብ እኮ እሳትና ጭድ ናቸው። ይሄ በሁሉም ካድሬዎች ዘንድ ይታወቃል። በአውቀት ስለሚበልጣት፣ ከተማ ቀመስ ስለሆነና ከሰው ጋር በቀላሉ መግባባት ስለሚችል ትቀናበታለች። ከስራው ያባረረችው እሷ እንደሆነች ነበር የማውቀው። በዚህ ምክንያት በሰፊው የተገመተው ራሷ አዜብ ልታሳስረው ፈልጋ እንደሆን ነበር" አልኳት።

በርግጥም አቁባይ በርሄ በብዙዎቹ ነባር የህወሓት ታጋዬች ዘንድ ጥሩ ስም የለውም። በደርግ ዘመን በአየር ሀይል ውስጥ ያገለገለ መሆኑና ደርግ ሊወድቅ ገደል አፋፍ ላይ እያለ ህወሓትን መቀላቀሉ የሀይል ሚዛን አይቶ እንደተሸበለለ ተደርጐ ይወሰድበታል። ከዛም አልፎ ውሎና አዳሩ ከተረከዘ ሎሚ ቆነጃጅት ጋር መሆኑ በቅናት አይን እንዲታይ ከማድረጉም ባሻገር "ሚስጥራችንን ሊያስወጣብን ይችላል" የሚል ጥርጣሬ እንዲያርፍበት አድርጓል።
አንገቷን እየነቀነቀችና ቡናዋን እያጣጣመች፣

"ትክክል ነህ። በጣም እንደምትቀናበት ይነገራል። ለነገሩ እናንተ አትሰሙም እንጂ በሴት ታጋዬች ዘንድ 'አዜብ ታጥቦ በተሰጣ ሙታንታም ትቀናለች' ይሏታል። በዚህ ምክንያት ከአቁባይ ጋር በተያያዘ ከኢህአዴግ ቢሮ ውጭ የተወራው አዜብ መረጃውን አውጥታ አሳሰረችው የሚል ነበር። ይህ የተሳሳተ ነው። በመጀመሪያ ጉዳዩ ወደ ሕግ ከሄደ ክሱ እሷ በበላይነት በምትመራው ተቋም ላይ ስለሆነ ቢያንስ በወንጀል ባያስጠይቃት በአመራር ድክመት ያስወቅሳታል። ...እስከዛሬ ድረስ የት ነበርሽ? ተቋሙን እንዴት ስትመሪው ነበር ያስብላል። በክሱ ላይ አይተኸው ከሆነ የማጭበርበር ወንጀል የተፈፀመው ለተከታታይ ስምንት አመታት (1995 -2002 ዓ.ም.) ያህል ነው። እንደ ሜጋ ሀላፊነቷ የአመት ገቢው ምን ያህል እንደሆነ፣ ምን ያህል ታክስ ለመንግስት እንደተከፈለ ጠንቅቃ ማወቅ ይጠበቅባታል። በሁለተኛ ደረጃ የመረጃው ምንጭ እሷ ብትሆን እና አቁባይ ይህንን ቢያውቅ ሌሎች በሁለቱ መካከል ያሉ በርካታ ሚስጥሮች ይወጣሉ። ስለዚህ አቴጌ በራሷላይ ገመድ አትጠመጥምም" በማለት ተናገረች።

"እሺ ባክሽ!" አልኳት የጀመረችውን እንድትጨርስልኝ በማሰብ።

ጉሮሮዋን ጠራርጋ፣

"እየህ የእርከበ ተንኮል እዚህ ጋር ነው። በቀጥታ እንዲከሰስ የተደረገውም እቁባይ በርሄ እንዲሆን አደረገ። ከአዜብ ጋር ስለተጣሉ እሷ አስከሰሰችው የሚለው እንዲወራ ለኔትወርኩቹ አስተላለፈ። ኢህአዴግ ጽ/ቤት ያሉት ሴት ተጋዳሊቶችን በሙሉ እንዲሳተፉ አደረገ።...ያከሱን ጭብጥ ብታየው ግን ሜጋ ባደረገው የንግድ እንቅስቃሴ ካገኘው ገቢ ላይ ለመንግስት ገቢውን አሳውቆ ባለመክፈሉ፣ ትርፍ አግኝቶ እያለ ወጪውን ከፍ አድርጎ አሳሳች ማስረጃ በማቅረቡና የሰበሰበውን የተጨማሪ እሴት ታክስ አሳውቆ ባለመክፈሉ ምክንያት ነው። ወንጀሉ የተመሰረተበት። ይህ ውሳኔ ደግሞ የሜጋ ኔት ኮርፖሬት ስራ አስኪያጅ የሆነችው አቴጌ አዜብ ስለሆነች በተባባሪነት ያስከስሳት ነበር።"

My text!

እሁንም ጉዳዩ አልገባኝ ብሎ፣

"በእውነት ግራ ኢጋባሽኝ። በ1999እም የመንግስት ተቋማትና የኢህአዴግ ኩባንያዎች የሙስና ደረጃ እንዲያጠና የተደረገው በወቅቱ የአደረጃጀት ሀላፊ የነበረው ሐይለማርያም ደሳለኝ ነበር። በመሀል አቶ መለስ ሀሳቡን ቀይሮ የኢህአዴግ ኩባንያዎች ጥናት እንዲቋረጥ ተደርጎ የመንግስት ተቋማት ላይ ብቻ እንዲያተኩር ተደረገ" አልኳት።

እስከትዬም፣

"ከዚህ ቀደም የማውቀው አሰራር ተቀይሯል ማለት ነው?...ድርጅት መንግስትን ይመራል የሚለው ተገልብጦ መንግስት ድርጅትን መምራት ጀመረ እንዴ?... ሙስናው በኢህአዴግ ደረጃ በፓርቲ መዋቅር ሳይታይ እንዴት ወደ ፍርድ ቤት እንዲሄድ ተደረገ?..." በማለት በጥያቄ አጣደፍኳት።

የቀድሞ ካድሬ ጓደኛዬ እየሳቀች፣

"ይሄን ልነግርህ ስል ነው ያቋረጥከኝ። በወቅቱ የኢህአዴግ ቢሮ የታመሰበትን ምክንያት እሁን ያነሳኸልኝ ጥያቄዎች ናቸው። በረከት 'ድርጅት መንግስትን መምራት አለበት ' የሚለው መርህ ተጥሷል በማለት ኢህአዴግን በአንድ እግሩ አቆመው። መረጃው በጋዜጣ ወጥቶ ወደ ህዝብ ተሰራጭቶ ስለነበር የኢህአዴግ ጽ/ ቤት አላፊው ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ደመቀ መኮንን ሁላችንንም ሰብስቦ የበረከትን አቋም አጠናከረ። በረከት ጠቅላይ ሚኒስትር ሐይለማርያምን

በመርህ መጣስ ከሰሰው። በረከትና ሐይሌ በማያባራ ፀብ ውስጥ ገቡ። በረከት አሉር በመጨረሻ፣ ሐይለማርያም የአቅም ችግር አለበት። ሊመራን አይችልም" የሚል ግምገማ አስቀመጠለት። ጉዳዩ እየከረረ ሲሄድ አባይ ፀሀዬ በመሀል ገብቶ አበረደው። እንደለመደው ውሀ ቸለሰበት" አለችኝ።

"ለነገሩ በሐይለማሪያም እና በረከት መካከል ከፍተኛ ችግር መፈጠሩን ሰምቻለሁ። አባይ እንዴት አበረደው?"

በማለት መልሼ ጠየኳት።

My text!

በድጋሚ እየሳቀች፣

"ሐይለማርያም መርህ የጣሰው በልምድ ማነስ እንጂ በአቅም ችግር እንዳልሆነ አስመረበት። ከዛ በተጨማሪም የፍርድ ቤት ሂደቱ የተሟላ መረጃ በቀረበበት ሁኔታ እንዲቋረጥ ማድረግ ከፍተኛ የፓለቲካ ኪሳራ ስለሚያመጣ እንዲቀጥል፣ የመጨረሻው ብይን ላይ ጣልቃ በመግባት ማስተካከያ እንዲደረግ ወሰነ" በማለት ነገረችኝ።

እኔም እየሳቅኩኝ፣

"ለዚህ ነዋ የፍርድ ብይኑ በጣም አስገራሚ የሆነው። ምንአልባት በኢትዮጵያ የፍርድ ቤት ታሪክ ውስጥ ጉላ ያለ የቅሌት ማስተማሪያ እንደሚሆን አልጠራጠርም። እንደውም የፍርድ ቤቱ ሂደትና ውሳኔ በሪፓርተር ጋዜጣ ላይ ጥር 30 ቀን 2013 እ.ኤ.አ. የወጣውን አላነበብሽም? አልኳት። መልሷን ሳልጠብቅ የሪፓርተር ጋዜጣን ዘገባ ኮፒ ካደረኩበት የእጅ ስልኬ እያወጣሁ እንደሚከተለው አነበብኩላት፣

እንዲህ ይላል፣

ሜጋ ኪነጥበባት ማዕከል የገንዘብ ቅጣት ተጣለበት።

የአቶ አቁባይ በርሄ የ53 ወራት የእስር ቅጣት ተገደበ።

ከሐምሌ 1996ዓም እስከ 2002 ዓም ካደረጋቸው የንግድ እንቅስቃሴዎች ካገኘው ገቢ ላይ ለመንግስት ገቢውን አሳውቆ የገቢ ግብር፣ የሰራተኛ ታክስ እንዲሁም ቫት አልከፈለም። ሜጋ ኢንተርፕራይዝ ጥፋተኛ የተባለበት የመጀመሪያ ክስ 40ሺህ ብር የሚጠጋ የትርፍ ግብር ሳለመክፈል ገቢውን አሳንሶ በማቅረቡ ነው። ሁለተኛው ጥፋት 400ሺህ ብር መክፈል ያለበትን

ሻት በማጭበርበሩ ነው። በሶስተኛ ደረጃ የሰራተኛ የገቢ ታክስ የማይከፍል በመሆኑ ጥፋተኛ የሆነበት ነው።

በተናደደ ስሜት ውስጥ ሆኜ፣
"እስቲ እግዜር ያሳይሽ ለስምንት ተከታታይ አመታት መንግስትን እያጭበረበረ የኖረ ግለሰብ ለአገሪቱ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረከተ የሚል ማእረግ ሲሰጠው አያሳፍርም!_በሶስት ወንጀሎች ጥፋተኝነቱ የተረጋገጠበት ሰው፣ የሶስቱ ክሶች ድምር 15 አመታትና 50ሺህ ብር የመነሻ ቅጣት የሚጣልበት፣ አሊያም ሕጉ ባስቀመጠው የመጨረሻ ገደብ በዝቅተኛው አራት አመት ከአምስት ወራት መቀጣት ያለበት ሰው ከሚታሰር ይልቅ በሁለት አመት ገደብ ይቆይ የሚል ውሳኔ የኢትዮጵያ የፍትህ ስርአት ላይ የመቃብር አበባ የማስቀመጥ ያህል ነው" አልኳት።

መስማማቷን ገልጻ፣ ለሌላ ጊዜ ለመጫወት ቀጠሮ ይዘን ተሰነባበትን።

እነሆ! እውነቱ ይህ ነው። የኤፈርት ኩባንያ አንድ አካል የሆነው ሜጋ ኪነጥበባት ማዕከል የአቶ መለስ መንግስት መቀመጫ የሆነችው አዲስ አበባ ውስጥ ቁጭ ብሎ ለስምንት አመታት ገቢውን አያሳውቅም። ትርፍ አግኝቶ እያለ ከስሬያለው እያለ ሪፖርት ያደርጋል። ከህዝቡ ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ ሰብስቦ ለራሱ ይወስዳል። እንግዲህ ኤፈርትን የመሳሰሉ ኩባንያዎች የሚፈጽሙት ወንጀል ይህን ይመስላል።

በተቃራኒው አቶ መለስ ጽፎ ባስነበበንና ባሰለጠነን መጽሀፍ ውስጥ ኤፈርትን የመሳሰሉ የፓርቲ ኩባንያዎች ከማንም በላይ ህግ እንደሚያከብሩ፣ ከመንግስት ቅንጣት ያህል ገንዘብ እንዳልወሰዱ እንደሚከተለው ይነግረናል፣
"እነዚህ ተቋማት በትጥቅ ትግሉ ወቅት በተገኘ ገንዘብና ንብረት የተቋቋሙ ናቸው።.. እነዚህ ከመንግስት ያገኙት ወይም የወሰዱት ቅንጣት ሳንቲም የለም። ወደፊትም አይኖርም። ..እነዚህ ተቋማት ሲመሰረቱ ጀምሮ ከማንኛውም የግል ኩባንያ በላይ ህግና መመሪያ አክብረው መሄድ እንዳለባቸውና ልዩ ድጋፍ ሊጠይቁም ሆነ ሊቀበሉ እንደማይገባቸው ያውቃሉ። ስራቸውም በዚህ የሚመራና ከማንኛውም ተቋም በላይ በዚህ ተመርተው የሚሄዱ ናቸው።"

እንግዲህ አቶ መለስ ያሉ አንዳች እፍረት በመጽሐፍ መልክ የሚጽፈው የተጠቀሰውን ነው። በተጨባጭ የሚታየው ግን የኤፈርት ኩባንያዎች ከላይ የሚያጭበረብሩና በሙስና የተዘፈቁ ናቸው። የትዳር አጋሩ ለሁለት አስርተ አመታት የምትመራው ሜጋ ኮርፖሬት በትርፍ እየተንበሸበሸ ለመንግስት መክፈል ያለበት ግብር ሲጠየቅ የኪሳብ መዝገብ ይዞ ይቀርባል። ግብር ክፈሉ ብለው የጠየቁ ሙያተኞችንም በማስፈራራትና ከስራ በማባረር መቀጣጫ ያደርጋል። ዛሬ በርካታ ነባር ነጋዴዎች የተጨማሪ እሴት ታክስ አልከፈላችሁም በሚል "ኢኮኖሚካል ኢንስትሩመንት" ተጠልፈውና ቢዝነሳቸው ተዘግቶ ዘብጥያ ወርደዋል። በተቃራኒው በተጨባጭ ማጭበርበርና ሙስና የፈፀሙትና ማስረጃ የቀረበባቸው የኤፈርት ኩባንያዎች የሚደርስባቸው የለም። ለዚህ አገላለጥ ጥሩ ምሳሌ ከሚሆኑት ውስጥ ሜጋ እና መስፍን ኢንዱስትሪያል ይገኙበታል።

397

የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በከባድ የሙስና ወንጀል ክስ የመሰረተባቸው የገቢዎች ባለስልጣን ሀላፊዎቹ ሚኒስትር መላኩ ፋንታና ገ/ዋህድ መዝገብ ላይ መስፍን ኢንዱስትሪያል ኢንጂነሪንግ ተካቷል። የኤፈርት ኩባንያ የሆነው መስፍን ኢንዱስትሪያል ከተለያዩ ሀገሮች የሚያስገባቸውን እቃዎችና ማሽኖች ቀረጥና ታክስ ሳይከፍል የሚያስገባ ነው። ኩባንያው የሚጠበቅበትን ግብርና ታክስ አይከፍልም። የፀረ ሙስና ኮሚሽን ባልተለመደ ሁኔታ እቃቸውን ሳያስፈትሹ እና ቀረጥ ሳይከፍሉ ወደ ሀገር ቤት የሚያስገቡ ካላቸው 20 ድርጅቶች ውስጥ በቅድሚያ የሚገኘው መስፍን ኢንዱስትሪያል ሆኗል።

ከኤፈርት ኩባንያዎች ውስጥ የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲመራ ግብ የተቀመጠለት መስፍን ኢንዱስትሪያል መንግስታዊ ድጋፍና ሙስና ተፈቅዶለት በሚያስደንግጥ ሁኔታ እየተመነደገ ሔዷል። ኤፈርትን በቻይና እና በበለፀጉ አገሮች የቴክኖሎጂ ደረጃ በማመጣጠን ላይ የሚገኘው መስፍን ኢንዱስትሪያል ገንዘብ በማስገኘትም ቁልፍ ተቋም ሆኗል። አቶ መለስ ከመሞቱ በፊት የኢትዮጵያ መንግስት ይሰራቸዋል ብሎ በትራንስፎርሜሽን እቅዱ ያካተታቸው ሜጋ ፕሮጀክቶች በሙሉ ከመስፍን ኢንዱስትሪያል ጋር እንዲተሳሰሩ ተደርገዋል። ከ71 ቢሊዮን በላይ የተመዘበረበት እና አገር ጉድ ያሰባለው የስኳር ፕሮጀክት ከ5 ቢሊዮን ብር በላይ የዜግነት ድርሻውን የወሰደው መስፍን ኢንዱስትሪያል ነው። በአገሪቱ ይቋቋማሉ ከተባሉት የስኳር ፋብሪካዎች ለ8 ያህሉ የማምረቻ ገንዳ ግንባታ ተከላ እሰራለሁ በማለት የኢትዮጵያን ህዝብ ገንዘብ እንዲዘርፍ ተደርጓል። ...ከውጭ ለሚያስመጣቸው እቃዎች ቀረጥ የማይከፍለው መስፍን ኢንዱስትሪያል በአውሮፓ

ሀብረት ብድር የሚሰራውን ከ6ሺህ ኪሎ ሜትር ያላነሰ የኢትዮ-ጅቡቲ የባቡር መስመር የማስፋፋት አገልግሎት ዋነኛ ተሳታፊ ነው።... የአዲስ አበባ ኤርፖርት ማስፋፊያ፣ የጢስ አባይና ባህርዳር የኤሌክትሪክ ግንባታ የአንበሳ ድርሻውን የወሰደው መስፍን ኢንዱስትሪያል ነው።... በመላው ኢትዮጵያ ለሚገኙ መኪኖች ታርጋ እንዲሰራ ለትራንስፖርት ሚኒስትር ትዕዛዝ በመስጠቱ በየእለቱ በማይነጥፍ ሚሊዮኖች እንዲንበሸበሽ ሆኗል። በኦሮሚያ፣ በአማራ፣ በደቡብና በተቀሩት ሌሎች ክልሎች የሚንቀሳቀሱ መኪኖች በሙሉ በቅርጽ የሚሰራውን ታርጋ ገዝተው የሚያመጡት ከመስፍን ኢንዱስትሪያል ነው።... በመላው ኢትዮጵያ የሚተከሉ የነዳጅ ማጠራቀሚያ ታንከሮችና ቱቦዎች የሚመረቱትና የሚተከሉት በመስፍን ኢንዱስትሪያል ነው። በአሁን ሰዓት ከውጭ የሚመጡት የነዳጅ ማጠራቀሚያ ታንከሮች እንዲቀሩ ተደርገዋል።_ የአገሪቷን 82% የመኪና ኮፈን (ካርጎ) ገበያ የተቆጣጠረው መስፍን ኢንዱስትሪያል ነው።_ በሞተር ተሸከርካሪ ሽያጭ ሁሉም ክልሎች በጋራ ተደምረው መስፍን ኢንዱስትሪያል ላይ አይደርሱበትም። የማዕከላዊ ስታስቲክስ በ2002 ባወጣው የሞተር ተሸከርካሪ ሽያጭ መሰረት ትግራይ 64 ሚሊዮን፣ ደቡብ 14 ሚሊዮን፣ አማራ 7ሚሊዮን... ወዘተ መሆኑን በግልጽ የሚያመላክት ነው።

398

እንደ እውነቱ ከሆነ ከ70ሺህ በላይ ኢትዮጵያውያንን የቀጠፈው የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ለመስፍን ኢንዱስትሪያል እና እሱን አክሲዮን አዋጥተው ለፈጠሩት (ህይወት ሜካናይዜሽን)፣ ሱር ኮንስትራክሽን፣ ትራንስ ኢትዮጵያ እና አርከበ እቁባይ ፀሀይ የወጣበት ነበር።

ከመከላከያ ሚኒስትርነት ወደ ኤፈርት ዋና ስራ አስፈፃሚነት የተመደበው ስዬ አብርሃ እነዚህ የኤፈርት ኩባንያዎች የሀገሪቷን እንጡራ ሀብት እንዲያግበሰብሱ ቀጥተኛ ትዕዛዝ ሰጥቷል። በአቶ መለስ የሚመራውና ስዬ አብርሃ አባል የሆነበት ማዕከላዊ ኮማንድ የጦርነቱ ሎጅስቲክ አገልግሎት ከኤፈርት ኩባንያዎች ጋር እንዲተሳሰር አድርጓል። የሰራዊቱ ትራንስፖርትና የምግብ አቅርቦት፣ የውሃ ታንከርና የወታደራዊ ቤዞች በመገንባት ስራ የተጠመዱት የኤፈርት ኩባንያዎች ነበሩ። እንግዲህ ከ70ሺህ በላይ ኢትዮጵያውያን በበጉብና ጥይት ጭንቅላታቸው እየተበረቀሰ "ዘመቻ ፀሀይ ግባት!" ሲፈፀምባቸው፣ በተቃራኒው የኤፈርት ኩባንያዎች ለራሳቸው "ዘመቻ ፀሀይ መውጣት!" አውጀው በቢሊዮን ብሮች ሲንበሻበሹ ነበር።

የሆነው ሆኖ በዚህ መልኩ የእድገት ጎዳናውን እጠናክሮ የቀጠለው መስፍን ኢንዱስትሪያል በተሳካ መንገድ የቴክኖሎጂ ሽግግሩን እና የፋይናንስ አቅሙን እያጎለበተ ይገኛል። የተቋቋመበትን አላማ በአጭር ጊዜ እውን ለማድረግ ከውጭ ታላላቅ ኩባንያዎች ጋር በሰብ ኮንትራት የሚሰራበትን ሁኔታ ፈጥሯል። ከሀንዱ ሶናሊካ ኢንተርናሽናል ትራክተር እምጥቶ በመገጣጠም በከፍተኛ ትርፍ ይሸጣል። በያዝነው አመት ደግሞ ከጀርመን የመኪና አምራች ኩባንያ ጋር በመጣመር ወደ አዲስ ምዕራፍ በመሸጋገር ላይ ይገኛል።

ሪፖርተር ጋዜጣ በማርች 12 ቀን 2016 ቢዝነስና ኢኮኖሚ አምዱ "የመስፍን ኢንጂነሪንግ እና የጀርመኑ መኪና አምራች ጥምረት" በሚል ርዕስ ሰፊ የዜና ዘገባ ይዞ ወጥቷል። በዜና ዘገባው የመስፍን ኢንጅነሪንግ ዋና ስራ አስኪያጅ የሆነው አቶ ("ታጋይ") ሀብተ ሐዱሽ የሚከተለውን ይገልጻል፣

"ከኤፈርት ኩባንያዎች መካከል አንዱ የሆነው መስፍን ኢንዱስትሪያል ኢንጂነሪንግ በ1985 ዓ.ም. የተመሰረተ ነው። በወቅቱ ሰባት ሚሊዮን ብር ካፒታል ይዞ ወደ ስራ ገብቷል። ባገለገሉ የእጅ መሳሪያዎችና ማሽነሪዎች ስራ የጀመረው ይህ ኩባንያ ደረጃ በደረጃ እያደገ መገጣጠሚያ ፋብሪካ ወደ መገንባት ተሸጋግሯል። በር፣ መስኮት፣ የከሰል ማንደጃና የመሳሰሉትን በመስራት ወደ ስራ የገባው መስፍን ኢንጂነሪንግ በአሁኑ ወቅት ስራዎች ውስጥ በመሳተፍ ብቻ ሳይሆን አዳዲስ ምርቶችን ከባድ ተሽከርካሪን ጨምሮ ያመርታል። ኩባንያው መገጣጠም የጀመራቸው ተሽከርካሪዎች በከባድ ተሽከርካሪዎች አምራችነቱ ከ100 አመት በላይ ልምድ ያለው የጀርመኑ ኤም ኤ ኤን (MAN) ተሽከርካሪዎች ናቸው።... በአውቶሞቲቭ ኢንዱስትሪ ውስጥ ያለንን ትልቅ ራዕይ ለማሳከት የኤም ኤ ኤን ተሽከርካሪዎችን ገጣጥመን ማቅረባችን መስፍን ኢንጂነሪንግ ወደፊት መኪና ወደማምረት ደረጃ የሚደርስ መሆኑን ማሳያ ነው"

መስፍን ኢንጂነሪንግ ወደ አዲስ የእድገት ምዕራፍ የሚያሸጋግረው ተግባር ተሽከርካሪዎችን በመገጣጠም ለገበያ ማቅረብ መጀመሩ ነው። የመስፍን ኢንጂነሪንግ የምርት ሂደት ወደፊት ያራመደው ይህ የተሽከርካሪዎች መገጣጠሚያ ፋብሪካ በኢትዮጵያ የአውሮፓ ምርት የሆነ ከባድ ተሽከርካሪ የሚገጣጠምበት ቀዳሚ ኩባንያ እንዲሆን ማስቻል ነው። መስፍን ኢንጂነሪንግ እያሳየ ካለው እድገት ጋር የሚመጥን አደረጃጀት ለመፍጠር በማሰብ በአራት ቢዝነስ ዩኒቶች እንዲዋቀር ተደርጓል።

አንድ፡ የከባድ መኪናና ሎኮሞቲቭ ማምረቻ ቢዝነስ ዩኒት

ሁለት፡ የኢንዱስትሪ ዕቃዎች ማምረቻ ቢዝነስ ዩኒት

ሦስት፡ የኢንዱስትሪ ኮንስትራክሽንና ተከላ ቢዝነስ ዩኒት

አራት፡ የአውቶሞቲቭ የእርሻ መሳሪያዎች ማምረቻ ቢዝነስ ዩኒት

እነዚህን አደረጃጀቶች በመጠቀም መስፍን ኢንዱስትሪያል አሁን እያመረታቸው ካሉት የፋብሪካ ምርቶች ከ13 ቢሊዮን ብር በላይ አመታዊ ሽያጭ የማከናወን ደረጃ ላይ ደርሷል። ኩባንያው በአሁን ወቅት እያመረታቸው ካለው መካከል የደረቅና ፈሳሽ ጭነት ማጓጓዣ ተሳቢዎች፣ ሃይቤድ እና ሎውቤድ፣ የነዳጅ ማጠራቀሚያ ዲፖዎች፣ ለሲሚንቶ ፋብሪካ የሚያገለግሉ መሳሪያዎች፣ ለሃይድሮ ኤሌክትሪክ ሀይል ማመንጫ አገልግሎት የሚውሉ ፔንስቶከር ኢንቴክ ላይነር... ወዘተ ይገኙበታል። ከዚህ በተጨማሪ የኤሌክትሮ መካኒካል ተከላ ስራዎች፣ ለተለያዩ የኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች የሚያገለግሉ የማሽን ተከላ ስራዎች፣ የሲቪል ህንጻ ግንባታዎች፣ የነዳጅ ማጠራቀሚያ ቁሳቁሶች፣ ፕሮጀክቶችን ከጅምር እስከ ፍፃሜ በመስራት ላይ ይገኛል።

400

በመቀሌ 100 ሔክታር ላይ የሚያርፈው እና ከ15 በላይ የተለያዩ ኢንዱስትሪዎችን የሚያቅፈው የመስፍን ኢንጂነሪንግ የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ መንደር ግንባታ ሲጠናቀቅ የብረታ ብረት ማቅለጫ፣ የንፋስ ተርባይኖች፣ የክሬን፣ የአውቶብሶችና የባቡር ፉርጎዎች ማምረቻዎች ይኖሩታል። በተመሳሳይ መንገድ በውቅሮ ከተማ በ50ሺህ ካሬ ሜትር ላይ እየተገነባ ባለው የመስፍን ኢንዱስትሪያል መንደር የቤት አውቶሞቢሎች፣ ሚኒባሶችና ፒካፕ ተሽከርካሪዎች ይመረታል። እነዚህ ግዙፍ ኢንዱስትሪዎች ሲጠናቀቁ የመስፍን ኢንዱስትሪል አቅም በአስር እጥፍ የሚያድግ ሲሆን፤ የሚፈጥረው የስራ እድል አሁን ካለበት 2500 ወደ 10ሺህ የሚያድግ ይሆናል።

***

የካቲት 24 ቀን 2015

ሁለተኛ ቀጠሮ

ስርአቱ በቃኝ ብላ ወደ አሜሪካን ከተሰደደችው ካድሬ ጓደኛዬ ጋር ለሁለተኛ ጊዜ ተገናኝተናል። ስደት የኢትዮጵያውያን እጣ ፋንታ በመሆኑ በየመንገዳችን የምናየው ኢትዮጵያዊ